ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር


# በደቡብ ክልል ሥራ ላይ ባሉ የ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ


በፈለቀች እሸቱ



ህዳር፣2014ዓ.ም

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

# በደቡብ ክልል ሥራ ላይ ባሉ የ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ


በ

ፈለቀች እሸቱ


ዋና አማካሪ፡- በቃሉ ፈረደ (ተ/ፕሮፌሰር)

ረዳት አማካሪ፡- ሀብታሙ እንግዳው

አማርኛን በማስተማር ስነ-ዘዴ ማስተርስ ድግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

ህዳር፣2014ዓ.ም

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ለድህረ ምረቃ መርሐ ግብር መሚያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

በደቡብ ክልል ሥራ ላይ ባሉ የ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት በፈለቀች እሸቱ ኃይሌ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ የዩኒቨርሲቲዉን የጥራትና ወጥነት መስፈርት በማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ዋና አማካሪ ስም--------------------------------------ፊርማ-----------

ረዳት አማካሪ ስም-------------------------------------ፊርማ-----------

የዉጭ ፈታኝ ስም-------------------------------------ፊርማ------------

የዉስጥ ፈታኝ ስም----------------------------------  ፊርማ------------

## የአማካሪዎች ይሁንታ

ተማሪ ፈለቀች እሸቱ ኃይሌ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ ተማሪ ስትሆን መመረቂያ ስራዋን ከአማካሪዎቿ ጋር በትብብር እየሰራች የቆየች በመሆኗ ለተቋቁሞ መቅረብ የምትችል መሆኗን እናረጋግጣለን።

ዋና አማካሪ ስም------------------------------------ፊርማ-----------

ረዳት አማካሪ ስም---------------------------------ፊርማ------------

## የአጥኝዋ ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተቀመጠዉ ይህ ጥናት የግል ስራዬ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡የሌላ ሰዉ ስራዎችን ሳያመሰግኑ ወስዶ መጠቀም በዩኒቨርሲቲዉ ህግ መሰረት እንደሚያስቀጣና የአዕምሮ ሌብነት መሆኑን አዉቃለሁ፡፡ስለዚህ የተጠቀምኳቸዉን ስራዎች በሙሉ በዋቢ መጻህፍት ስር ዋጋ ሰጥቻቸዋለሁ፡፡

የአጥኝዋ ስም ፈለቀች እሸቱ

ፊርማ---------

## ምስጋና

ይህ ጥናት ይሳካ ዘንድ ዉድ ጊዜያቸዉን በመስዋት ገንቢ አስተያየት በመስጠትና አካሄዱን በማስተካከል ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ ለዋና አማካሪዬ በቃሉ ፈረደ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) እና ለረዳት አማካሪዬ ለመምህር ሃብታሙ እንግዳዉ ምስጋናዬ ከልብ ነዉ፡፡በመቀጠል ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መጻሕፍት በማዋስ ለተባበሩኝ ለመምህር አክሊሉ አየለ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ መረጃዎችን በመስጠት ለተባበሩኝ ለዮክጭጨ፣ጫሻና ጌጫ የ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

በመጨረሻም የድህረ ምረቃ ትምህርቴን እንድከታተል ላበረታታህኝና ልጄን በመንከባከብ ድጋፍህ ላልተለየኝ ባለቤቴ መስፍን መኮንንና ልጄ ህጻን መክሊት መስፍን ምስጋናዬ የበዛ ነዉ፡፡መረጃዎችን በመላክና ልምድህን በማካፈል ከጎኔ ሆነህ ላገዝከኝ ዉድ ለሆንከዉ ወንድሜ ጌትነት እሸቱ አክብሮቴ ላቅ ያለ ነዉ፡፡

# አጠቃሎ

*በዚህ ጥናት በደቡብ ክልል ስራ ላይ ባሉ  በ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል ተገምግሟል፡፡የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ገላጭ የምርምር ንድፍ የተመረጠ ሲሆን የተገኙት መረጃዎች  በዓይነታዊ የምርምር ዘዴዎች ተተንትነዋል፡፡በጥናቱ ሰነድ ፍተሻና ቃለመጠይቅ ጥቅም ላይ የዋሉ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ናቸዉ፡፡ጥናቱን ለማካሄድ በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶችን ለይቶ በማዉጣት በክለሳ ድርሳን ክፍል የቀረቡትን Larsen Freeman(1991)፣ Harmer(1991) እና Ur(1996)የሚያራምዷቸዉን ንድፈ ሀሳባዊ መሰረቶችን በመመርኮዝ ትንተና ተሰጥቶባቸዋል፡፡በጥናቱ የተገኘዉ ዉጤት እንደሚያመለክተዉ የይዘቶች አቀራረብን በተመለከተ በታላሚዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ስልት ያልተካተተ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ዉጤት ተኮር በሆነ ስልት የቀረቡት ይዘቶች ሂደት ተኮር በሆነ ስልት ከቀረቡት ይዘቶች አብላጫዉን እንደሚይዙ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ከአደረጃጀት አንጻር ደግሞ አብዛኛዎቹ ሰዋስዋዊ መልመጃዎች በተለያዩ ምዕራፎች እየተደጋገሙ መቅረባቸዉን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ነገር ግን በርካታ ይዘቶች ስፋትና ጥልቀታቸዉን ሳይጨምሩ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ተደራጅተዉ መቅረባቸዉን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ይሁን እንጂ በተተኳሪዎቹ መጻሕፍት ዉስጥ የተካተቱት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት መርሆዎች አኳያ ሲፈተሹ ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ በምሳሌዎች እየታገዙ መቅረባቸዉና በተለያዩ ምዕራፎችና ክፍሎች እየተከታተሉ መደራጀታቸዉ ከጠንካራ ጎናቸዉ መካከል የሚጠቀስ ሲሆን አብዛኛዎቹ ይዘቶች ደግሞ ጥልቀታቸዉን ሳይጨምሩ መደራጀታቸዉ እንደ ደካማ ጎን ታይተዋል፡፡ በመሆኑም የታዩት ደካማ ጎኖች ወደፊት መጻሕፍቱ በሚሻሻሉበት ወቅት እንዳይደገሙና ጥንቃቄ እንዲደረግ አጥኚዋ ለመጠቆም ትወዳለች፡፡*

# የይዘት ማዉጫ

**ይዘት** **ገጽ**

ምስጋና ....... i
አጠቃሎ ....... ii
የይዘት ማዉጫ ....... iii
ሠንጠረዥ ማዉጫ ....... v
ምዕራፍ አንድ:- መግቢያ ....... 1
1.1.የጥናቱ ዳራ ....... 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ....... 3
1.3. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ....... 4
1.4. የጥናቱ ዓላማዎች ....... 5
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ....... 5
1.6. የጥናቱ ወሰን ....... 6
1.7. የጥናቱ ዉስንነት ....... 6
ምዕራፍ ሁለት:-ክለሳ ድርሳናት ....... 7
2.1 ንድፈሐሳባዊ ዳሰሳ ....... 7
2.1.1 የሰዋስው ምንነት ....... 7
2.1.2 የሰዋሰው ትምህርት አስፈላጊነት ....... 8
2.1.3 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ....... 10
2.1.3.1. የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ....... 10
2.1.3.1.1. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ....... 11
2.1.3.1.2. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ ....... 11
2.1.3.1.3. ውጤት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ....... 12
2.1.3.1.4. ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ....... 12
2.1.3.2. የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ....... 13
2.1.3.2.1 ተከታታይነት ....... 13
2.1.3.2.2 ተለጣጣቂነት ....... 14
2.1.4. የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ምንነት ....... 14
2.2. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ....... 15
ምዕራፍ ሦስት፡- የአጠናን ዘዴ ....... 18
3.1. የጥናቱ ንድፍ ....... 18

3.2.2 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ ........ 18
3.2.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ........ 19
3.3.የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 20
3.3.1.ሰነድ ፍተሻ ........ 20
3.3.2 ቃለ -መጠይቅ ........ 20
3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 21
ምዕራፍ አራት:- የጥናት ዉጤት ትንተናና ማብራሪያ ........ 22
4.1 የጥናት ዉጤት ትንተና ........ 22
4.1.1 የመማሪያ መጻሕፍቱ አጠቃላይ ቅኝት ........ 22
4.1.1.1 የ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አጠቃላይ ቅኝት ........ 22
4.1.1.2 የ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ አጠቃላይ ቅኝት ........ 24
4.1.2 በመማሪያ መጻሕፍቱ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ........ 25
4.1.2.1 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ........ 25
4.1.2.1.1 የ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ........ 25
4.1.2.2 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ ........ 27
4.1.2.2.1 የ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ........ 27
4.1 2.2.2 የ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ........ 30
4.1.2.3.1 የ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ........ 33
4.1.2.3.2 የ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ........ 35
4.1.2.4 ሂደት ተኮር አቀራረብ ........ 37
4.1.2.4.1 የ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ........ 37
4.1.2.4.2 የ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ........ 39
4.1.3 በመማሪያ መጽሀፍት ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ........ 41
4.1.3.1.3 በ5ኛ እና በ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት መካከል ያለዉ የሰዋስዉ ትምህርት የይዘቶች ተከታታይነት ........ 55
4.1.3.2.1 የ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ........ 57
4.1.3.2.2 የ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ........ 65
4.1.3.2.3.በ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት መካከል ያለዉ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ተለጣጣቂነት ........ 72
ምዕራፍ አምስት: ማጠቃለያ መደምደሚያና የመፍትሄ ሃሳብ ........ 82
5.1 ማጠቃለያ ........ 82
5.2 መደምደሚያ ........ 83
5.3 የመፍትሄ ሃሳቦች ........ 84
ዋቢ መጻሕፍት ........ 86

## ሠንጠረዥ ማዉጫ

ሰንጠረዥ 3.1. በናሙናነት በተመረጡ ትምህርት ቤቶች በ5ኛና 6ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩና ለጥናቱ የተመረጡ መምህራን አጠቃላይ ዳራ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 20

ሰንጠረዥ.4.1 የ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አጠቃላይ ቅኝት የሚያሳይ ሰንጠረዥ .. 23

ሰንጠረዥ.4.2 የ6ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አጠቃላይ ቅኝት የሚሳይ ሰንጠረዥ ........ 24

ሰንጠረዥ 4.3 በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የክትትሎሽ ሁኔታ ........ 41

ሰንጠረዥ 4.4 በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች የድግግሞሽ መጠን ........ 48

ሰንጠረዥ 4.5 በ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍት መካከል ተከታታይነት አግኝተዉ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ........ 55

# ምዕራፍ አንድ:- መግቢያ

## 1.1.የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት ዋነኛ ዓላማ የተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎት ማጎልበት እና የስነ-ጽሑፍና የስነ-ልሳን (ሰዋስው) እውቀትን ማሳደግ ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት በየደረጃው በሚዘጋጁ የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተለያዩ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ተካትተው ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም ይዘቶች መካከል የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ይጠቀሳሉ፡፡

የሰዋስዉ ምንነትን አስመልክተዉ ባየ (2000፣xxi) ‹‹ሰዋስዉ የአንድን ቋዋንቋዋ ስርዓት ከድምጽ አሰካኩ እስከ ሀረግ አመሰራረቱ ድረስ የሚያሳይ ሳይንስ ነዉ›› በማለት ገልጸዋል፡፡ Batstone (1994፣1-4) ደግሞ ‹‹ሰዋስዉ እለት ተእለት ለተግባቦት ከምንገለገልበት ቋንቋ ጋር የተጣመረ የቋንቋ አካል ነዉ›› ይሉታል፡፡ከእነዚህ ገለጻዎች መረዳት እንደሚቻለዉ ሰዋስዉ በየእለቱ ከምናካሂደዉ ተግባቦት ተነጥሎ የማይታይ የቋንቋ ስርዓት መሆኑን ነዉ፡፡

Batstone (1994) የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊነትን አስመልክተው በቋንቋ አጠቃቀም ሂደት ሰዋስዋዊ ችሎታ ከሌለን በቋንቋው ሀሳባችንን ለመግለጽ አስቸጋሪ እንደሚሆን ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም Ellis (2000) ይህንን ሀሳብ በመደገፍ የሰዋስው ትምህርት ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ባህሪያት በሚገባ ተረድተው በተግባቦት ሂደት ጥቅም ላይ የሚያውሉበትን ስርዓት የሚያሳይ እንደመሆኑ ሰዋስውና ተግባቦት ተነጣጥለው መታየት እንደሌለባቸው ይገልጻሉ፡፡Michal (2007) ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ የተማሪዎችን የንግግርም ሆነ የጽሁፍ ክሂሎች ከሰዋስዉ እዉቀት ጋር በማጣመር የቋንቋ ደረጃቸዉን ከግምት ዉስጥ ያስገባ የትምህርት አቀራረብ የሚያስፈልግ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ከላይ የቀረቡትን ሀሳቦች ስንመለከት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ መዋቅራዊ ስርዓት ተረድተው ቋንቋውን ለተግባቦት የሚያውሉበትን መንገድ የሚያመቻች ዘመናዊ የቋንቋ ትምህርት እሳቤ ሲሆን በክፍል ዉስጥ መማር ማስተማር ወቅት ተማሪዎች በቋንቋ እንዲገለገሉበት ክህልን ከሰዋስዉ ይዘት ጋር አዋህዶ ማቅረብ በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ነዉ፡፡

ዘመናዊ የሰዋስው ትምህርት እሳቤ ሰዋስዋዊ ቅርጾችን ወይም መዋቅር ፍቺና አጠቃቀም ላይ መሆን እንደሚገባው Cook (2001) ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም LarsenFreeman (1991፣280) «የሰዋስው ትምህርት ተማሪዎች የቋንቋውን ስርዓት ትርጉም ባለው መንገድ ጠንቅቀው

አውቀው በትክክለኛው መንገድ እንዲገለገሉበት ማስቻል አለበት፡፡ ይህንን ዓላማ ከግብ ማድረስ ይቻል ዘንድ ትምህርቱ የቋንቋውን ቅርጽ፣ ፍቺና አገባብ ማካተት ይኖርበታል» በማለት ያስረዳሉ፡፡ከእነዚህ ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው የሰዋስው ትምህርት ሁሉንም የቋንቋ ገጽታ ማለትም ቅርጽን ፍቺንና አገባብን ማዕከል ያደረገ መሆን እንዳለበት ነው፡፡

ስነትምህርታዊ ሰዋስው ወቅታዊና የተሻሻሉ የቋንቋ ማስተማር፣ የይዘት አቀራረብና አደረጃጀት የመሳሰሉትን ጉዳዮች ከግምት በማስገባት የሚዘጋጅ መሆኑን Bygate et.al. (1994) ይገልጻሉ፡፡ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ በተለያዩ የመስኩ ባለሙያዎች ዘንድ ተቀራራቢነት ባላቸው ጽንሰ ሀሳቦች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ሆኖ እናገኛቸዋለን፡፡ እንደ Bygate et.al. (1994፣22) ፤CunningsWorth (1995፣99)፣ LarsenFreeman (1991 ፣ 292) ፤ Harmer (1991 ፣ 18) አባባል የሰዋስው ትምህርት ውጤት ተኮር፣ ሂደት ተኮር፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆኑ መንገዶች እንደሚቀርቡ ገልጸዋል፡፡

አደረጃጀት ስንል ደግሞ በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚቀርቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች እንዴት ባለ ቅደም ተከተል መቅረብ እንዳለባቸው የሚያመለክት ሲሆን በተጨማሪም የትምህርት ይዘቶች ቅንጅታዊ ውጤት ያስገኙ ዘንድ እርስ በራሳቸው ተደጋግፈው ሊደራጁ የሚገባ መሆናቸውን እና አደረጃጀታቸውም ተዋረዳዊና ጎናዊ ግንኙነትን የጠበቀ መሆን እንደሚገባው CunningsWorth (1995) ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ ሰዋስው የአንድን ቋንቋ ስርዓት ይመለከታል ሲባል ስነ ድምጽን፣ ስነ-ምእላድን፣ስነ-አገባብና ፍቺን አስመልክቶ ትክክለኛ ሳይንሳዊና ተቀባይነት ያለውን የቋንቋ አጠቃቀም የሚተነትን መሆኑን ነው፡፡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ውጤታዊ ይሆኑ ዘንድ የቋንቋውን ቅርጽ፣ ፍቺና አጠቃቀም አንድ ላይ አስተሳስረው መቅረብ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም አደረጃጀታቸው ተከታታይነትን የጠበቁ ሆነዉ ስፋትና ጥልቀታቸዉን እየጨመሩ የሚሄዱ መሆናቸዉን መረዳት ይቻላል፡፡

የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ለመማር ማስተማር ዓላማ ተነድፈው ከሚቀርቡባቸው ማስተማሪያ መሳሪያዎች ውስጥ የተማሪዎች መማሪያ መጻሕፍት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚካተቱ ይዘቶች የታቀደላቸውን ዓላማ ይመቱ ዘንድ በዝግጅት ወቅትም ይሁን በስራ ላይ ከዋሉ በኋላ ተከታታይ ግምገማ ወይም ፍተሻ ሊደረግባቸውና ከዚያም

በሚገኙ ምላሾች ሊሻሻሉ እንደሚገባቸው Stern (1992) እና CunningnsWorth (1995) ይገልጻሉ፡፡

በኢትዮጵያ አዲሱ የትምህርት ስልጠና ፖሊሲ መተግበር ከተጀመረበት ከሁለት አስርት ዓመታት ወዲህ የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት በክልል ደረጃ እንዲዘጋጁ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የ5ኛ እና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ይገኙበታል፡፡ይህ ጥናት አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር በደቡብ ክልል ስራ ላይ ባሉ የ5ኛ እና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ከስነትምህርታዊ ሰዋስው መርሆዎች አንጻር ገምግሟል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

አጥኚዋ ይህንን ጥናት ለማካሄድ ካነሳሷት ምክንያቶች መካከል የተለያዩ ምሁራን የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት በየጊዜው መገምገም እንዳለባቸው እና ከችግሮች እንዳልጸዱ የሚያቀርቡት ሀሳብ ተጠቃሽ ነው፡፡

Donough and Show (1995) ግምገማ የሚያስፈልገው ስራ ላይ ያሉ መጻሕፍትን ጠንካራና ደካማ ጎኖቻቸውን ለመለየት ሲሆን አዲስ የሚዘጋጁትን መጻሕፍት ደግሞ ተገቢነታቸውን ለማረጋገጥ ነው ይላሉ፡፡ Grant (1988) ደግሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች የተካተቱባቸውን የመማሪያ መጻሕፍት ትኩረት ሰጥቶ የመገምገምን ተገቢነት ሲያስረዱ «ምንም አይነት ችግር የሌለባቸው የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት አዘጋጅቶ ማቅረብ አይቻልም» ይላሉ፡፡ **ከነዚህ ምሁራን ሀሳብ** መረዳት እንደምንችለው መማሪያ መጻሕፍት በየጊዜው እየተገመገሙ መሻሻል እንዳለባቸው የሚጠቁም በመሆኑ ይህንን ጥናት ለማካሄድ አነሳሽ ምክንያት ሆኗል፡፡

ሌላው አጥኚዋ በተተኳሪዎቹ የክፍል ደረጃዎች ለሁለት ዓመታት ያህል በማስተማር ቆይታለች፡፡ በማስተማር ሂደቱም በነዚህ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከአቀራረብ አንጻር የተወሰኑ ክፍተቶችን አጥኚዋ ማስተዋሏ ይህንን በጥናት ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑ የጥናቱ ሌላዉ አነሳሽ ምክንያት ነዉ፡፡

በተጨማሪም ሰሚራ (2010) ባካሄዱት ጥናት በ2009 ዓመተ ምህረት በደቡብ ክልል ስራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘቶች

አቀራረብና አደረጃጀት ላይ ከአቀራረብ አንጻር ውጤት ተኮር እና ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልቶች ተመጣጣኝ ሆነው ያልቀረቡ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ኢያሱ (2003) ባደረጉት ጥናት በሀገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅተው በስራ ላይ ያሉ የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጻሕፍት ውስጥ አብዛኛዎቹ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከቋንቋ ሰዋስዋዊ ክፍሎች ያልተመጣጠኑ መሆናቸውን በጥናታቸው አመልክተዋል።

እስሌማን (2003) እንደዚሁ በ12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ ከስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው አንጻር በሚል ርዕስ ጥናት አካሄደዋል። በውጤታቸዉም ይዘቶቹ የታላሚውን ቋንቋ ቅርጽ የሚተነትኑ እንጂ ለፍቺና አጠቃቀም ትኩረት የማይሰጡ መሆናቸውን ጠቁመዋል። በአጠቃላይ ከተዘረዘሩት ጥናቶች ከተገኙት ዉጤቶች መረዳት እንደሚቻለዉ በ8ኛ፣9ኛ፣10ኛ እና 12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከአቀራረብና አደረጃጀት አንጻር ክፍተት የሚታይባቸዉ መሆኑን ማስተዋል ተችሏል።በመሆኑም በተተኳሪዎቹ 5ኛና 6ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከአቀራረብና አደረጃጀት መርሆዎች አንጻር የተሰጣቸዉ ትኩረት ምን እንደሚመስል በጥናት ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑ የጥናቱ ሌላዉ አነሳሽ ምክንያት ነዉ።

## 1.3. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

የጥናቱ ዋና ዓላማ በደቡብ ክልል ሥራ ላይ ባሉ የ5ኛ እና የ6ኛ ክፍል የመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ምን ይመስላል? የሚለውን የሚመልስ ነው።

ከዚህ አጠቃላይ ጥያቄ መነሻነት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል፦

- በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ተመርጠው የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከአቀራረባቸው አንጻር ለቋንቋው ቅርጽ፣ ፍቺና አጠቃቀም የሰጡት ትኩረት ምን ይመስላል?
- በ5ኛና 6ኛ ክፍል የመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከአደረጃጀት አንጻር የይዘቶቹ ተከታታይነት ምን ይመስላል?
- በታላሚዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከአደረጃጀት አንጻር የይዘቶቹ ተለጣጣቂነት ምን ገጽታ አለው?

## 1.4. የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደቡብ ክልል ስራ ላይ ባሉ የ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል መገምገም ነው።

በዚህ መነሻነት ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡-

- በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከአቀራረብ አንጻር ለቋንቋው ቅርጽ፣ ፍቺና አጠቃቀም የተሰጡትን ትኩረት መፈተሽ፤
- በ5ኛና 6ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ከይዘቶች ተከታታይነት አንጻር መመርመር፤
- በታላሚዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ከይዘቶች ተላጣጣቂነት አንጻር መገምገም ፤

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

የመማሪያ መጻሕፍት በዝግጅት ወቅትም ይሁን ስራ ላይ ሲውሉ ግምገማ ማካሄድ በርካታ ጠቀሜታዎች  አሉት። በመሆኑም ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል።

- ለስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች በ5ኛና 6ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን በሚያዘጋጁበትና በሚያሻሽሉበት ሂደት ሊገለገሉባቸው የሚችሉ ግብዓቶችን ሊጠቁም ይችላል።
- ለተመራማሪዎች በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀትን ፈትሾ ምን ገጽታ እንዳለው በመጠቆም በመስኩ ለሚደረግ ቀጣይ ጥናት የበኩሉን አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችላል።
- የቋንቋ መምህራን የሚያስተምሩባቸው መጻሕፍት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ቅርጽን፣ ፍቺና አጠቃቀምን አካትተዉ እንዲሁም ተከታትለውና ተደጋግፈው መቅረብ እንዳለባቸው ለመገምገም የሚያስችላቸውን መነሻ ሀሳብ ሊያገኙበት ይችላሉ።

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በደቡብ ክልል ስራ ላይ በዋሉ የ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀትን መገምገም ነው፡፡በመማሪያ መጻሕፍቱ  ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች በርካታ ሲሆኑ የሁሉንም ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት አይመለከትም፡፡በመሆኑም ይህ ጥናት የሚያተኩረው የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ላይ ሲሆን ከ2009 ዓመተ ምህረት ወዲህ በስራ ላይ ያሉትን መማሪያ መጻሕፍት ብቻ የሚፈትሽ ነው፡፡ከተተኳሪዎቹ ክፍል በላይም ሆነ በታች ያሉትን መማሪያ መጻሕፍትም ሆነ አስቀድመው ስራ ላይ ውለው የነበሩትን የመማሪያ መጻሕፍት አያካትትም፡፡በተጨማሪም ከተተኳሪው ክልል ውጪ  ሌሎች ክልሎች የሚገለገሉባቸዉን 5ኛና 6ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት አይመለከትም፡፡

## 1.7. የጥናቱ ዉስንነት

ይህ ጥናት በሚካሄድበት ወቅት ካጋጠሙት ችግሮች መካከል መረጃ ሰጪዎችን በታቀደዉ ጊዜ መሰረት  ማግኘት አለመቻል ነዉ፡፡ ምክንያቱም በ2012 ዓመተ ምህረት በተከሰተዉ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ትምህርት ቤቶች ተዘግተዉ መቆየታቸዉ ይታወሳል፡፡በተጨማሪም በ2013 ዓመተ ምህረት ዘግይተዉ በመከፈታቸዉ የተነሳ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ከፍተኛ ጫናን አስከትሏል፡፡በመሆኑም ካለዉ የጊዜ ጥበት አኳያ በናሙናነት ከተመረጡ ተማሪዎችና መምህራን መረጃዎችን በታቀደዉ ጊዜ ማግኘት አልተቻለም፡፡ይሁን እንጂ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ከተማሪዎችም ሆነ ከመምህራን ፍቃደኝነታቸዉን በማግኘት በዕረፍት ቀናቸዉ መረጃዎችን እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት:-ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 ንድፈሐሳባዊ ዳሰሳ

### 2.1.1 የሰዋስው ምንነት

ጌታሁን (1989) እና LarsenFreeman (1991) ሰዋስው ከስነ ድምጽ እስከ ዓረፍተ ነገር መዋቅር ድረስ ያለውን የቋንቋ ሥርዓት ያጠናል ሲባል ከቋንቋ ላዕላይ ቅርጽ በተጨማሪ በተናጋሪው አዕምሮ ውስጥ ያለውንና የቋንቋ እውቀት ጭምር እንደሚያካትት ያስገነዝባሉ፡፡ Brown (2000) "ሰዋስው ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ በስርዓት ተቀናጅተው የሚፈጥሩትና ያላቸውን ግንኙነት የሚመለከት የቋንቋ ስርዓትና ህግ ነው» በማለት ይገልጻሉ፡፡ Hdfield (2008) "ሰዋስው ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ የሚኖራቸውን ቅደም ተከተላዊ አደራደር፣ አወቃቀርና አደረጃጀት እንዲሁም ቅርጻቸውን በመለወጥ እንዴት ትርጉም ሊያስገኙ እንደሚችሉ የሚገልጽ ስርኣት ነው"ይላሉ፡፡

ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ሰዋስው ከድምጽ አንስቶ እስከ ዓረፍተ ነገር ድረስ ያለውን መዋቅር የሚመለከት ሳይንስ ሲሆን ሃሳብን በጽሑፍ ወይም በንግግር ስኬታማ በሆነ መልኩ ለማስተላለፍ የሚረዳ የቋንቋ ስርዓት መሆኑን ነዉ፡፡

በቀደምት የቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ የቋንቋ ትምህርት ዓላማ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ቅርጾችንና ህግጋትን በማቅረብ ተማሪዎች በደንብ እንዲያጠኗቸውና እንዲያከናውኗቸው ማስቻል ነበር፡፡ለዚህም በምሳሌነት ሰዋስው ው-ትርጉም ዘዴ ተጠቃሽ ነው፡፡Stern (1992) እና LarsenFreeman (1986) በሰዋስው ው-ትርጉም ዘዴ የታላሚው ቋንቋ ትምህርት የሚሰጠው በተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሲሆን ዋነኛ ትኩረቱም የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ቅርጾችና ህግጋት ማቅረብ ነበር በማለት ይገልጻሉ፡፡በዘመናዊ የቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ ግን የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ቅርጾችንና ህግጋትን ብቻ ማስተማሩ ተቀባይነት የለውም፡፡ እንደ Larsen Freeman(1986) እና CunningsWorth (1995) ገለጻ የሰዋስው ትምህርት ትኩረት የቋንቋ ቅርጽ ወይም መዋቅር ፍቺና አጠቃቀም መሆን አለበት፡፡Ur (1988) በበኩላቸው የታላሚውን ቋንቋ የተለያዩ ክፍሎች ወይም አካላት ቅርፅ ፍቺና አውዳዊ አጠቃቀም በተመጣጠነ መልኩ ማስተማር እንደሚገባ ይገልጻሉ፡፡Harmer (1987) የሰዋስው ትምህርት ትኩረት በሰዋስዋዊ ቅርፆች ወይም መዋቅሮች ላይ ብቻ ማነጣጠር እንደሌለበት ያስረዳሉ፡፡

ምሁራኑ ካቀረቡት ገለፃ መረዳት እንደሚቻለው የሰዋስው ትምህርት ትኩረቱ በቋንቋ ሰዋስዋዊ ቅርፆች ወይም መዋቅሮች፣ በፍቺና በአጠቃቀም ወይም በአገልግሎት ላይ መሆኑን ነዉ።ይህም ማለት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ በሚካተቱበት ወቅት ወጥ ሆነዉ መቅረብ የሌለባቸዉ በመሆኑ ሁሉንም የቋንቋዉን ክፍሎች በተመጣጠነ መልኩ ማቅረብ መቻል አለባቸዉ።

ሰዋስዉ በርካታ ዘርፎች ያሉት ሲሆን በመደበኛው የቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከቋንቋ የክሂል ትምህርት ጋር ቀጥተኛ ተዛማጅነት ያለው ሥነ-ትምህርታዊ ሰዋስው መሆኑን የመስኩ ባለሙያዎች ይናገራሉ። Odlin (1994) ሥነ-ትምህርታዊ ሰዋስው የተለያዩ የሰዋስው ዓይነቶች ጥምረት የሚታይበት መሆኑን በመግለጽ አዛዥ፣አዕምሮታዊ፣ስነ-ልሳናዊ እና ገላጭ ሰዋስው እንደሚገኙባቸው ያስረዳሉ።Direven (1990) Chalker (1991) ሥነ-ትምህርታዊ ሰዋስው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ትምህርቱን ውጤታማ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪም ሆነ ለመምህሩ የሚያገለግል መሆኑን ጠቁመው ገላጭ፣አዛዥ፣የማስተማሪያ ወይም የማጣቀሻ ሰዋስው ዓይነቶችን ሁሉ እንደሚያቅፍ አመልክተዋል።Bygate et.al. (1994) ስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት ላይ በማተኮር ልምምዶችን እንደሚያደርጉና በተግባራዊ ግልጋሎትም ወቅት እንደሚጠቀሙበት የሚያግዝ ነው በማለት ያስረዳሉ።

ከላይ ከቀረቡት ገለፃዎች መረዳት እንደሚቻለው ሰዋስው የተለያዩ ዘርፎች ያሉት ሲሆን ቋንቋን በክፍል ውስጥ ከመማር ማስተማር ሂደት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው ነዉ። ይህ የሰዋስዉ ዘርፍ ተማሪዎች በክፍል ዉስጥ ብቻ ሳይሆን ከክፍል ዉጭም በቋንቋዉ ተግባቦትን ለመፍጠር የሚያስችላቸዉን ስርዓት የሚያሳዉቅ መሆኑን ነዉ።

### 2.1.2 የሰዋሰው ትምህርት አስፈላጊነት

ከ1960ዎቹ ወዲህ የቋንቋ ትምህርት ሰዋስው ላይ ማተኮር የለበትም በሚል አዳዲስ የማስተማር ስነ-ዘዴዎች ብቅ ብቅ ማለት የጀመሩበት ዘመን ነበር። የነዚህ ስነ-ዘዴዎች ፍልስፍና የቋንቋ ትምህርት በሰዋስው ላይ ትኩረት ከማድረግ ይልቅ ተማሪዎች ተግባቦታዊ ብቃታቸውን ሊያዳብሩ ከሚችሉባቸው ተግባራዊ ክንውኖች ላይ ማተኮር አለበት የሚል ነው። እነዚህ ስነ-ዘዴዎች የቋንቋ ትምህርት የሰዋስው ትክክለኛነት አያስፈልገውም። በሚል ተማሪዎች እውናዊ ተግባቦትን በክፍል ውስጥ መጠቀም የሚያስችሏቸውን ግብአቶች ወይም

አውዶች ሊቀርቡላቸው ይገባል ከሚሉ የቋንቋ ምሁራን ከሚያራምዱት ፍልስፍና የተገኘ እንደሆኑ ይታመናል (Bygate et.al.፣1994፣ LarsenFreeman፣ 1991)::

በሌላ በኩል Ur (1988) የተግባቦት ብቃት ያለሰዋስው እውቀት እውን ይሆናል ተብሎ ስለማይታሰብ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚተገብሯቸውን ክንውኖች በሙሉ ከሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ጋር ተሳስረው ቢቀርቡ የታቀደውን የትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ ጠቀሜታ አለው በማለት የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊነትን ያስረዳሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ Michal(2007) ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎችን የንግግርም ሆነ የጽሑፍ ክሂሎች ከሰዋስው እውቀት ጋር በማጣመር የቋንቋ ደረጃዎችን ከግምት ያስገባ የትምህርት አቀራረብ የሚያስፈልግ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ከላይ የቀረበውን ሀሳቦች ስንመለከት የቋንቋ ትምህርት ተግባቦት ላይ እንጂ ሰዋስው ላይ ማተኮር የለበትም፡፡ እንዲያውም የሰዋስው ትምህርት ለቋንቋ ትምህርት የሚሰጠው ፋይዳ የለም የሚሉ ወገኖች ባለፉት ዘመናት ሀሳባቸዉን ሲያራምዱ እንደነበረ ነዉ፡፡ ይህን አስተሳሰብ ስንመለከተው ድክመት የሚታይበት ነው፡፡ ምክንያቱም ሰዋስው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሚጫወተውን ሚና ዋጋ ያሳጣ ነው፡፡ ስለዚህ የቋንቋ ትምህርት የሰዋስው እውቀትንና ተግባቦትን ነጣጥሎ የሚመለከት ሳይሆን ሁለቱንም አስተሳስሮ የያዘ መሆኑን Ur(1988) ከሰጡት ብያኔዎች መረዳት ይቻላል፡፡በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ክህሎት በሚገባ ተግባራዊ ይደረጉ ዘንድ የቋንቋዉን ሰዋስዋዊ ስርዓት ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

Harmer(1991) የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊነትን ሲገልፁ ለተዋጣለት የቋንቋ አጠቃቀም የሰዋስው ዕውቀት በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ይህም ዕውቀት ለተማሪዎች በጣም አሰፈላጊ ነው ብለዋል፡፡ጌታሁን (1989) የቋንቋ ትምህርት ዓላማ በክህሎት ላይ ብቻ ሳይሆን በስርአትም ላይ መሆን አለበት፡፡ምክንያቱም ሁለቱም አንድን ቋንቋ ተማርኩ ከሚል ሰው የሚጠበቁ ችሎታዎች ናቸው፡፡ይህ ካልሆነ ደግሞ ተምሬያለሁ የሚለው ሰው ዕውቀት ቁንፅል ይሆናል በማለት ያስረዳሉ፡፡ሌለዉ CunningsWorth (1984) ሰዋስውን ያላካተተ የቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የተሟላ ነው ለማለት አያስደፍርም ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ባየ (2000) ደግሞ ከአንድ ቋንቋ ተማሪ የሚጠበቀው ችሎታ ሁሉን አቀፋዊ የክህሎትና የሥርዓት ቅንጅት መሆን እንዳለበት በመግለጽ የአንድን ቋንቋ አጠቃቀሙን ብቻ ካወቀ ተማሪ ይልቅ አጠቃቀሙን ማለትም ክህሎቱን ከነሥርዓቱ የተገነዘበ ተማሪ የበለጠ ዕውቀት ያለው መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ገለፃዎች እንደምንረዳው የክህሎት ትምህርት በሰዋስው ዕውቀት ተደግፎ ካልቀረበ ውጤታማ ተግባቦትን ማድረግ አይቻልም፡፡ተማሪዎች ከክፍል ዉጪ ለሚያደርጉት ተግባቦት የሰዋስዉ ትምህርት አስፈላጊ መሆኑን ነዉ፡፡በመሆኑም ትርጉም ያለዉ ተግባቦት ለማድረግ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የስነትምህርታዊ ሰዋስዉ መርሆዎችን ተከትለዉ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

Brown(1994) የቋንቋ ትምህርት የተማሪውን ክህሎት ከማዳበር ባሻገር ተማሪው ሊገነዘበው የሚገባውን ሰዋስዋዊ ዕውቀት ጭምር ማካተት ይኖርበታል፡፡ይህም የአፍ መፍቻ ቋንቋንም ሆነ ሁለተኛ ቋንቋን በማስተማር ወቅት ከተግባቦት በተጨማሪ የአጠቃቀም ስርዓቱን ማስተማር አስፈላጊ መሆኑን በመግለፅ የቋንቋ እውቀትና ችሎታ የሚለካው ተግባቦታዊ አገልግሎትን ከሥርዓቱ ጋር አቀናጅቶ በመገንዘብ በመሆኑ ሰዋስውን የማስተማር ተገቢነት መካድ የሌለበት መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ምሁራኑ ካቀረቡት ገለፃዎች መረዳት እንደሚቻለው በአንድ ቋንቋ አፈ-ፈት ለሆኑም ይሁን ለኢ-አፈ-ፈት ተማሪዎች ክህሎትና የቋንቋውን ሥርዓት ጠንቅቆ ማወቅ የሚጠበቁ ችሎታዎች መሆናቸዉን ነዉ፡፡

### 2.1.3 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት

#### 2.1.3.1. የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ

በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ሲቀርቡ የሚከተሏቸው አጠቃላይ ስነትምህርታዊ መርሆዎች አሏቸው፡፡እነዚህ መርሆዎችን በተመለከተ በባለሙያዎች ዘንድ በአብዛኛው ተቀራራቢነት ባላቸው ጽንሰ ሀሳቦች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በዚህም መሰረት እንደ Bygate et.al. (1994፣22) ፤CunningsWorth (1995፣99) ፤ LarsenFreeman (1991፣292) እና Harmer(1991፣18) አገላለጽ የሰዋስው ትምህርት ማቅረቢያ መንገዶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ውጤት ተኮርና፣ሂደት ተኮር መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡ Ur(1996) የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ በሚካተቱበት ጊዜ ሁሉንም የማቅረቢያ መንገዶች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ አካትቶ ማቅረቡ የተሻለ ዉጤት ያስገኛል በማለት ያስረዳሉ፡፡Harmer(1987)በክፍል ዉስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የተለያዩ እንደመሆናቸዉ መጠን የተለያየ የትምህርት አቀባበል ያላቸዉ ናቸዉ፡፡ይህ ብቻም ሳይሆን የተለያዩ የትምህርት ዓላማዎች የተለያዩ አቀራረቦችን የሚከተሉ በመሆናቸዉ ሁሉም የሰዋስዉ ትምህርት አቀራረቦች በመማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ

መካተት አለባቸዉ፡፡በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ውስጥም እነዚህ የማቅረቢያ መርሆዎች ተተኳሪ ሆነዋል፡፡

### 2.1.3.1.1. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ

CunningsWorth(1995፣99) «በዚህ ስልት የቋንቋው ዋና ዋና ህግጋት፣ደንቦችና ገለፃዎች ለተማሪዎች እየቀረቡላቸዉ እንዲያገኙ በተደረገው አጠቃላይ ዕውቀት ላይ በመመስረት ዝርዝር መልመጃዎችን በመስራት ትክክለኛውን የቋንቋ ሥርዓት እንዲያውቁ የሚያደርግ የአቀራረብ ስልት ነው» በማለት ይገልጹታል፡፡

ከላይ ከቀረበው ገለጻ መረዳት እንደሚቻለዉ በመማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ መርህን ተከትለዉ ሲቀርቡ የቋንቋዉን ህግጋት የሚያሳዩ ገለጻዎችን በመስጠት ተማሪዎች የቋንቋዉን ስርዓት እንዲለማመዱ በሚያስችል መልኩ መሆኑን ነዉ፡፡

### 2.1.3.1.2. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ

Cunningsworth(1995፣99) «በዚህ የአቀራረብ ስልት የታላሚውን ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለፃ አይቀርብም፡፡ በቅድሚያ ህግጋቱን ሊያሳዩ የሚችሉ ምሳሌዎች ለተማሪዎች ይቀርባሉ፡፡ ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ምሳሌዎች በደንብ በማጤን የቋንቋውን ህግጋት ምን ሊሆን እንደሚችል ይገምታሉ» በማለት ያስረዳሉ፡፡ Harmer (1997) እና LarsenFreeman (1991) ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአደረጃጀት ስልት ተማሪዎች ከቀረቡላቸው ዝርዝር ምሳሌዎች በመነሳት የቋንቋውን አጠቃላይ ህግጋት እንዲያወጡ የሚያበረታታ ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡ Woods(1995) ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ማቅረብ ሲባል በአግባቡ የተመረጡ ምሳሌዎችን በማቅረብ ተማሪዎች የቀረቡትን ምሳሌዎች መሰረት አድርገዉ የተሰጣቸዉን መልመጃዎች ከሰሩ በኃላ የቋንቋዉን ህግ በራሳቸዉ እንዲደርሱበት የሚያደርግ መርህ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ከላይ ከቀረቡት ብያኔዎች መረዳት እንደሚቻለው በዚህ የአቀራረብ ስልት ተማሪዎች ከቀረቡላቸው ዝርዝር ምሳሌዎች በመነሳት የቋንቋውን አጠቃላይ ህግ እንዲያወጡ የሚያስችል በመሆኑ የተማሪዎቹን ንቁ ተሳትፎ የሚፈልግ ነው፡፡ትኩረቱም ተማሪዎቹ ምሳሌዎችን መነሻ በማድረግ ቋንቋዉን ለመጠቀም የሚያስላቸውን ሰዋስዋዊ መረጃዎችን እንዲለዩ ማስቻል ነው፡፡በመሆኑም ይህን የአቀራረብ መርህ ተከትለዉ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጻህፍት ዉስጥ በሚካተቱበት ወቅት በቂ ምሳሌዎች መቅረብ እንዳለባቸዉ መገንዘብ ይቻላል፡፡በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የተለያዩ እንደመሆናቸዉ መጠን የተለያዩ

የትምህርት አቀባበል ስልቶችን ይከተላሉ፡፡ስለዚህ ሁለቱንም የአቀራረብ መርሆዎች በተገቢው ሁኔታ መጠቀም የሚያስፈልግ መሆኑን Harmer (1987) ያስረዳሉ፡፡

### 2.1.3.1.3. ውጤት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ

Batstone (1994፣51) «ይህ የአቀራረብ ስልት በታላሚው ቋንቋ መዋቅር ዙሪያ ባለው የቋንቋ ቅርጽ ላይ የሚያተኩር መሆኑን ይናገራሉ»ይህ ዘዴ ተማሪዎች በታላሚዉ ቋንቋ ስርዓት ላይ በማተኮር የቃላትና የዐረፍተ ነገር አመሰራረት እዉቀት እንዲኖራቸዉ የሚያደርግ ነዉ፡፡በቋንቋዉ መዋቅራዊ ስርዓት ትክክለኛነት ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ የሰዋስዉ አህዶችን ነጥሎ በመተንተን ተማሪዎች በቋንቋዉ ህግ ላይ ተመስርተዉ ትክክለኛ ዐረፍተነገሮችን እንዲያፈልቁ የሚያስችል መሆኑን Baygate.et,al(1994)ያስረዳሉ፡፡አቀራረብ ስልቱ ልማዳዊ የሆነ የሰዋስው ትምህርት የአቀራረብ መርህን የተከተለ፣በመጻህፍቱ ላይ የተመሰረተና በቋንቋ መዋቅራዊ ህግጋትና ብያኔዎች ላይ ያተኮረ በመሆኑ የሚተቹት ወገኖች ይበዛሉ፡፡

### 2.1.3.1.4. ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ

ሂደት ተኮር የሰዋስዉ ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች የታላሚዉን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት የሚያዉቁት በተለያዩ ተግባራዊ ልምምዶች ዉስጥ ማለፍ ሲችሉ እንደሆነ ያምናል፡፡በመሆኑም ለቋንቋዉ ቅርጽ ትኩረት ሰጥቶ በቀጥታ ከማስተማር ይልቅ ተማሪዎች ከሚፈጽሟቸዉ የተለያዩ ተግባራት ጀርባ የታላሚዉን ቋንቋ ስርዓት በሂደት ሊደርሱበት የሚችሉበትን የመማር ማስተማር ክንዋኔን ይከተላል፡፡ይህ አቀራረብ ዋና ትኩረቱን በመዋቅር ፍቺ ላይ ያደረገ በመሆኑ ተማሪዎች መልሶችን፣ክርክሮችን ወዘተ.እየፈጸሙ የቋንቋ ክህሎታቸዉን እንዲያዳብሩ የሚያደርግ መሆኑን Baygate.et.al(1994)ይገልጻሉ፡፡ዉጤት ተኮርና ሂደት ተኮር የሰዋስዉ ትምህርት አቀራረቦች የየራሳቸዉ ደካማና ጠንካራ ጎን ያላቸዉ ናቸዉ፡፡ዉጤት ተኮር የሰዋስዉ ትምህርት አቀራረብ የአንድን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት የሚያሳዉቅ ሲሆን ለመዋቅሩ ፍቺና አዉዳዊ አጠቃቀም የሚሰጠዉ ትኩረት አናሳ መሆኑ አቀራረቡን የተጓደለ ያደርገዋል፡፡ሂደት ተኮር የሰዋስዉ ትምህርት አቀራረብ ደግሞ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ የታላሚዉን ቋንቋ መዋቅራዊ ፍቺና አዉዳዊ አጠቃቀም ተገንዝበዉ በቋንቋዉ መገልገል እንዲችሉ ማድረጉ አዎንታዊ ገጽታዉን ቢያሳይም ሰዋስዉን በቀጥታ ማቅረብ ያለመቻሉ ደግሞ የድክመቱ መገለጫ እንደሆነ Batstone(1994)ይገልጻሉ፡፡

ከላይ የተመለከትናቸው ሁለት የአቀራረብ ስልቶች የራሳቸው የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎን ያሏቸው ናቸው፡፡እነዚህን ስልቶች አንዱ የሌላውን ክፍተት ሊሸፍን በሚችል መልኩ እያፈራረቁ

ወይም እያዋሀዱ መጠቀም ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ምሁራን ያስረዳሉ፡፡Batstone (1994) ከ1980ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ ሁለቱንም አቀራረቦች በማቀናጀት ማቅረቡ በስፋት እየተሰራበት መሆኑን በመጠቆም ይህም ቅንጅታዊ ስልት በተናጥል ሲሰራባቸው በነበሩት ውጤት ተኮርና ሂደት ተኮር አቀራረቦች ላይ የተመሰረተ ሆኖ የሰዋስው ትምህርት ለቅርጽም ሆነ ለአጠቃቀም ትኩረት መስጠት ያለበት መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

### 2.1.3.2. የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት

አደረጃጀት በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች በክፍል ደረጃዉ በተለያዩ ምዕራፎች እንዴት ባለ ቅደም ተከተል መቅረብ እንዳለባቸው ማለትም የትኛው ከየትኛው መቅደም እንዳለበት እና የትኛው መከተል እንዳለበት የሚያመለክት ሲሆን በቀጣዮቹም የክፍል ደረጃዎች ስፋትና ጥልቀታቸዉን እየጨመሩ መምጣት እንዳለባቸዉ የሚያመለክት መሆኑን Nunan (1988) ይገልጻሉ፡፡

Tayler (1949) እና Taba (1962) የትምህርት ይዘቶች ቅንጅታዊ ውጤት ማስገኘት ይችሉ ዘንድ እርስ በርሳቸው ተደጋግፈው ሊደራጁ ይገባል፡፡አደረጃጀታቸውም ተዋረዳዊና ጎናዊ ግንኙነት ሊኖረው ያስፈልጋል፡፡ተዋረዳዊ ግንኙነት በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች ግንኙነትን ያሳያል፡፡ጎናዊ ግንኙነት ደግሞ በተመሳሳይ የክፍል ደረጃዎች በተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶችን ግንኙነት ያሳያል፡፡በዚህ ጥናት ዉስጥ ተተኳሪ የሆነው የአደረጃጀት ስልት የይዘቶችን ተዋረዳዊ ግንኙነትን የሚያሳይ ሲሆን በዋናነት ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት የሚሉት የአደረጃጀት ስልቶች ናቸዉ፡፡

#### 2.1.3.2.1 ተከታታይነት

Tayler (1949፣84) «ተከታታይነት በአንድ የክፍል ደረጃ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በዛው የክፍል ደረጃ በተለያዩ ምዕራፎች ተደጋግመው መቅረባቸውንና በቀጣዮቹ የክፍል ደረጃዎች ሳይቆራረጡ እየተደጋገሙ መምጣትን የሚያመለክት ነው» በማለት ይገልጻሉ፡፡Larsen Freeman (1991) ተከታታይነት ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ይዘቱን በተለያዩ ምዕራፎችና በተለያዩ አውዶች ውስጥ ሊያገኙት ይገባል፡፡ይህም ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ይዘቱን በሚገባ እንዲረዱት፣ እንዲካኑትና በተገቢው ሁኔታ ለተግባቦት እንዲያውሉት ያስችላቸዋል፡፡ድግግሞሽ በተለይም ለሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ጠቀሜታ አለው፡፡ምክንያቱም ሰዋስዋዊ ቅርጾች ለተማሪው በቀላሉ ለመረዳት የሚያዳግቱ ሊሆኑ ይችላሉ በማለት ያስረዳሉ፡፡

ከላይ የቀረቡትን ብያኔዎች ስንመለከት ተከታታይነት በአንድ ምዕራፍ የቀረበ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘት በተከታታይ ሌሎች ምዕራፎች ዉስጥ እየተደጋገመ መምጣትን የሚመለከት ሲሆን በተጨማሪም በተከታታይ የክፍል ደረጃዎች የሚቀርቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በአንድ ክፍል ብቅ ብለዉ በቀጣዩ ክፍል የሚጠፉ መሆን እንደሌለባቸዉ የሚመለከት ነዉ፡፡

### 2.1.3.2.2 ተለጣጣቂነት

ተለጣጣቂነት በአንድ የክፍል ደረጃ ወይም በተከታታይ የክፍል ደረጃዎች የሚቀርብ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘት መጀመሪያ ከቀረበዉ የትምህርት ይዘት ተነስቶ ነገርግን ስፋትና ጥልቀት አግኝቶ መምጣትን የሚመለከት ነው በማለት Larsen (1991) ሲገልጹ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች እርስ በራሳቸዉ ተደጋግፈዉ በመሄድ የተማሪዉን የተግባቦት ደረጃ ለማሳደግ በመማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ ስፋትና ጥልቀት እያገኙ መሄድ አለባቸዉ፡፡ Nunan (1988) በበኩላቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ተለጣጣቂነት ባለው መልኩ ሳይቆራረጡ እርስ በርስ ተሳስረው መደራጀት እንዳለባቸው የሚያሳይ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

ከገለፃው መረዳት እንደሚቻለው ተለጣጣቂነት የትምህርት ይዘቶች ተደጋግመዉ መምጣት በመሆኑ ከተከታታይነት ጋር የሚመሳሰል ቢመስልም በመሀከላቸዉ ግን ልዩነት አለ ፡፡ይኸዉም ተለጣጣቂነት የትምህርት ይዘቶች ተደጋግመዉ መምጣት ብቻ ሳይሆን ተደጋግመዉ የሚመጡት የትምህርት ይዘቶች መጀመሪያ የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች መነሻ አድርገዉ ነገር ግን ስፋትና ጥልቀት ያላቸዉ ሆነዉ መምጣትን የሚያመለክት ነዉ እንጅ ያለፈዉን የሰዋስዉ ትምህርት ይዘት ቅጅ የሚያቀርብ ባለመሆኑ ተማሪዎች የሰፋና የጠለቀ ግንዛቤ እንዲጨብጡ የሚያሥችል የአደረጃጀት ስልት ነዉ፡፡

### 2.1.4. የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ምንነት

Grant (1988) መማሪያ መጽሐፍ የተደራጁ የትምህርት ይዘቶችን በውስጡ አቅፎ በመያዝ የትምህርት ዓላማዎችን ከግብ የሚያደርስ መሳሪያ ነው በማለት ይገልጹታል፡፡የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ማለት ተማሪው አስፈላጊውንና የታለመውን የቋንቋ ግብኣት እንዲያገኝ የሚያደርጉና ተማሪው በቋንቋ ትምህርቱ አማካይነት ያገኘውን ግብኣት እንዲለማመድ የሚያስችሉት እና ዕድሉን የሚያመቻቹለት ዋነኛ የትምህርት መሳሪያዎች መሆናቸዉን Richard (2001) ሲያስረዱ Good (1973) ደግሞ የመማሪያ መጻሕፍት ለአንድ ለተወሰነ የትምህርት ዓይነትና የክፍል ደረጃ የሚዘጋጁ ሥርዓታዊ የሆነ አደረጃጀት ያላቸውና በትምህርትነት ስለቀረበው የትምህርት ይዘት በምንጭነት የሚያገለግሉ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ናቸው ይሉታል፡፡

በአጠቃላይ የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ተማሪዎች መማር ያለባቸውን የትምህርት ይዘቶች፣መልመጃዎችንና ምሳሌዎችን አካትተው የሚይዙ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማቃናትና ለማገዝ የሚዘጋጁ፤በክፍል ውስጥ የሚተገበረውን የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ የመወሰን አቅም ያላቸው ሰነዶች መሆናቸውን ከላይ ከቀረበው ገለጻ መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.2. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር ከዚህ ጥናት ጋር ዝምድና ያላቸው ቀደምት ጥናታዊ ጽሑፎችን ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ከጥናታዊ ጽሑፉ ጋር ተዛማጅነት ካላቸው ጥናቶች መካከል የኢያሱ (2003) ጥናት ተጠቃሽ ነው፡፡ኢያሱ« በ1997 ዓመተ ምህረት በተሻሻሉት የ9ኛና 10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት የስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ይዘቶች አመራረጥ፣አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ» በሚል ጥናት አቅርበዋል፡፡ የኢያሱ ጥናት ዓላማ በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣አቀራረብና አደረጃጀት በመፈተሽ ያለውን ደካማና ጠንካራ ጎን መጠቆም ነው፡፡ጥናቱን ከዳር ለማድረስ ከጽሑፍና ከቃለ መጠይቅ በተጨማሪ የሰነድ ምርመራ በማድረግ ወደ ጥናቱ ማጠቃለያ ደርሰዋል፡፡በውጤቱም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከቋንቋው ሰዋስዋዊ ክፍሎች የተውጣጡ አለመሆናቸው እና የግልጽነት ችግር የሚስተዋልባቸው ከመሆናቸውም በተጨማሪ ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያልተዛመዱ መሆናቸውን በመጠቆም መፍትሔ የሚሏቸውን ሀሳቦች ሰንዝረዋል፡፡

ሐዋዝ ወልደየስ (2000) በበኩሉ«በአዲስ አበባ ከተማና በአማራ ክልል አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት ንጽጽራዊ ግምገማ» በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ድግሪ ያቀረቡት ጥናት ተጠቃሽ ነው፡፡

የጥናቱ ዓላማ የተጠቀሱት ሁለት ክልሎች በሚጠቀሙባቸው የ7ኛና 8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት በማነጻጸር ተመሳስሎና ልዩነታቸውን ነቅሶ ማውጣት ነው፡፡ጥናቱን ከድምዳሜ ለማድረስ የፅሁፍ መጠይቅ፣ቃለ መጠይቅና የሰነድ ምርመራ የተጠቀመ ሲሆን በውጤቱም ክልሎቹ መሠረት ያደረጉት አንድ ዓይነት መርሃ ትምህርት ቢሆንም በአቀራረብና በአደረጃጀታቸው መለያየታቸውን በጥናቱ ሂደት የተደረሰባቸው ግኝቶች መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

እስሌማን(2003) እንደዚሁ «በ12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ ከስነ ትምህርታዊ ሰዋስው አንጻር»በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዷል፡፡የጥናቱ ዓላማ በ1998 ዓመተ ምህረት ተሻሽሎ ሥራ ላይ በዋለው የ12ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አደረጃጀትና አቀራረብ ከሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው መርሆዎች አንጻር መገምገም የሚል ነው፡፡ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ ቃለመጠይቅ፣የጽሑፍ መጠይቅና የሰነድ ምርመራን በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት ተጠቅሟል፡፡ይዘቶቹ የታላሚውን ቋንቋ ቅርጽ የሚተነትኑ እንጂ ለፍቺና አጠቃቀም ትኩረት የማይሰጡ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

እምሻው ማሞ (2005) «ለ9ኛና ለ10ኛ ክፍል በተዘጋጁት (ከ1968-2004 ዓመተ ምህረት)የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ» በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ድግሪ ያቀረበው ጥናት ተጠቃሽ ነው፡፡የጥናቱ ዓላማ ከ1968 እስከ 2004 ዓመተ ምህረት አገልግሎት ላይ በነበሩት እና አሁንም ግልጋሎት እየሰጡ ባሉት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብን በመገምገም ያሳየውን ለውጥ መፈተሽ ነው፡፡ጥናቱን ለማካሄድ የሰነድ ምርመራን የተጠቀመ ሲሆን በውጤቱም በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ተመጣጥነው አለመቅረባቸውን በመጠቆም የመፍትሔ ሀሳብ የሚሏቸውን ሰንዝረዋል፡፡

ሰሚራ (2010)«በደቡብ ክልል በ2009 ዓመተ ምህረት ሥራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ» በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ድግሪ ያቀረቡት ጥናት ተጠቃሽ ነው፡፡የጥናቱ ዓላማ በደቡብ ክልል በ2009 ዓመተ ምህረት ሥራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘቶችን ከአቀራረብና ከአደረጃጀት መርሆዎች አንፃር መፈተሽ ነው፡፡ሰነድ ፍተሻን በመጠቀም ጥናቱን ያካሄዱ ሲሆን በውጤቱም ከአቀራረብ አንጻር ውጤት ተኮርና ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልቶች ተመጣጣኝ ሆነው ያልቀረቡ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡በተጨማሪም ከአደረጃጀት አንጻር ብዙዎቹ ድግግሞሽ የሚታይባቸው መሆናቸውንና የተወሰኑት ደግሞ አንድ ጊዜ ተከስተው የማይቀጥሉ መሆናቸውን በመግለጽ የመፍትሔ ሃሳብ ሰንዝረዋል፡፡

ይህ ጥናት ከኢያሱ ጥናት ጋር በክፍል ደረጃ፣በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ልዩነት ሲታይበት፣የሐዋዝ ጥናት ደግሞ ሁለት ክልሎችን በማነፃፀር ላይ ዓላማውን ያደረገ በመሆኑ

ልዩነት ይታይበታል፡፡ከእስሌማን ጥናት ጋር ይዞት ከተነሳው ዓላማ አንጻር ተመሳሳይነት ቢኖረውም ከተጠኝዎቹ የክፍል ደረጃ አንጻር ልዩነት ይታይባቸዋል፡፡የእምሻው ጥናት ከ1968-2004 ዓመተ ምህረት ባሉት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ያሳየውን ለውጥ የሚገመግም ሲሆን ይህ ጥናት ግን በአንድ ወቅት ታትመው ሥራ ላይ ያሉትን መጻሕፍት የሚፈትሽ በመሆኑ በእጅጉ ይለያል፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር ይበልጥ ተቀራራቢነት ያለዉ የሰሚራ ጥናት ነዉ፡፡ጥናቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብና አደረጃጀት የሚፈትሽ በመሆኑና ተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ከታተሙበት ዘመንና አገልግሎት ከሚሰጡበት ክልል አንጻር ተመሳሳይነት አላቸዉ፡፡ነገርግን ጥናቱ ከሚያተኩርባቸዉ የክፍል ደረጃዎች አኳያ ሲታይ ልዩነት አላቸዉ፡፡በተጨማሪም ሰሚራ ተጠኝዉ መጽሐፍና መረሃ ትምህርቱ ያላቸዉን ዝምድና የፈተሹ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ተተኳሪዎቹ መጻሕፍት ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያላቸዉን ዝምድና አይፈትሽም፡፡ከመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አንጻር ሰሚራ ሰነድ ፍተሻን ብቻ በመጠቀም መረጃዎችን የሰበሰቡ ሲሆን በዚህ ጥናት ግን ከሰነድ ፍተሻ በተጨማሪ የጽሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅን በመጠቀም መረጃ ተሰብስቧል፡፡የሰሚራ ጥናት ከሰዋስዉ ትምህርት አቀራረብ አንጻር ክፍተቶች አለመኖራቸዉን ጠቅሷል፡፡ነገር ግን ይህ ጥናት ትኩረት ባደረገባቸዉ የ5ኛና 6ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ከአቀራረብ አንጻር ችግሮች እንዳሉባቸዉ ጠቁሟል፡፡የሰሚራ የጥናት ዉጤት እንደሚያመለክተዉ የመማሪያ መጽሀፉ ከቀላል ወደ ከባድ የሚሄድ ፣ስፋትና ጥልቀቱን እየጨመረ የተደራጀ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ነገር ግን በዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆኑት መጻሕፍት ዉስጥ አብዛኛዎቹ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀታቸዉን ሳይጠብቁ የተደራጁ መሆናቸዉን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት፡- የአጠናን ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደቡብ ክልል ስራ ላይ ባሉ በ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ከሰዋስው ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት መርሆች አንጻር መገምገም ነው፡፡ በመሆኑም የጥናቱን ዓላማ መነሻ በማድረግ በተተኳሪዎቹ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብና አደረጃጀት በመፈተሽ ጥናቱ ላነሳቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች መልስ ሰጥቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ጥናቱ በአቀራረቡ ገላጭ የምርምር ንድፍን ተከትሏል፡፡ ጥናቱም ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡ መረጃዎችን በገለጻ ያቀረበ በመሆኑ ገላጭ የምርምር ንድፍ ጥቅም ላይ ዉሏል፡፡በተጨማሪም ጥናቱ መሰረት ያደረገዉ የአጠናን ዘዴ ዓይነታዊ ምርምር ነዉ፡፡ምክንያቱም ዓይነታዊ ምርምርን በመጠቀም ጥናቱ በሚዳስሳቸዉ የ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶችን ከአቀራረብ አንፃር ለቅርጽ፣ፍቺና አጠቃቀም የተሰጠዉ ትኩረት ምን እንደሚመስል፣ከአደረጃጀት አንፃር ደግሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶቹ በተለያዩ ምዕራፎች እንዴት ተከታትለዉ እንደቀረቡ ፣እንዲሁም እንዴት ስፋትና ጥልቀታቸዉን እየጨመሩ እንደቀረቡ በሰነድ ፍተሻ የተገኙ ዉጤቶችና በታላሚዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ከሚገለገሉ መምህራን የተሰበሰቡ መረጃዎች ገለጻዊ መንገድን በመጠቀም የተተነተኑ በመሆናቸዉ ዓይነታዊ ምርምር ተመራጭ ሆኗል፡፡

## 3.2. የናሙና አመራረጥ

### 3.2.1 የመማሪያ መጻህፍት ናሙና አመራረጥ

ተጠኝዎቹ መማሪያ መጻህፍት የተመረጡት በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ነዉ፡፡ምክንያቱም አጥኝዋ በእነዚህ መጻህፍት ለአራት ዓመታት በማስተማር መጻህፍቱ ከሰዋስዉ ትምህርት አቀራረብ መርሆዎች አንጻር የተወሰኑ ክፍተቶች እንዳሉባቸዉ አስተዉላለች፡፡በመሆኑም የበለጠ በጥልቀት በማጥናት ከሰዋስዉ ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት አንጻር የሚታይባቸዉን ጥንካሬና መሻሻል የሚገባቸዉን ጎኖች ለመጠቆም ነዉ፡፡

### 3.2.2 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደቡብ ክልል በ2009 ዓመተ ምህረት ስራ ላይ የዋሉ የ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶችን

ከሰዋስዉ ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት መርሆዎች አንፃር መገምገም ነዉ፡፡በመሆኑም የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት በአንድራቻ ወረዳ ከሚገኙ 19 የመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛና ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች መካከል ዮክጭጪ፣ጫሻና ጌጫ የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛና ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች በአላማ ተኮር ንሞና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ያለዉ(2009፣136) በአላማ ተኮር ንሞና ዘዴ ተመራማሪዉ የጥናቱን ተሳታፊዎች የሚመርጠዉ ከጥናቱ ዓላማ አንፃር ነዉ፡፡እነማንን ብመርጥ የሚፈለገዉ መረጃ ኖሯቸዉ ሊሰጡኝ ይችላሉ የትኞቹ የጥናቱ አካላይ አባላት በጥናቱ ቢሳተፉ አስፈላጊዉን መረጃ ላገኝባቸዉ እችላለሁ የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ሰዎችን ወይም ነገሮችን ይመርጣል በማለት ያስረዳሉ፡፡ከዚህ በመነሳት አጥኝዋ በወረዳዉ ዉስጥ በታላሚዎቹ መማሪያ መጻሕፍት የሚያስተምሩ መምህራንን መረጃ በምታሰባስብበት ወቅት በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች 5ኛና 6ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ የተመረቁ (specialized) ያደረጉ በመሆናቸዉ በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀትን በተመለከተ የጠለቀና የዳበረ መረጃ ይሰጡኛል ከሚል ግላዊ ግምገማ በመነሳት ነዉ፡፡

### 3.2.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

መምህራን ተጨማሪ የመረጃ ምንጭ በመሆን አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡በናሙናነት በተመረጡት ሶስት ትምህርት ቤቶች ዉስጥ በታላሚዎቹ የመማሪያ መጻሕፍት የሚያስተምሩ  የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አጠቃላይ ብዛት ወንድ 2 ሴት 2 በድምሩ 4 ናቸዉ፡፡ እነዚህ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ የተመረቁ (specialized) ያደረጉ በመሆናቸዉ በመማሪያ መጽሀፍቱ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀትን በተመለከተ የጠለቀና የዳበረ መረጃ ይሰጡኛል ከሚል ግላዊ ግምገማ በመነሳት ሁሉንም መምህራን በጠቅላይ የንሞና ዘዴ በመዉሰድ የዚህ ጥናት አካል ተደርገዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 3.1.በናሙናነት በተመረጡ ትምህርት ቤቶች በ5ኛና 6ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩና ለጥናቱ የተመረጡ መምህራን አጠቃላይ ዳራ የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| የትምህርት ቤቱ ስም | የመምህራን ብዛት | | | የመምህራን የትምህርት ደረጃ | የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ | የአገልግሎት ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | | | |
| ዮክጭጪ | 1 | - | 1 | ዲግሪ | 5ኛና 6ኛ | 10 ዓመት |
| ጫሻ | 1 | 1 | 2 | ዲግሪ | 5ኛና 6ኛ | 8 ዓመት |
| ጌጫ | - | 1 | 1 | ዲግሪ | 5ኛና 6ኛ | 14 ዓመት |

## 3.3.የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

### 3.3.1.ሰነድ ፍተሻ

ለጥናቱ አብይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ ያገለገለዉ ሰነድ ፍተሻ ነው፡፡ የሚገመገሙት ሰነዶች በ2009 ዓመተ ምህረት ሥራ ላይ የዋሉ የ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ናቸው፡፡ በመሆኑም በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከአቀራረብ አንጻር ለቋንቋው ቅርጽ፣ ፍቺና አጠቃቀም ምን ያህል ትኩረት እንደተሰጣቸው ፍተሻ ተካሂዷል፡፡ በተጨማሪም ከአደረጃጀት አንጻር በነዚህ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በዚሁ ክፍል በተለያዩ ምዕራፎች ተከታትለው መምጣታቸውንና ከሌሎች ክፍሎች ጋር ተለጣጥቀው መገኘታቸውን ለማረጋገጥ ግምገማ ተካሂዷል፡፡ግምገማው የተካሄደዉ በክለሳ ድርሳን ክፍል የቀረቡትን ንድፈ ሀሳቦች በመመርኮዝ ነዉ፡፡

### 3.3.2 ቃለ -መጠይቅ

ቃለ መጠይቁ የቀረበዉ በጥናቱ በናሙናነት በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች በ2013 ዓመተ ምህረት በተተኳሪዎቹ የክፍል ደረጃዎች በማስተማር ላይ ለሚገኙ 2 ወንድና 2 ሴት በድምሩ 4 መምህራን ነዉ፡፡ለቃለ መጠይቁ 9 ጥያቄዎች የተዘጋጁ ሲሆን በታላሚዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ዙሪያ ያላቸዉን ግላዊ አስተያየት እንዲሰጡ ታልመዉ የቀረቡ ክፍት ጥያቄዎች ናቸዉ፡፡ጥያቄዎቹ ለአራቱ የቋንቋ መምህራን በተናጥል በአጥኝዋ የቀረበላቸዉ ሲሆን ለቀረጻ ፍቃደኛ ካልሆኑት መምህራን ማስታወሻ በመያዝ ፍቃደኛ ከሆኑት ደግሞ በመቅረጸ ድምጽ እንዲቀረ ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም

መረጃዎቹ ወደ ወረቀት ተመልሰዉ በትንተናዉ ዉስጥ ጥቅም ላይ ዉለዋል፡፡ የቃለ መጠይቁ ጥያቄዎችም በአጥኚዋ ከተዘጋጁ በኋላ በአማካሪ ተገምግመዉ አስፈላጊዉ ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል፡፡

## 3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ገላጭ የምርምር ዘዴ በመጠቀም ተተኳሪ በሆኑት በ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በክለሳ ድርሳናት ውስጥ ከተጠቀሱት የሰዋስው ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት ንድፈ ሀሳቦች አንጻር እየተፈተሹ ተተንትነዋል፡፡ በመሆኑም ሰነድ ፍተሻን በመጠቀም በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶችን በስነ-ድምጽ፣ ስነ-ምዕላድ፣ስነ-አገባብና ስነ-ፍች ንዑሳን ክፍሎች በየፈርጃቸዉ ተለይተዉ እንዲመደቡ ከተደረገ በኋላ በክለሳ ድርሳን የቀረቡትን የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከስነ-ትምህርታዊ ሰዋስዉ የማቅረቢያ መርሆች አንጻር በተለያዩ ባለሙያዎች ዘንድ ከቀረቡት ንድፈ ሀሳቦች ዉስጥLarsenFreeman(1991)፣ Harmer(1991) Ur(1996) የሚያራምዷቸዉን ንድፈ ሀሳቦች በመመርኮዝ ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ እንዴት እንደቀረቡና እንደተደራጁ እየተመረመረ ትንተናዉ ተካሂዷል፡፡በተጨማሪም አጋዥ የመረጃ ምንጭ ከሆኑት መምህራን የተገኙ መረጃዎች በሰነድ ፍተሻ የተገኙትን መረጃዎች ተከትለዉ ቀርበዋል፡፡ተተኳሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትም በመጀመሪያ የ5ኛ ክፍል ቀጥሎም የ6ኛ ክፍል ደረጃ በደረጃ ተተንትነዋል፡፡ሁለቱንም መማሪያ መጻሕፍት ለመገምገም በአጥኚዋ የተዘጋጁ መጠይቆች ተመሳሳይ በመሆናቸዉ ከመጻሕፍቱ ተገልጋዮች የተገኙ ምላሾች በክፍል ደረጃ ቅደም ተከተል ትንታቴ ተሰጥቶባቸዋል፡፡በመጨረሻም በምዕራፍ አምስት የጥናቱን ግኝቶች በአጭሩ በመጠቆም ታላሚዎቹ የመማሪያ መጻሕፍት ከሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት መርሆዎች አንጻር የሚታይባቸዉ ጠንካራ ጎኖች ተጠናክረዉ እንዲቀጥሉ፤ መሻሻል የሚታይባቸዉን ጎኖች በመጠቆም ጥናቱ ተጠቃሏል፡፡

# ምዕራፍ  አራት:- የጥናት ዉጤት ትንተናና ማብራሪያ

## 4.1 የጥናት ዉጤት ትንተና

በዚህ ክፍል የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑ የ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በክለሳ ድርሳን ክፍል ከሰፈሩት ንድፈ ሀሳቦች አንጻር ተተንትነዋል፡፡ በተጨማሪም ከመምህራን በቃለ መጠይቅ በተገኙ ምላሾች ትንተናዉን ለማጠናከር ጥረት ተደርጓል፡፡በቅድሚያ ግን ስለተተኳሪዉ መጻሕፍት ውስጣዊና ዉጫዊ ገጽታ አጠር ያለ ቅኝት እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

### 4.1.1 የመማሪያ መጻሕፍቱ አጠቃላይ ቅኝት

የ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተዉ በደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ ለክልሉ እንዲስማሙ ተደርጎ በ2007 ዓመተ ምህረት ተዘጋጅተዉ በ2009 ዓመተ ምህረት ስራ ላይ የዋሉ ናቸዉ፡

#### 4.1.1.1 የ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አጠቃላይ ቅኝት

ተጠኝዉ መጽሀፍ 233 ገጾችና 10 ምዕራፎችን አሉት፡፡እያንዳንዱ ምዕራፍ ደግሞ በሶስት ሳምንትና በዘጠኝ ቀናት ተሸንሽኖ ቀርቧል፡፡በመጽሀፉ 10 ዋና ርዕሶችን መሰረት ያደረጉ 30 ምንባቦች ቀርበዋል፡፡ ከእነዚህ ምንባቦች መካከል 16ቱ ኢ-ልቦለድ ፣13ቱ ልቦለድና 1 ግጥም ናቸዉ፡፡በታላሚዉ መጽሐፍ ዉስጥ ከተካተቱት 190 መልመጃዎች መካከል14ቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶችን የሚያስተምሩ ሲሆኑ እነዚህን ይዘቶች በመደጋገም በታላሚዉ መጽሀፍ ዉስጥ 60 ጊዜ ቀርበዋል፡፡በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ተማሪዎችን ሊያግዙ ይችላሉ ተብለዉ ከቀረቡት 9 የተለያዩ ገለጻዎች መካከል ሰዋስዉን የሚመለከት ገለጻ ግን 1 ብቻ መሆኑን  ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህንን የመጽሀፉን አጠቃላይ ገጽታ በሚከተለዉ  ሰንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡፡

## ሰንጠረዥ.4.1 የ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አጠቃላይ ቅኝት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ምዕራፍ | የምዕራፎች ዋና ርዕስ | የምንባቦች ርዕስ | የምንባቡ ዓይነት | የቀረቡት መልመጃዎች ብዛት | የቀረቡት የሰዋስው መልመጃ ብዛት | በአጠቃላይ የቀረበው ገለጻ ብዛት | የቀረቡት የሰዋስው ገለጻ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጓደኝነት | ሀዋና ጓደኞቿ | ልቦለድ | 7 | 2 | 1 | ---- |
| | | ለጓደኛ አለመታመን | | 6 | 2 | 1 | --- |
| | | ሱሰኝነትና መዘዙ | | 6 | 2 | --- | ---- |
| 2 | አከባቢያችን | የአየርና የውሃ ብክለት | ኢ-ልቦለድ | 7 | 2 | ---- | --- |
| | | የቆሻሻ አፈጣጠርና የሚየስከትላቸው ችግሮች | | 6 | 2 | --- | ---- |
| | | በኢትዮጵያ የደን መመናመን መንስኤዎችና የሚያስከትላቸው ችግሮች | | 6 | 2 | --- | -- |
| 3 | ልማዶች | ቡና ጠጡ | ልቦለድ | 7 | 2 | 3 | 1 |
| | | ዕድር | ኢ-ልቦለድ | 6 | 2 | -- | --- |
| | | ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች | | 6 | 2 | --- | ---- |
| 4 | የትራፊክ ደህንነት | የመንገድ ላይ ጥንቃቄ | | 7 | 2 | 1 | ----- |
| | | አስቀድሞ መጠንቀቅ | ልቦለድ | 6 | 2 | --- | --- |
| | | በድንገተኛ አደጋ ጊዜ የሚወሰዱ እርምጃ | ኢ-ልቦለድ | 6 | 2 | --- | --- |
| 5 | ጽዳትና ንጽህና | ማቃጠል ወይስ መቅበር? | | 7 | 2 | 1 | --- |
| | | የጥሩ ጓደኛ ምክር | ልቦለድ | 6 | 2 | --- | --- |
| | | ቆሼና አዲሱ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ | ኢ-ልቦለድ | 6 | 2 | ---- | --- |
| 6 | ምግብ | ምግቦቻችን | | 7 | 2 | 1 | --- |
| | | የስንዴ ዳቦ አዘገጃጀት | | 6 | 2 | 1 | --- |
| | | የተመጣጠነ ምግብ ጥቅም | | 6 | 2 | --- | --- |
| 7 | የዱር እንስሳት በኢትዮጵያ | አጋዘን አስተኔ | | 7 | 2 | --- | --- |
| | | ዋልያና ቀይ ቀበሮ | | 6 | 2 | --- | --- |
| | | በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ይዞታ | ኢ-ልቦለድ | 6 | 2 | --- | --- |
| 8 | ባህላዊ ጫወታዎች | የገና ጫወታ ትውስታ | ልቦለድ | 7 | 2 | --- | --- |
| | | እቴ ሜቴ | | 6 | 2 | --- | --- |
| | | የፈረስ ሸርጥ(ሽምጥ)ውድድር ጫወታ | ኢ-ልቦለድ | 6 | 2 | --- | --- |
| 9 | ስነ ቃል | ቃላዊ ግጥም | ግጥም | 7 | 2 | ---- | --- |
| | | ይቅር ደሞወዜ | ልቦለድ | 6 | 2 | --- | --- |
| | | የምሳሌያዊ ንግግሮች ፋይዳ | | 6 | 2 | --- | --- |
| 10 | ኤች አይ ቪ ኤድስ መድሎና መገለል | ወይኔ ሰውዬው | | 7 | 2 | --- | --- |
| | | ሁሉም የድርሻውን ይወጣ | | 6 | 2 | --- | --- |
| | | ፍቅርና እንክብካቤ | | 6 | 2 | --- | --- |
| | | | ድምር | 190 | 60 | 9 | 1 |

### 4.1.1.2 የ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ አጠቃላይ ቅኝት

ተተኳሪዉ መጽሀፍ 233 ገጾችና 10 ምዕራፎች ያካተተ ሲሆን እያንዳንዱ ምዕራፍ 3ምንባቦችን ይዟል፡፡ ሁሉም ምንባቦች የተለያየ ይዘቶችን የሚያስተምሩ መልመጃዎችንና ገለጻዎችን አካትተዉ በመያዝ ለ3 ቀናት ተከፋፍለው ቀርበዋል፡፡ ተተኳሪዉ መጽሐፍ 30 ምንባቦችን የያዘ ሲሆን 14 ኢ-ልቦለድ ፣10 ልቦለድ፣ 3 ግጥምና 3 ተዉኔት ናቸዉ፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከተካተቱ የተለያየ ይዘት ካላቸው 190 መልመጃዎች መካከል 25ቱ ሰዋስዉን የሚያስተምሩ ሲሆኑ እነዚህን ይዘቶች በመደጋገም 60 ጊዜ ቀርበዋል፡፡በመጽሐፉ ውስጥ ተማሪዎችን ሊያግዙ የሚችሉ 3 ገለጻዎች የቀረቡ ሲሆን ለሰዋስው ትምህርት መግለጫነት የቀረቡ ገለጻዎች ግን አለመካተታቸውን በሰነድ ፍተሻና ቃለ መጠይቅ ከተገኙ መረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡የመጽሐፉን አጠቃላይ ገጽታ በሚመለከት የሚከተለውን ሠንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡፡

**ሰንጠረዥ.4.2 የ6ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አጠቃላይ ቅኝት የሚሳይ ሰንጠረዥ**

| ምዕራፍ | የምዕራፎች ዋና ርዕሶች | የምንባቦች ርዕስ | የምንባቡ ዓይነት | የቀረበው መልመጃ ብዛት | የቀረበው የሰዋስው መልመጃ ብዛት | የቀረበው ገለጻ ብዛት | የቀረበው የሰዋስው ገለጻ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ባህላዊ ልብስ | ሙሽሮቹ | ልቦለድ | 7 | 2 | --- | --- |
| | | ዓውደ ዓመት | | 6 | 2 | --- | --- |
| | | ባህላዊ ልብሶቻችን | ኢ-ልቦለድ | 6 | 2 | --- | --- |
| 2 | ታዋቂ አትሌቶች | ማርሽ ቀያሪው | | 7 | 2 | --- | --- |
| | | ጽናት ያላት አትሌት | | 6 | 2 | --- | --- |
| | | የስኬታማነት ምስጢር | | 6 | 2 | --- | --- |
| 3 | ቃላዊ ግጥሞች | ዘመናይ ማሪዬ | ግጥም | 7 | 2 | 1 | --- |
| | | በሰፊው ለማረስ | | 6 | 2 | --- | --- |
| | | ቃላዊ ግጥም | ኢ-ልቦለድ | 6 | 2 | --- | --- |
| 4 | ልጅነት | መሃረቤን ያያችሁ | | 7 | 2 | --- | --- |
| | | የጠወለገ ልጅነት ሲያብብ | ልቦለድ | 6 | 2 | --- | --- |
| | | በአግባቡ የታነጸ ልጅነት | | 6 | 2 | 2 | --- |
| 5 | ቱሪዝም | አባያና ጫሞ ሃይቆች | ኢ-ልቦለድ | 7 | 2 | --- | --- |
| | | ቱሪዝም በኢትዮጵያ | | 6 | 2 | --- | --- |
| | | ቱሪዝምና ቀበሌያችን | ልቦለድ | 6 | 2 | --- | --- |
| 6 | ተወዳጅ ታሪኮች | ቤተሰባዊ ገጽታ | | 7 | 2 | --- | --- |
| | | ለፍሬ መብቃት | | 6 | 2 | --- | --- |
| | | የህይወት ውጣ ውረድ | | 6 | 2 | --- | --- |
| 7 | ኤች-አይ-ቪ ኤድስ በኢትዮጵያ | ኤች-አይ-ቪ እና መተላለፊያዎቹ | ኢ-ልቦለድ | 7 | 2 | --- | --- |
| | | በሽታውን የደበቀ | ልቦለድ | 6 | 2 | --- | --- |
| | | ሃያትና ጓደኛዋ | | 6 | 2 | --- | --- |
| 8 | ባህላዊ | እንቁጣጣሽ | ግጥም | 7 | 2 | --- | --- |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ክንዋኔዎች | ያልተፈታ ችግር | ኢ-ልቦለድ | 6 | 2 | --- | --- |
| | | ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች | | 6 | 2 | --- | --- |
| 9 | ሴቶችን ማብቃት | ሥርዓተጾታና ትምህርት | | 7 | 2 | --- | ---- |
| | | የትነበርሽ | | 6 | 2 | --- | --- |
| | | ፋና ወጊዋ ካፒቴን | | 6 | 2 | --- | --- |
| 10 | ተውኔት | ጅብነች ትዕይንት 1 | ተውኔት | 7 | 2 | --- | --- |
| | | ጅብነች ትዕይንት 2 | | 6 | 2 | --- | --- |
| | | የመንደሩ መረፌ ወጊ | | 6 | 2 | ---- | ---- |
| | | | ድምር | 190 | 60 | 3 | ---- |

### 4.1.2 በመማሪያ መጻሕፍቱ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ

#### 4.1.2.1 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ

በዚህ የአቀራረብ ስልት ለተማሪዎች ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቱን በሚመለከት ህግጋት ደንቦችና ገለጻዎች እየቀረቡላቸዉ ህጉን መሰረት በማድረግ የሚቀርቡላቸዉን መልመጃዎች በመስራት ትክክለኛዉን የቋንቋዉን ስርዓት እንዲያዉቁ የሚያደርግ አቀራረብ መሆኑን በክለሳ ድርሳን ክፍል ተጠቅሷል፡፡

##### 4.1.2.1.1 የ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ

በአምስተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ተካትተዉ ከቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ገለጻ የቀረበበት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘት ኢ-ሳቢ ግስን አስመልክቶ የቀረበ ሲሆን ይኸዉም፡-*አስረጂ 1 ‹‹ኢ-ሳቢ ግስ የሚባለዉ ድርጊቱ በራሱ በባለቤቱ ላይ ያለቀ መሆኑን የሚያሳይ ወይም ድርጊቱ ወደሌላ አካል የማይሻገር የግስ ዓይነት ነዉ፡ምሳሌ፡-መጣ ፣ሄደች፣ ቆመ፣ ተቀመጠች የመሳሰሉት ግሶች ኢ-ሳቢ ግሶች ናቸዉ፡፡››የሚል ነዉ፡፡ /ገጽ፣ 48/*

ይህን የሰዋስዉ ትምህርት ይዘት አቀራረብ ስንመለከት ተማሪዎች ከቀረበላቸዉ ማብራሪያ በመነሳት የቋንቋዉን አጠቃላይ ስርዓት እንዲያዉቁ የሚያግዝ ነዉ፡፡ይሁን እንጂ በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ከላይ ከተጠቀሰዉ አቀራረብ ዉጪ ሌሎች የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ መርህን ተከትለዉ ያልቀረቡ መሆናቸዉን በሰነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ነገር ግን በክለሳ ድርሳናት ክፍል ለማቅረብ እንደተሞከረዉ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ በሚቀርቡበት ወቅት የአቀራረብ መርሆዎችን ተከትለዉ መሆን እንዳለበት የተለያዩ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ Ur (1996) ‹‹የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ በሚካተቱበት ጊዜ ሁሉንም የማቅረቢያ መንገዶች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ አካትተዉ ቢቀርቡ የተሻለ ዉጤት ይገኛል፡፡›› በማለት

ያስረዳሉ።ምክንያቱም አቀራረቡ ለተማሪዎች ስለቋንቋዉ ህግጋትና አወቃቀር ማብራሪያ ስለሚሰጣቸዉ ከተሰጠዉ በምሳሌ የተደገፈ ማብራሪያ በመነሳት የሚቀርብላቸዉን ይዘት በፍጥነትና በቀላሉ እንዲረዱት ያስችላቸዋል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ይዘቶችን አስመልክተዉ ለሚያቀርቡት ጥያቄዎች ምላሽ በመስጠት ተማሪዉን ሆነ መምህሩን ያግዛል፡፡ዳሩ ግን ተተኳሪዉ መማሪያ መጽሐፍ ይህን የአቀራረብ መርህ ከሌሎች የአቀራረብ መርሆዎች ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ባለማቅረቡ ክፍተት ይስተዋልበታል፡፡ከዚህ አቀራረብ ጋር ተያያዥነት ያለዉ ጥያቄ ለመምህራን ከቀረበዉ ቃለ መጠይቅ የተገኘዉ ምላሽ እንደሚከተለዉ ቀርቧል ፡፡

ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ ቁጥር 1.በአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ከተካተቱት የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች ዉስጥ የቋንቋዉን ሰዋሰዋዊ ስርዓት የሚያሳዉቁ ገለጻዎችን በመስጠት በዛዉ መነሻነት ተማሪዎች መልመጃዎችን እንዲሰሩ የሚያደርጉ አቀራረቦች አሉ፡፡

መምህር 1‹‹በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የቀረቡ አብዛኛዎቹ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ገለጻዎች የቀረቡባቸዉ አይደሉም፡፡››በማለት መልሰዋል፡፡

መምህርት 2 ደግሞ‹‹መማሪያ መጽሀፍቱ ዉስጥ የቀረቡ ብዙዎቹ ይዘቶች ገለጻዎች የታከሉባቸዉ አይደሉም፡፡ነገርግን ጥቂት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በማብራሪያ ተደግፈዉ መቅረባቸዉን ማስተዋል ችያለሁ፡፡››በማለት አስረድተዋል፡፡

መምህርት 3 በበኩላቸዉ‹‹መማሪያ መጽሀፉ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ገለጻዎች ያልቀረቡባቸዉ ናቸዉ፡፡››በማለት አስተያየታቸዉን ሰጥተዋል፡፡

ከዚህ የምንረዳዉ በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ መርህን ያልተከተሉ መሆናቸዉን በሰነድ ፍተሻና ለመምህራን ከቀረበዉ ቃለመጠይቅ የተገኙ ዉጤቶች ያመለክታሉ፡፡

#### 4.1.2.1.2 የ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ መርህን ተከትሎ የቀረበ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘት አለመኖሩን በሰነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በዚህ አቀራረብ ዙሪያ በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሀፍ ለሚያስተምሩ መምህራን ከቀረበ ቃለመጠይቅ የተገኙ ምላሾችን እንመልከት፡-

ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ ቁጥር 1.በአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ከተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ዉስጥ የቋንቋዉን ሰዋስዋዊ ስርዓት የሚያሳዉቁ ገለጻዎችን በመስጠት በዛዉ መነሻነት ተማሪዎች መልመጃዎችን እንዲሰሩ የሚያደርጉ አቀራረቦች አሉ፡፡

መምህር 1 ‹‹እኔ እንዳስተዋልኩት በመማሪያ መጽሀፉ ዉስጥ ከቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል ገለጻ የቀረበበት ይዘት የለም፡፡ሁሉም ይዘቶች ምሳሌዎችን እያሳዩ መልመጃዎችን ያቀረቡ ናቸዉ፡፡››በማለት ምላሻቸዉን ሰጥተዋል፡፡

መምህር 2 ደግሞ ‹‹በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ገለጻ የቀረበበት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘት የለም፡፡››በማለት አስተያየታቸዉን ሰጥተዋል፡፡

መምህር 3 ‹‹በማስተምርበት መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ማስታወሻ በማቅረብ ተማሪዎች መልመጃዎችን እንዲሰሩ የሚጋብዝ አቀራረብ የለም፡፡››በማለት አስረድተዋል፡፡

ከመምህራኑ ከተገኙት ምላሾች መረዳት እንደሚቻለዉ በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ገለጻዎችን በማቅረብ ተማሪዎች መልመጃዎችን እንዲሰሩ የሚያደርጉ አቀራረቦች አለመኖራቸዉን ነዉ፡፡ይህም መማሪያ መጽሀፉ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ መርህን በተከተለ መልኩ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ማቅረብ ያለመቻሉን ነዉ፡፡Harmer(1987)በክፍል ዉስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የተለያዩ እንደመሆናቸዉ የተለያየ የትምህርት አቀባበል ያላቸዉ ናቸዉ፡፡ይህ ብቻም ሳይሆን የተለያዩ የትምህርት ዓላማዎች የተለያዩ አቀራረቦችን የሚከተሉ በመሆናቸዉ ሁሉም የሰዋስዉ ትምህርት አቀራረቦች በመማሪያ መጻህፍቱ ዉስጥ መካተት እንዳለባቸዉ ያስረዳሉ፡፡

### 4.1.2.2 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ

ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአቀራረብ ስልት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቱን በሚመለከት ምንም ዓይነት ገለጻ ሳይቀርብ ነገርግን ተማሪዎች በምሳሌዎች እየታገዙ መልመጃዎችን ከሰሩ በኋላ በራሳቸው ጥረት አጠቃላይ የቋንቋውን ስርዓት ለይተው እንዲገነዘቡ የሚያስችል ስልት መሆኑን በክለሳ ድርሳን ላይ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡

#### 4.1.2.2.1 የ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

በ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአቀራረብ ስልትን ተከትለዉ የቀረቡ ናቸው፡፡በአስረጂነት የሚከተሉትን እንመልከት ፡-

አስረጂ.2 « *ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ስሞች የተጸውኦ ወይም የወል ስም መሆናቸውን ለይታችሁ በደብተራችሁ ሠንጠረዥ አዘጋጅታችሁ መድቡ » ከሚል ትዕዛዝ ስር የሚከተለው ምሳሌ ይገኛል።*

| *የተጸውኦ ስም* | *የወል ስም* |
|---|---|
| *ዋቢ ሸበሌ* | *ድመት* |

*/ ገጽ፣19 /*

ሌላዉ በዚህ የአደረጃጀት ስልት ከቀረቡት ይዘቶች መካከል በምዕራፍ ዘጠኝ ግሳዊ ሀረግ መለየትን በተመለከተ የቀረበዉ ይዘት ይጠቀሳል ።በዚህም መሰረት፡-

አስረጂ.3 *‹‹በሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ዉስጥ የሚገኙትን ግሳዊ ሀረጎች ለይታችሁ በደብተራችሁ ጻፉ።››*

*ምሳሌ፡- በለጡ ወደ ቤቷ ሮጠች።*

*ግሳዊ ሀረግ ፡ ወደ ቤቷ ሮጠች /ገጽ፣188/*

ከላይ በአስረጂ 2 የቀረቡትን መልመጃዎች ስንመለከት ተማሪዎች ከቀረቡላቸዉ ስሞች የተጸዉኦና የወል ስሞችን እየለዩ እንዲጽፉ *ይጠበቃል።በአስረጂ3 ደግሞ ከቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ዉስጥ ግሳዊ ሀረጉን ብቻ ለይተዉ በማዉጣት እንዲያመለክቱ ያዛል*።እነዚህ የቀረቡ ይዘቶችን ስንመለከት ተማሪዎች የተሰጧቸዉን ምሳሌዎች በመመልከት መልመጃዎቹን ከሰሩ በኂላ ወደ ሰዋስዋዊ ስርዓቱ እንዲሄዱ የሚጋብዙ በመሆናቸዉ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአቀራረብ መርህን የተከተሉ ናቸዉ።

ሌላዉ በምዕራፍ አምስት ስር ቅፅልንና የሚገልፁትን ነገር መለየትን በተመለከተ የቀረበዉ ይዘት ይጠቀሳል፡ይኸዉም *አስረጂ.4 ‹‹ከዓረፍተ ነገሮቹ በታች የቀረበዉን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጁ። ከዚያም ቅፅሎችን ከዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ እየለያችሁ በሠንጠረዥ ዉስጥ ፃፉ። ቀጥሎም የሚገልፁትን ነገር አመልክቱ››/ገፅ፣87/* በማለት መልመጃ ቀርቧል።በተጨማሪም በምዕራፍ ስምንት ቅፅልን፣መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮችን መለየት በሚል ንኡስ ርዕስ ስር ‹‹ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ያሉትን መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮች እንዲሁም ቅፅሎችን ለይታችሁ በምሳሌዉ መሰረት በደብተራችሁ ፃፉ።››በማለት የሚከተለዉ ምሳሌ ቀርቧል።

*አስረጂ.5 ምሳሌ ስድስት ነጫጭ በጎች አሉኝ።*

*ስድስት =መጣኝ ቁጥር*

*ነጫጭ=ቅፅል / ገጽ፣164/*

ከላይ የቀረቡት መልመጃዎች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብን የተከተሉ ናቸዉ፡፡ነገር ግን ትዕዛዞቹን ስንመለከት ከአንድ በላይ ጉዳዮችን የሚጠቅሱ ናቸዉ፡፡ይህ ሲባል ግን የግድ አንድ ጉዳይ ብቻ ይጠየቅ ለማለት አይደለም ፡፡ምክንያቱም በአንድ ይዘት ስር የተለያዩ ጉዳዮችን ማቅረብ ተማሪዎች የይዘቱን ተከታታይነት እያወቁ እንዲሄዱ የሚያግዝ ጠንካራ ጎን ቢኖረዉም እንኳ እንደክፍል ደረጃዉ ይለያያል፡፡Harmer(1987) የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በሚቀርቡበት ወቅት የተማሪዎችን ዕድሜና የቀደመ ዕዉቀት መሰረት ማድረግ እንዳለባቸዉ አበክረዉ እንደሚገልፁ በክለሳ ድርሳን ክፍል ለመጥቀስ ተሞክሯል፡፡በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአቀራረብ መርህን ተከትለዉ የቀረቡ ቢሆንም ከይዘቶቹ መደራረብ የተነሳ የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች የቋንቋዉን ሰዋስዋዊ ስርዓት በራሳቸዉ ጥረት በቀላሉ ለመገንዘብ ሊቸግራቸዉ ይችላል፡፡ ይህን አቀራረብ  አስመልክቶ 5ኛ ክፍል ለሚያስተምሩ መምህራን ከቀረበዉ መጠይቅ የተገኙ ምላሾችን ቀጥለን እንመልከት፡-

ለመምህራን የቀረበ መጠየቅ ቁጥር 2. በመማሪያ መጽሐፉ ዉስጥ ከቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ዉስጥ ምሳሌዎችን በማቅረብ በዛዉ መነሻነት ተማሪዎች መልመጃዎችን እንዲሰሩ እና የቋንቋዉን ስርዓት ወደ መለማመድ እንዲሸጋገሩ የሚያደርጉ አቀራረቦች አሉ፡፡

መምህር 1‹‹እኔ በማስተምርበት ጊዜ እንዳስተዋልኩት በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍ ዉስጥ የቀረቡ አብዛኛዎቹ ይዘቶች ምሳሌዎችን በማሳየት ተማሪዎች የተሰጧቸዉን መልመጃዎች እንዲሰሩ የሚጋብዙ ናቸዉ፡፡››በማለት አስረድተዋል፡፡

መምህርት 2 ደግሞ‹‹በመማሪያ መጽሀፉ ዉስጥ የቀረቡ በርካታ የሰዋስዉ ይዘቶች ተማሪዎች መልመጃዎችን እንዲሰሩና በራሳቸዉ ጥረት የቋንቋዉን ስርዓት እንዲደርሱበት የሚያደርጉ ቢሆኑም የተወሰኑ መልመጃዎች ግን በምሳሌዎች ታግዘዉ አለመቅረባቸዉን አስተዉያለሁ፡፡›› በማለት አስተያየታቸዉን ሰጥተዋል፡፡

መምህርት 3‹‹በመማሪያ መጽሀፉ የተካተቱ ሁሉም የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች የቀረቡት ምሳሌዎችን በማሳየት ተማሪዎች መልመጃዎችን እንዲሰሩና በተደጋጋሚ ልምምድ የቋንቋዉን ስርዓት እንዲያዉቁ የሚያደርጉ ናቸዉ፡፡››በማለት ምላሻቸዉን ሰጥተዋል፡፡

ከላይ ከመምህራኑ የተሰጡ ምላሾችን ስንመለከት ተቀራራቢ በሆነ መልኩ መማሪያ መጽሀፉ መልመጃዎችን በማቅረብ ተማሪዎች በምሳሌዎች ተደግፈዉ እንዲለማመዱ በማድረግ የቋንቋዉን ስርዓት እንዲደርሱበት የሚያደርጉ አቀራረቦች መካተታቸዉን ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ በ5ኛ ክፍል *መማሪያ* መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከአቀራረብ መርህ አንጻር ምን እንደሚመስሉ በተደረገዉ ሰነድ ፍተሻና በመማሪያ መጽሐፉ ለሚገለገሉ መምህራን በተደረገዉ መጠይቅ ከተገኙ ምላሾች ማረጋገጥ እንደተቻለዉ ተተኳሪዉ *መማሪያ* መጽሐፍ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአቀራረብ መርህን አካትቶ መቅረቡን መረዳት ተችሏል፡፡

### 4.1 2.2.2 የ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

በስድስተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ *መማሪያ* መጽሐፍ ዉስጥ የተካተቱ በርካታ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአቀራረብ ስልትን ተከትለዉ የቀረቡ ናቸዉ፡፡በአስረጅነትም የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡-‹‹የሚከተሉትን ሰንጠረዥ በምሳሌዉ መሰረት በደብተራችሁ አሟልታችሁ ጻፉ፡፡›› ከሚል ትዕዛዝ ስር የሚከተለዉ ምሳሌ ይገኛል*፡፡አስረጂ.6*

| *የዋህ ኃላፊ ግስ* | *ጾታ* | *መደብ* | *ቁጥር* |
|---|---|---|---|
| *ወደቀ* | *ተባዕት* | *3ኛ* | *ነጠላ* |

*ከላይ የቀረበዉን ይዘት ስንመለከት ተማሪዎች የቀረበላቸዉን ምሳሌ በመመልከት ግሱን በጾታ፣በመደብና በቁጥር ተንትነዉ እንዲለዩ ያዛል፡፡*

ሌላዉ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ከቀረቡት ይዘቶች መካከል፡-

አስረጂ *7‹‹ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ባለቤትና ማሰሪያ ግሱን ለይታችሁ ጻፉ፡፡››*

*ምሳሌ፡-ደራርቱ አሸነፈች፡፡በዚህ ዓረፍተ ነገር ባለቤቱ ደራርቱ የሚለዉ ቃል ሲሆን ማሰሪያ ግሱ አሸነፈች የሚለዉ ነዉ፡፡በሚለዉ ትዕዛዝ ስር ስድስት ዓረፍተ ነገሮች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም መካከል፡-*

*ሀ.ዓለሙ ተኛ፡፡*

*ለ.ዘይነባ ተነሳች፡፡የሚሉት ይገኙበታል፡፡/ገጽ፣29/*

*አስረጂ 8 በተጨማሪም ቅጽልንና መስተዓምር መለየትን አስመልክቶ‹‹የሚከተሉትን ቃላት ቅጽል ወይም መስተዓምር በማለት በሰንጠረዡ ዉስጥ ለይታችሁ አመልክቱ፡፡››*

*ምሳሌ፡-ቅጽል-ደካማ*

*መስተዓምር-ሁለት*

*በሚል መልመጃ ስር አስራ አንድ ቃላት ይገኛሉ፡፡ከነዚህም ዉስጥ፡-*

*ሀ.ጥቁር*

*ለ.ሁለት የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡/ገጽ፣88/*

*ሌላዉ ደግሞ የቃላትን ፊደላት በማጥበቅና በማላላት የተለያየ ፍቺ መስጠት በተሰኘዉ ይዘት ስር፡-*

*አስረጂ 9‹‹የሚከተሉትን ቃላት ፊደላቸዉን በማጥበቅና በማላላት ሁለት ፍቺ እንዲሰጡ አድርጋችሁ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸዉ፡፡››*

*ምሳሌ፡-ጥፍር ካደገ ቆሻሻ ይይዛል፡፡*

*መንገደኛዋ ወገቧን በመቀነቷ ጥፍር አድርጋ ስትጓዝ ዋለች፡፡*

*ሀ.አብራ(አንቀጽ 2)*

*ለ.ሰፈሩ(አንቀጽ 3) /ገጽ፣155/* የሚሉት መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡

በተጨማሪም በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአቀራረብ መርህን ተከትለዉ ከቀረቡት የሰዋስዉ ይዘቶች መካከል ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ተሳቢ መለየትን በሚመለከት የቀረበዉን ይዘት ስንመለከት፡-

*አስረጂ 10 ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ተሳቢዎችን በመጠቀም ክፍት ቦታዎችን በማሟላት ዓረፍተ ነገሮችን ጻፉ፡፡ምሳሌ ዓለሙ ለአባቱ ኮት ሰጣቸዉ፡፡ለአባቱ ኢቀጥተኛ ተሳቢ ሲሆን ኮት ደግሞ ቀጥተኛ ተሳቢ ነዉ፡፡በማለት ስድስት ያልተሟሉ ዓረፍተ ነገሮች ቀርበዋል፡፡ከእነዚህም መካከል*

*ሀ.አሚናት- -ነገረቻቸዉ፡፡*

*ለ.አልማዝ- -ለካሰች፡፡/ገጽ፣224/ የሚሉት ይገኙበታል፡፡*

ከላይ የተዘረዘሩት የሰዋስዉ ትምህርት መልመጃዎች በተጠኘዉ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአቀራረብ መርህን ተከትለዉ የቀረቡ ናቸዉ፡፡ Woods (1995) ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ማቅረብ ሲባል በአግባቡ የተመረጡ ምሳሌዎችን በማቅረብ ተማሪዎች የቀረቡትን ምሳሌዎች መሰረት አድርገዉ የተሰጣቸዉን መልመጃዎች ከሰሩ በኋላ የቋንቋዉን ህግ በራሳቸዉ እንዲደርሱበት የሚያደርግ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ስንመለከተዉ ተማሪዎቹ የቀረበላቸዉን ምሳሌ ተደግፈዉ የተሰጧቸዉን መልመጃዎች ደጋግመዉ በመስራት የቋንቋዉን አጠቃላይ ስርዓት በራሳቸዉ ጥረት ለይተዉ ለማወቅ አይቸገሩም፡፡

ሌላዉ በተተኳሪው መጽሐፍ ውስጥ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአቀራረብ ስልት ተከትለው ከቀረቡ ይዘቶች መካከል ገጽ/176/ ተግባር 3 ላይ የቀረበዉን መልመጃ ስንመለከት

*‹‹በሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ወደረኛ መስተኣምሮች ለዩ » በሚል ትዕዛዝ ስር ከቀረቡት አረፍተ ነገሮች መካከል ለአብነት እንመልከት፡-*

*አስረጂ 11 ሀ. ጨረቃና ኮከብ የራሳቸው ብርሃን የላቸውም።*

*ለ. በቃላችሁ ወይም በጽሑፍ መልሱ።የሚሉና ሌሎች አረፍተ ነገሮች ይገኙበታል።/ገጽ፣176/*

ከላይ የቀረበው መልመጃ ትዕዛዝ ችግር ይስተዋልበታል።ይኸውም ወደረኛ መስተፃምር እንጂ ወደረኛ መስተኣምር የሚባል የመስተኣምር ዓይነት የለም።በትዕዛዙ ስር የቀረቡት ዓረፍተ ነገሮችንም ስንፈትሽ መስተኣምር አይገኝባቸውም።በመሆኑም እንደዚህ ዓይነት አቀራረቦች ተማሪዎችን ወደተሳሳተ ግንዛቤ ሊመሯቸው ስለሚችሉ በተቻለ መጠን ጥንቃቄ ቢደረግበት የተሻለ ይሆናል።በመቀጠል ከዚህ የአቀራረብ መርህ ጋር በተያያዘ ለመምህራን ከቀረበ ቃለ መጠይቅ የተገኙ ምላሾችን እንደሚከተለዉ ቀርበዋል::

ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ ቁጥር 2. በመማሪያ መጽሐፉ ዉስጥ ከቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ዉስጥ ምሳሌዎችን በማቅረብ በዛዉ መነሻነት መልመጃዎችን እንዲሰሩና የቋንቋዉን ስርዓት ወደመለማመድ እንዲሸጋገሩ የሚያደርጉ አቀራረቦች አሉ።

መምህር 1.‹‹በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የተካተቱ በርካታ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ምሳሌዎችን በማሳየት ተማሪዎች መልመጃዎችን እንዲሰሩ የሚጋብዙ መሆናቸዉን አስተዉያለሁ።››በማለት አስረድተዋል።

መምህርት 2 ደግሞ‹‹መማሪያ መጽሀፉ ተማሪዎች መልመጃዎችን እየሰሩ በራሳቸዉ ጥረት የቋንቋዉን ስርዓት እንዲለዩ በሚገፋፋ መልኩ መቅረቡን እንደጠንካራ ጎን አይቸዋለሁ።›› በማለት አስተያየታቸዉን ሰጥተዋል።

መምህርት 3 በበኩላቸዉ‹‹በርግጥ በርካታ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች የቀረቡት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአቀራረብ መርህን ተከትለዉ ነዉ።ነገርግን የተወሰኑ መልመጃዎች በምሳሌዎች ታግዘዉ አለመቅረባቸዉን ተመልክቻለሁ ይህ ቢስተካከል።››በማለት ምላሻቸዉን ሰጥተዋል።

ከላይ ከተሰጡት ምላሾች መገንዘብ እንደሚቻለዉ ሶስቱም መምህራን ተቀራራቢነት ባለዉ መልኩ መማሪያ መጽሀፉ የተለያዩ የሰዋስዉ መልመጃዎችን በማቅረብ ተማሪዎች እየሰሩ ልምምድ በማድረግ የቋንቋዉን ህግ እራሳቸዉ እንዲደርሱበት የሚያደርጉ አቀራረቦችን ማካተቱን ገልጸዋል።

በአጠቃላይ በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአቀራረብ መርህ እንዴት እንደተካተተ በተደረገዉ ፍተሻ በርካታ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ይህን የአቀራረብ መርህ ተከትለዉ መቅረባቸዉን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ይህም ከጠንካራ ጎን የሚጠቀስ ነዉ፡፡

### 4.1.2.3 ውጤት ተኮር የአቀራረብ ስልት

ይህ የአቀራረብ ስልት በታላሚው ቋንቋ መዋቅር ዙሪያ ባለው የቋንቋ ቅርጽ እና በቋንቋ መዋቅራዊ ህግጋትና ብያኔ ላይ ትኩረት እንደሚያደረግ በክለሳ ድርሳን ክፍል ለመጥቀስ ተሞክሯል፡፡በዚህም መሰረት በተተኳሪዎቹ መጻሕፍት ውስጥ ውጤት ተኮር በሆነ ዘዴ ከቀረቡ በርካታ ይዘቶች መካከል ለአብነት ያህል የተወሰኑትን እንመልከት፡-

### 4.1.2.3.1 የ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አብዛኛዎቹ የትምህርት ይዘቶች የቀረቡት ውጤት ተኮር የአቀራረብ ስልት ተከትለው ነው፡፡በአስረጂነት የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት ፡-

*አስረጂ 12.‹‹ወሰደ›› የሚለውን ግስ በምሳሌው መሰረት በተለያየ ቅርጽ አርቡ፡፡*

*ምሳሌ « ሰበረ »*

*ሰበርኩ ሰበርን ወዘተ /ገጽ፣67/*

በተጨማሪም በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ዉጤት ተኮር መርህን ተከትለዉ ከቀረቡ ሰዋስዋዊ መልመጃዎች መካከል የሚከተለዉ ይገኝበታል፡፡

አስረጂ 13. ‹‹በቀረበዉ ምሳሌ መሰረት ሠንጠረዡን አሟሉ፡፡»

| | *ቅጽል* | *ብዙ ቁጥር* | *እንስታይ ፆታ* |
|---|---|---|---|
| *ሀ* | *ጥቁር* | *ጥቁሮች* | *ጥቁሪቱ(ጥቁሯ)* |
| *ለ* | *ረጅም* | ------- | ----------- |
| *ሐ* | *ቀጭን* | --------- | ------------ |

*/ገጽ፣95/*

ሌላዉ ይህን አቀራረብ ተከትለዉ ከቀረቡት ይዘቶች መካከል የተጸዉኦ ስሞችን፣የወል ስሞችንና ግሶችን መለየት የተሰኘዉ ይዘት በሚከተለዉ መልኩ ቀርቧል፡፡

*አስረጂ 14.‹‹ከተዘረዘሩት ቃላት ውስጥ የተፃውኦ ስም፣ የወል ስሞችና ግሶች ተቀላቅለው ቀርበዋል፡፡ እየለያችሁ በደብተራችሁ ዘርዝሩ፡፡››*

*ለምሳሌ ተራራ አገዘ እመቤት ሜዳ /ገጽ፣118/*

ከላይ የተዘረዘሩትን አስረጂዎች ስንመለከት ተማሪዎች የቀረቡላቸዉን ምሳሌዎች ተመልክተዉ ቃላቱን በተናጠል እንዲተነትኑ የሚያዙ እንጂ እነዚህን ቅርጾች በአዉድ ዉስጥ

እንዲጠቀሙባቸዉ የሚያዙ ባለመሆናቸዉ ዉጤት ተኮር የአቀራረብ መርህን ተከትለዉ የቀረቡ ናቸዉ፡፡በመቀጠል ደግሞ ዉጤት ተኮር የአቀራረብ ስልትን ተከትለው ስነአገባብን ለማስተማር ከቀረቡት ይዘቶቸ መካከል የሚከተሉትን እንመልከት፡-

*አስረጂ 15.«የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መሆናቸውን በመለየት በደብተራችሁ ፃፉ፡፡/ገጽ፣210/*

ከዚህ በተጨማሪም አዎንታዊና አሉታዊ ዓረፍተ ነገር አመሰራረትን በሚመለከት የቀረቡትን መልመጃዎች መመልከት ይቻላል፡፡

*አስረጂ 16.‹‹የሚከተሉትን አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች ወደ አዎንታ ለውጡ፡፡»*

*ምሳሌ ወደ ቤታችን ለመሄድ ታክሲ አያስፈልገንም፡፡*

*ወደ ቤታችን ለመሄድ ታክሲ ያስፈልገናል፡፡ /ገጽ፣218/*

*« የሚከተሉትን አዎንታዊ ዓረፍተ ነገሮች ወደ አሉታ ለውጡ፡፡»*

*ምሳሌ ዳዊት የገዛዉ መጽሐፍ በጣም ዉድ ነዉ፡፡*

*ዳዊት የገዛዉ መጽሐፍ በጣም ዉድ አይደለም፡፡ /ገጽ፣219*

ከቀረቡት አስረጂዎች በተጨማሪ በተተኳሪው መጽሐፍ ውስጥ ውጤት ተኮር የአቀራረብ መርህን ተከትለዉ ከተካተቱት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መካከል የወልና የተፃውኦ ስሞችን መለየት ገጽ /19/፣መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮችን መለየት ገጽ /32/፣ቅጽሎችን መለየት ገጽ /87/---እና ሌሎችም ይጠቀሳሉ፡፡

ከላይ አስረጂዎችን በመጥቀስ ለማሳየት እንደተሞከረዉ በተጠኘዉ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ከቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል በርካታ ይዘቶች የቀረቡት ዉጤት ተኮር የአቀራረብ መርህን ተከትለዉ ነዉ፡፡ይህን አቀራረብ በተመለከተ ለመምህራን ከቀረበ መጠይቅ የተገኙ ምላሾች ቀጥሎ እንመልከት፡-

ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ ቁጥር 3 በመማሪያ መጽሀፉ ዉስጥ ከቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ዉስጥ የቋንቋዉን ሰዋስዋዊ ስርዓት ብቻ የሚያሳዉቁ አቀራረቦች ይገኛሉ፡፡

መምህር 1‹‹በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ከቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካካል ብዙዎቹ የቋንቋዉን ሰዋስዋዊ ስርዓት ብቻ በሚያሳዉቁ መልኩ የተካተቱ መሆናቸዉን አስተዉያለሁ፡፡››በማለት አስረድተዋል፡፡

*መምህርት 2‹‹እኔ እንዳስተዋልኩት አብዛኞዎቹ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች የታላሚዉን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ቅርጽ የሚተነትኑ እንጂ ተማሪዎችን ለተግባቦት የሚጋብዙ ባለመሆናቸዉ እንደደካማ ጎን አይቸዋለሁ፡፡››በማለት መልሰዋል፡፡*

*መምህርት 3 ደግሞ‹‹በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የቀረቡ አብዛኞዎቹ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በቋንቋዉ ቅርጽ ላይ የሚያነጣጥሩ በመሆናቸዉ የቋንቋዉን ሰዋስዋዊ ስርዓት እንጂ የተግባቦት ልምምድ ላይ የሚያተኩሩ አለመሆናቸዉን ተገንዝቤያለሁ፡፡››በማለት አስተያየታቸዉን ሰጥተዋል፡፡*

በአጠቃላይ በ5ኛ ክፍል *መማሪያ መጽሀፍ* ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ለዉጤት ተኮር አቀራረብ የሰጡት ትኩረት ምን እንደሚመስል በተደረገዉ ፍተሻ አብዛኞዎቹ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በዚህ የአቀራረብ *መርህ* ላይ *ያተኮሩ* መሆናቸዉን በተደረገዉ ፍተሻና ለመምህራን ከቀረበ መጠይቅ ከተገኙ ምላሾች *መረዳት* ተችሏል፡፡

#### 4.1.2.3.2 የ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ *መማሪያ* መጽሐፍ

በስድስተኛ ክፍል *መማሪያ መጽሐፍ* ውስጥ ከቀረቡት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መካከል አብዛኞዎቹ ይዘቶች ውጤት ተኮር የአቀራረበ ስልትን ተከትለው የቀረቡ ናቸዉ፡፡ለአስረጂነት የሚከተሉትን *እንመልከት፡-አስረጂ 17.‹‹በሚቀጥለዉ ባሉ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በምሳሌው መሰረት ቅጽል የሆኑትን ቃላት ከስር አስምሩባቸው፡፡»*

*ምሳሌ፡-1.ክብ ጫወታ መጫወት እወዳለሁ፡፡*

*2.ወጣቶች በበዓላት ጊዜ አዳዲስ ልብሶችን ይለብሳሉ፡፡ /ገጽ፣73/*

በተጨማሪም *አስረጂ 18.‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ መስተኣምር የሆኑትን ቃላት ከስራቸዉ አስምሩ፣መጣኝና ደረጃ አመልካች መሆናቸዉንም ግለጹ፡፡››*

*ምሳሌ፡-ሀ.ዘገየ አንድ ጥቁር በግ ገዛ፡፡*

*ለ.እኔ ለቤተሰቦቹ ሦስተኛ ልጅ ነኝ፡፡ /ገጽ፣80/*

*አስረጂ19.«በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ባለቤት፣ተሳቢና ግስ የሆኑት ቃላትን ለይታችሁ ፃፉ፡፡»ገጽ፣108/*

*አስረጂ 20.ግስን በመደብ፣በፆታና በቁጥር ማርባት በሚል ንዑስ ርዕስ ስር «በምሳሌው መሰረት ሌሎችን ቃላት በሠንጠረዥ ውስጥ ፃፍ»የሚል ትዕዛዝ ይገኛል፡፡ /ገጽ፣151/*

ከላይ የቀረቡትን አስረጂዎች ስንመለከት ዉጤት ተኮር የአቀራረብ መርህን ተከትለዉ የቀረቡ በመሆናቸዉ ትኩረታቸዉ በቋንቋዉ መዋቅራዊ ህግጋት ላይ ነዉ፡፡ይህን የአቀራረብ መርህ

Batstone(1994)‹‹ይህ የአቀራረብ መርህ በታላሚዉ ቋንቋ መዋቅር ዙሪያ ባለዉ የቋንቋ ቅርጽ የሚያተኩር ነዉ፡፡››ሲሉ ይገልጹታል፡፡በመሆኑም ከላይ የቀረቡትን መልመጃዎች ስንመለከት ተማሪዎች ከቃል ክፍሎች ዉስጥ ቅጽልን፣መስተኣምርንና ቁጥሮችን ለይተዉ እንዲያሳዩ ይጠበቃል፡፡ቀጥለን ደግሞ ዓረፍተ ነገር አመሰራረት በተመለከተ በውጤት ተኮር ስልት የቀረቡት መልመጃዎች እንመልከት፡-

*አስረጂ 21.«የሚከተሉትን ሐተታዊ ዓረፍተ ነገሮችን አሉታዊ ወይም አዎንታዊ በማለት በምክንያት ለዩ፡፡ /ገጽ፣58/*

*አስረጂ 22.«የሚከተሉትን አዎንታዊ ዐረፍተ ነገሮችን ወደ አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች በመለወጥ ፃፉ፡፡» /ገጽ፣65/*

ከእነዚህ በተጨማሪ በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከተካተቱት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መካከል የወል ስም፣የተጸውኦ ስምና የዋህ ሀላፊ ግስን መለየት ገጽ/21/፣ሐተታዊ (አዎንታዊና አሉታዊ) ዓረፍተ ነገሮችን መለየት ገጽ/51/ ፣ ቅጽልንና መስተዓምርን መለየት ገጽ/88/፣ የስምን ሙያ መለየት ገጽ/95/፣ ተዉሳከ ግስንና እምርነት አመልካች ቅጥያዎችን መለየት ገጽ/143/፣ ባለቤትንና ተሳቢን መለየት ገጽ/233/---እና ሌሎችም ዉጤት ተኮር በሆነ ስልት የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ናቸዉ፡፡በዚህ የአቀራረብ መርህ ዙሪያ ለመምህራን የቀረበላቸዉን ጥያቄና የተሰጡ ምላሾችን ቀጥለን እንመልከት፡-

ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ ቁጥር 3 በመማሪያ መጽሐፉ ዉስጥ ከቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል የቋንቋዉን ሰዋስዋዊ ስርዓት ብቻ የሚሳዉቁ አቀራረቦች ይገኛሉ፡፡

መምህር 1‹‹በዚህ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የተካተቱ በርካታ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች የቀረቡት የቋንቋዉን ስርዓት በማስተማር ላይ በሚያተኩር መልኩ ነዉ፡፡ይህም ማለት ከግማሽ በላይ ይዘቶች ዉጤት ተኮር የአቀራረብ መርህ ላይ ያተኮሩ ናቸዉ ማለት ይቻላል፡፡››በማለት አስረድተዋል፡፡

መምህርት 2 ደግሞ‹‹በርግጥ በርካታ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጽሀፉ ዉስጥ ተካትተዉ እንደሚገኙ አስተዉያለሁ፡፡ነገር ግን ከእነዚህ ይዘቶች ዉስጥ ብዙዎቹ የቀረቡት የቋንቋዉን ስርዓት በሚያስተምር መልኩ እንጂ ተግባቦት ላይ አይደለም፡፡››ሲሉ ምላሻቸዉን ሰጥተዋል፡፡

መምህርት 3‹‹የቋንቋዉን ሰዋስዋዊ ስርዓት የሚያሳዉቁ ይዘቶች መማሪያ መጽሀፉ ዉስጥ መካተታቸዉን አስተዉያለሁ፡፡››በማለት መልሳቸዉን ሰጥተዋል፡፡

በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ በርካታ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ዉጤት ተኮር የአቀራረብ መርህን ተከትለዉ የቀረቡ መሆናቸዉን ከመምህራኑ ከተገኙ ምላሾች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ስንመለከተዉ የ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ለዉጤት ተኮር የአቀራረብ መርህ የሰጠዉ ትኩረት ምን እንደሚመስል በተደረገዉ ፍተሻ በተጠኘዉ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ በርካታ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች የቀረቡት ዉጤት ተኮር የአቀራረብ መርህን ተከትለዉ መሆኑን በሰነድ ፍተሻ ከተገኘዉ ዉጤትና ከመምህራን ከተገኙ ምላሾች መረዳት ተችሏል፡፡

### 4.1.2.4 ሂደት ተኮር አቀራረብ

ሂደት ተኮር የአቀራረብ መርህ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ መዋቅራዊ ህጎች ተገንዝበው በቋንቋው እንዲገለገሉ የሚያስችል መሆኑን በክለሳ ድርሳናት ክፍል ለመጥቀስ ተሞክሯል፡፡ይሁን እንጂ በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ሂደት ተኮር በሆነ ስልት የቀረቡት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ጥቂቶች ናቸው፡፡

#### 4.1.2.4.1 የ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ ከተካተቱት ይዘቶች መካከል ሂደት ተኮር በሆነ ስልት የቀረቡትን እንመልከት፡-አስረጂ 23‹‹ገዛ የሚለዉን ግስ በተለያየ ቅርጽ እያስተካከላችሁ የተጓደሉትን ዓረፍተ ነገሮች በምሳሌዉ መሰረት አሟሉ፡፡››ምሳሌ፡-ገዛ

1.እሷ ሁለት ኪሎ ሙዝ------

እሷ ሁለት ኪሎ ሙዝ ገዛች፡፡ /ገጽ፣74/

*አስረጂ 24‹‹ቀጥሎ የተዘረዘሩት የወል ስሞች፣የተጸውዖ ስሞችና ግሶች በተገቢ ቦታቸው በማስገባት ዓረፍተ ነገሮቹን አሟሉ፡፡ /ገጽ፣127/*

*አስረጂ 25«ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ ያሉትን መጣኝ ቁጥሮች፣ደረጃ አመልካች ቁጥሮችና ቅጽሎች በማቀናጀት የተጓደሉት ዓረፍተ ነገሮች አሟልታችሁ በደብተራችሁ ፃፉ፡፡ (በአንድ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ከአንድ ቅጽል በላይ መጠቀም ትችላላችሁ፡፡››) /ገጽ፣171/*

*አስረጂ 26‹‹ቅጽሎችን ፣መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮችን ተጠቅማችሁ 6 ዓረፍተ ነገሮችን ጻፉ፡፡›› /ገጽ፣172/*

በተጨማሪም ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምንባብ በማንበብ ከምንባቡ ውስጥ ቅጽሎችን፣መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮችን ለይተው እንዲያወጡ የሚያዝ መልመጃ እንዲህ ሲል ቀርቧል፡፡

*አስረጂ 27«የፈረስ ሸርጥ(ሽምጥ) የውድድር ጫወታ ከሚለው ምንባብ ቅጽሎች፣መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮችን ለይታችሁ በደብተራችሁ ፃፉ። /ገጽ፣179/*

*ከዚህ በተጨማሪም ስለዓረፍተ ነገር አመሰራረት በሂደት ተኮር ስልት የቀረቡ መልመጃዎችን ስንመለከት አስረጂ 28«አምስት አምስት አዎንታዊና አሉታዊ ሃተታ ዓረፍተ ነገሮች መስርቱ።›› /ገጽ፣225/*

ከላይ የቀረቡትን አስረጂዎች ስንመለከት ተማሪዎች የቀረቡላቸዉን የቃል ክፍሎች በመጠቀም የተጓደሉትን ዓረፍተ ነገሮች እንዲያሟሉና ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ የሚያዙ መልመጃዎች ናቸዉ። ይህ አቀራረብ ተማሪዎች የቋንቋዉን ቅርጾች ከተግባቦት ጋር በማቀናጀት እንዲለማመዷቸዉና በቋንቋዉ እንዲገለገሉ የሚያግዙ በመሆናቸዉ የቀረቡት ሰዋስዋዊ መልመጃዎች ሂደት ተኮር አቀራረብን የተከተሉ ናቸዉ።

ሂደት ተኮር የአቀራርብ ስልትን አስመልክቶ በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሀፍ ለሚያስተምሩ መምህራን የቀረበ ጥያቄና የተገኙ ምላሾች በሚከተለዉ መልኩ ቀርበዋል።

ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ ቁጥር 4. በመማሪያ መጽሐፉ ዉስጥ ከተካተቱት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል ተማሪዎች በቋንቋዉ እንዲገለገሉ ወይም የሀሳብ ልዉዉጥ እንዲያደርጉ የሚያስችሉ አቀራረቦች አሉ።

መምህር 1‹‹እንደ እኔ አስተያየት በመማሪያ መጽሀፉ ዉስጥ ይህን አቀራረብ የተከተሉ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በጣም ጥቂት ናቸዉ።››በማለት ሲመልሱ

መምህርት 2 ደግሞ‹‹እኔ እንዳስተዋልኩት ተማሪዎችን ለተግባቦት የሚያግዙ የሰዋስዉ መልመጃዎች የሉም።››በማለት ምላሻቸዉን ሰጥተዋል።

መምህርት 3‹‹በመማሪያ መጽሀፉ ከቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል ጥቂት ይዘቶች ተማሪዎች በቋንቋዉ እንዲገለገሉ የሚያስችሉ መሆናቸዉን ተመልክቻለሁ።››በማለት መልሰዋል።

ከመምህራኑ ከተገኙ ምላሾች መረዳት እንደሚቻለዉ ሁለቱ መምህራን ተቀራራቢ በሆነ መልኩ በመማሪያ መጽሀፉ ዉስጥ ጥቂት ይዘቶች ተማሪዎች በቋንቋዉ እንዲገለገሉ ወይም የሀሳብ ልዉዉጥ እንዲያደርጉ በሚያስችሉ መልኩ መቅረባቸዉን ገልጸዋል።

በአጠቃላይ በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶችን በመፈተሽ ከተገኘዉ ዉጤትና ከመምህራን ከተገኙ ምላሾች መረዳት እንደሚቻለዉ በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ሂደት ተኮር የአቀራረብ መርህ ተካትቶ የቀረበ ቢሆንም ከዉጤት ተኮር የአቀራረብ መርህ ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛዉን ቁጥር ይይዛል።Ur (1988) የሰዋስዉ

ትምህርት ይዘቶች የታላሚዉን ቋንቋ የተለያዩ ክፍሎች ወይም አካለት ቅርፅ፣ፍቺና አዉዳዊ አጠቃቀም በተመጣጠነ መልኩ ማስተማር እንዳለባቸዉ ይገልጻሉ፡፡ከዚህ አንጻር ስናየዉ ተተኳሪዉ መማሪያ መጽሀፍ ለሂደት ተኮር አቀራረብ የሰጠዉ ትኩረት አነስተኛ ነዉ፡፡ነገር ግን ይህ የአቀራረብ መርህ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ የታላሚዉን ቋንቋ መዋቅራዊ ፍቺና አጠቃቀም ተገንዝበዉ በቋንቋዉ እንዲገለገሉ የሚያስችል ስልት በመሆኑ ተመራጭ ያደርገዋል፡፡

#### 4.1.2.4.2 የ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

በተተኳሪው መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ ሂደት ተኮር በሆነ ስልት ከቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መካከል የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት፡-‹‹ተዉሳከ ግስን፣እምርነት አመልካች ቅጥያንና መደብን መለየት» በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር የቀረበውን ትዕዛዝ ስንመለከት፡-

*አስረጂ 28«የሚከተሉትን ተውሳከ ግሶች በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ስሩ፡፡» /ገጽ፣157/*

*በተመሳሳይ መልኩም ‹‹ጠቋሚ መስተዓምርንና ወደረኛ መስተጻምርን መለየት››በሚል ይዘት ስር የሚከተለዉ መልመጃ ይገኛል፡፡*

*አስረጂ 29«የሚከተሉትን ጠቋሚ መስተኣምሮች በመጠቀም በምሳሌው መሰረት ዓረፍተ ነገር ስሩ፡፡»*

*ምሳሌ፡-1.ያች ልጅ ጎበዝ ተማሪ ናት፡፡ያቺ የሚለዉ ጠቋሚ መስተዓምር ነዉ፡፡*

*2. ይህ መጽሐፍ የራሴ ነዉ፡፡ይህ የሚለዉ ጠቋሚ መስተዓምር ነዉ፡፡ /ገጽ፣167/*

በተጨማሪም በአንቀጽ ውስጥ አያያዦችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ለማስተማር የቀረበውን መልመጃ ስንመለከት፡-አስረጂ *30‹‹የሚከተሉትን አያያዦች በተገቢው ቦታቸው በመጠቀም አንቀጹን የተሟላ አድርጉ፡፡» /ገጽ፣206/*

ከቀረቡት አስረጂዎች መረዳት እንደሚቻለዉ ተማሪዎች የቀረቡላቸዉን የቃል ክፍሎች በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ሰርተዉና አንቀጾችን አሟልተዉ እንዲያሳዩ የቀረቡ ናቸዉ፡፡ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ ተማሪዎች የቋንቋዉን ቅርጾች በመገልገል ተግባራዊ ልምምድ እያደረጉ ቋንቋዉን እንዲጠቀሙበት የሚጋብዙ አቀራረብ በመሆናቸዉ ሂደት ተኮር የአቀራረብ መርህን የተከተሉ ናቸዉ፡፡

በመቀጠል ደግሞ ሂደት ተኮር የአቀራረብ መርህን በሚመለከት በተጠኘዉ መማሪያ መጽሀፍ ለሚያስተምሩ መምህራን ከቀረበዉ መጠይቅ የተገኙ መልሶችን እንመልከት፡-

ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ ቁጥር 4.በመማሪያ መጽሐፉ ዉስጥ ከተካተቱት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል ተማሪዎች በቋንቋዉ እንዲገለገሉ ወይም የሀሳብ ልዉዉጥ እንዲያደርጉ የሚያስችሉ አቀራረቦች አሉ፡፡

መምህር 1‹‹በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ከቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል ጥቂቶቹ ብቻ ተማሪዎች በቋንቋዉ እንዲገለገሉ በሚያስችሉ መልኩ መካተታቸዉን አስተዉያለሁ፡፡››በማለት ሲያስረዱ

መምህርት 2 በተጨማሪ‹‹እንደኔ አስተያየት በዚህ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ አብዛኛዎቹ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች የቋንቋዉን ቅርጽ እንዲተነትኑ እንጂ በነዚህ ቅርጾች እንዲገለገሉ በሚያስችሉ መልኩ የቀረቡ አይደሉም፡፡››በማለት መልሰዋል፡፡

መምህርት 3 ደግሞ‹‹ተማሪዎች በቋንቋዉ ቅርጾች እንዲገለገሉ የሚያዙ መልመጃዎች በመማሪያ መጽሀፉ ዉስጥ አልፎ አልፎ እንደተካተቱ ተመልክቻለሁ፡፡››በማለት ምላሻቸዉን ሰጥተዋል፡፡

ጠቅለል አድርገን ስንመለከተዉ ተተኳሪዉን መማሪያ መጽሐፍ በመፈተሽና ለመምህራን ከቀረበዉ መጠይቅ ከተገኙ ምላሾች መገንዘብ እንደተቻለዉ በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት አብዛኛዎቹ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ውጤት ተኮር ስልትን ተከትለው የቀረቡ ሲሆን ሂደት ተኮር ስልትን ተከትለው የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ስንመለከት ግን በቁጥር አነስተኛ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ጥናቱ ከሚመልሳቸዉ ጥያቄዎች መካከል በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ ተመርጠዉ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከአቀራረባቸዉ አንጻር ለቋንቋዉ ቅርፅ፣ፍቺና አጠቃቀም የሰጡት ትኩረት ምን ይመስላል?የሚል ነዉ፡፡በዚህም ጥናቱ የሚከተለዉን ምላሽ ሰጥቷል፡፡ይኸዉም በአጠቃላይ በደቡብ ክልል ስራ ላይ ባሉ የ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብን ስንፈትሽ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ መርህ ያልተካተተ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የቀረቡት ይዘቶች ቁጥር በርካታ መሆናቸዉን መረዳት ተችሏል፡፡ ዉጤት ተኮር የአቀራረብ ስልት ተከትለው የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልትን ተከትለው ከቀረቡት ይዘቶች በርካታውን ቁጥር እንደሚይዙ

መመልከት ተችሏል፡፡በዚህም ተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ከሰዋስዉ ትምህርት አቀራረብ መርህ አንጻር ሲታዩ ጠንካራ ጎናቸዉ የሚያመዝን መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

### 4.1.3 በመማሪያ መጽሀፍት ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት

### 4.1.3.1 ተከታታይነት

ተከታታይነት በአንድ የክፍል ደረጃ ወይም በተከታታይ የክፍል ደረጃዎች የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች ተደጋግመው መቅረባቸውን የሚመለከት መሆኑን በክለሳ ድርሳን ክፍል ለመጥቀስ ተሞክሯል፡፡ በዚህም መሰረት ተተኳሪ በሆኑት የ5ኛና 6ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ምን ያህል ተከታትለዉ እንደቀረቡ ለማየት እንሞክራለን፡፡

#### 4.1.3.1.1 የ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች እየተከታተሉ መቅረባቸዉን ተተኳሪዉን መማሪያ መጽሀፍ በመፈተሽ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ይኸዉም ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ይዘቱን በቀላሉ እንዲያስታዉሱት የሚያግዝ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ቀጥለን ደግሞ ተተኳሪ በሆነዉ በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ክትትሎሽ ምን እንደሚመስል በሚከተለዉ ሰንጠረዥ ለማየት እንሞክር፡-

**ሰንጠረዥ 4.3 በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የክትትሎሽ ሁኔታ**

| አብይ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | ንዑሳን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | የሚገኝበት ገጽ | የድግግሞሽ መጠን | |
|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ስነ ምዕላድ | የተጸውዖ ስም፣የወል ስሞችና ግስን መለየት | 7፣13፣19፣111፣118፣127 | 6 | 10% |
| | መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮች | 26፣32፣39 | 3 | 5% |
| | ኢ-ሳቢ ግሶች | 48፣54፣60 | 3 | 5% |
| | ሳቢ ግሶች | 67፣74፣80 | 3 | 5% |
| | ቅጽልን መለየት | 87፣95፣103፣163፣171፣179 | 6 | 10% |
| | ስም እንደባለቤት | 138፣144፣154 | 3 | 5% |
| | ግሳዊ ሐረግን መለየት | 188፣195፣201 | 3 | 5% |
| ስነ አገባብ | በቃላትና በሐረጋት ዓረፍተ ነገር መመስረት | 37፣108፣124፣150፣159፣201 | 6 | 10% |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በአንቀጽ ውስጥ የተጓደሉ ቃላትን ማሟላት | 142፣177 | 2 | 3% |
| | አዎንታዊና አሉታዊ ሐተታ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረትና መለየት | 210፣218፣225 | 3 | 5% |
| ስነ ፍቺ | የቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺ | 4፣24፣31፣51፣58፣72፣93፣100፣134፣168፣184፣193 | 12 | 20% |
| | የቃላትና ሐረጋት ተቃራኒ ፍቺ | 111፣17፣44፣84፣199 | 5 | 8% |
| | የቃላትና ሐረጋት አውዳዊ ፍቺ | 64፣78፣115፣199 | 4 | 7% |
| | ቃላት ከምንባቡ ውጪ ያላቸው ፍቺ | 206 | 1 | 2% |
| | | ድምር | 60 | 100% |

ከላይ በሠንጠረዡ እንደቀረበዉ በተተኳሪው 5ኛ ክፍል *መማሪያ መጽሐፉ* ውስጥ በአስር ምዕራፎች ከቀረቡት አስራ አራት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ዉስጥ አስራ ሶስት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከሁለት እስከ አስራ ሁለት ጊዜ ተደጋግመዉ የቀረቡ ሲሆን አንድ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘት ግን ምንም ሳይደገም የቀረበ መሆኑን ለማየት ተሞክሯል፡፡በተጨማሪም ስነ ድምጽን የተመለከቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በተተኳሪዉ *መማሪያ መጽሀፍ* ዉስጥ ያለመካተታቸዉን በፍተሻዉ ተስተዉሏል፡፡

በ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ *መማሪያ መጽሀፍ* ዉስጥ ከተካተቱት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል የቃላትና ሀረጋት ተመሳሳይ ፍች የሚለዉ ይዘት አስራ ሁለት ጊዜ በምዕራፍ አንድ፣በምዕራፍ ሁለት፣ በምዕራፍ ሶስት ፣በምዕራፍ አራት ፣በምዕራፍ አምስት ፣በምዕራፍ ሰባት ፣በምዕራፍ ስምንትና ዘጠኝ በተለያዩ ገጾች ተደጋግሞ ቀርቧል፡፡ይዘቱ በመቶኛ ያለዉ ድርሻም ከጠቅላላዉ 20% ያህሉን ይሸፍናል፡፡ይህ ይዘት በተለያዩ ምዕራፎች ዉስጥ እንዴት ተከታትሎ እንደቀረበ የሚከተለዉን አስረጂ እንመልከት፡-

*አስረጂ 31.በምዕራፍ አንድ ‹‹በ ሀ ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺ ከ ለ ረድፍ እየመረጣችሁ በማዛመድ ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡››/ገጽ፣4/ በማለት የቀረበ ሲሆን በአስረጂ 32*

በምዕራፍ ሁለት ደግሞ‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ለተሰመረባቸዉ ቃላትና ሐረጋት ፍቺ ስጡ፡፡››/ገጽ፣24/ እና *በአስረጂ 33 ‹‹በ ሀ ረድፍ ለቀረቡት ቃላትና ሐረግ ተመሳሳይ ፍቻቸዉን በ ለ ረድፍ ካሉት ጋር አዛምዱ፡፡››/ገጽ፣31/ በማለት* ቀርቧል፡፡ተቀራራቢነት ባለዉ መልኩ

በምዕራፍ ሶስት ደግሞ አስረጂ 34 ‹‹ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ ዉስጥ ያላቸዉን ፍቺ ስጡ፡፡››/ገጽ፣51/ እና

*አስረጂ 35 ‹‹በ ሀ ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸዉን ከ ለ ረድፍ ካሉት በመምረጥ አዛምዱ፡፡››/ገጽ፣58/ በማለት ቀርቧል፡፡በምዕራፍ አራት ደግሞ አስረጂ 36 ‹‹ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምሳሌዉ መሰረት ተመሳሳይ ፍቻቸዉን ፈልጉ፡፡››/ገጽ፣72/ ሲል ተካትቷል፡፡በተጨማሪም*

በምዕራፍ አምስት *አስረጂ 37 ‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ የተሰመረባቸዉ ቃላት በምንባቡ መሰረትና ከምንባቡ ዉጪ ያላቸዉን ፍቺ ጻፉ፡፡››/ገጽ፣93/ እና አሰረጂ 38‹‹ቀጥሎ በሰንጠረዥ ዉስጥ የቀረቡትን ቃላት ከምንባቡ ዉስጥና ዉጪ ያላቸዉን ፍቺ ግለጹ፡፡››/ገጽ፣100/ በማለት ቀርቧል፡፡ተከታታይነት ባለዉ መልኩ በምዕራፍ ሰባት ደግሞ አስረጂ 39‹‹በሀ ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸዉን ከ ለ ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ፡፡››/ገጽ፣134/ ሲል ቀርቧል፡፡በምዕራፍ ስምንት ደግሞ አስረጂ 40‹‹ቀጥሎ በሳጥን ዉስጥ የቀረቡትን ቃላት ከፍቻቸዉ ጋር በምሳሌዉ መሰረት እያዛመዳችሁ በደብተራችሁ ጻፉ፡፡››/ገጽ፣168/የቀረበ ሲሆን በምዕራፍ ዘጠኝ ደግሞ አስረጂ 41‹‹በምንባቡ ዉስጥ የተሰመረባቸዉን ቃላትና ሀረጋት የምንባቡን ሀሳብ በማይቀይሩ ተመሳሳይ ቃላትና ሐረጋት ተክታችሁ አንብቡ፡፡››/ገጽ፣184/እና አስረጂ 42«በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ የተሰመረባቸዉን ቃላትና ሐረጋት የሚተኩ ተመሳሳይ ቃላትና ሐረጋት ከቀረቡት አማራጮች መርጣችሁ ጻፉ፡፡»/ገጽ፣193/በማለት ቀርቧል፡፡*

ከላይ በአስረጂነት የቀረበዉ ይዘት በተለያዩ ምዕራፎች እየተከታተለ መቅረቡን ለማየት ሞክረናል፡፡ይህም ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ይዘቱን እንዳይረሱትና በቋንቋዉ እንዲካኑ የሚያደርግ በመሆኑ የተሻለ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘት አደረጃጀት ነዉ ማለት ይቻላል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ተደጋግመዉ የቀረቡት የተጸዉዖ ስም ፣የወል ስሞችና ግስን መለየት ፣ቅጽልን መለየትና ስነ አገባብን ለማስተማር ከቀረቡት ይዘቶች ደግሞ በቃላትና በሀረጋት ዐረፍተ ነገር መመስረት የተሰኙት ይዘቶች በእኩል መጠን ስድስት ስድስት ጊዜ ተደጋግመዉ የቀረቡ ሲሆን ከጠቅላላዉ በመቶኛ ያላቸዉ ድርሻም እያንዳንዳቸዉ 10% ነዉ፡፡ ሌላዉ ስነ ፍቺን ለማስተማር ከተካተቱት ይዘቶች መካከል የቃላትና ሀረጋት ተቃራኒ ፍቺ የተሰኘዉ ይዘት አምስት ጊዜ ተደጋግሞ የቀረበ ሲሆን ከጠቅላላዉ በመቶኛ ያለዉ ድርሻም 8% ነዉ፡፡ከእነዚህ ይዘቶች መካከል የተጸዉዖ ስም፣የወል ስሞችና ግስን መለየት የሚለዉን ይዘት ለአብነት እንመልከት፡-

*አስረጂ 43 በምዕራፍ አንድ ‹‹ቀጥሎ የቀረበዉን ሰንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጁ ፡፡የምታዉቋቸዉን የሰዉ፣የወንዝ፣የሀይቅ፣የቦታ ወይም የከተማ ስሞችን ባዘጋጃችሁት ሠንጠረዥ ዉስጥ ዘርዝሩ፡፡››/ገጽ፣7/ በማለት የቀረበ ሲሆን አስረጂ 44 ሆኖ የቀረበዉ ደግሞ በዚሁ ምዕራፍ ገጽ/13/ ‹‹ቀጥሎ የቀረበዉን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጁና የቤትና የዱር እንስሳትን የሚያመለክቱ የወል ስሞችን ዘርዝሩ፡፡››ሲል የቀረበዉ ነዉ፡፡በተጨማሪም በአስረጂ 45 ‹‹ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ስሞች የተጸዉዖ ወይም የወል ስም መሆናቸዉን ለይታችሁ በደብተራችሁ ሠንጠረዥ አዘጋጅታችሁ መድቡ፡፡››/ገጽ፣19/ በማለት ቀርቧል፡፡አስረጂ 46 በምዕራፍ ስድስት ደግሞ ‹‹የሚከተለዉን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ የተሰመረባቸዉ ቃላት የተጸዉዖ ስም፣የወል ስም ወይም ግስ መሆናቸዉን የ√ ምልክት በማድረግ ለዩ፡፡››/ገጽ፣111/ በማለት የቀረበ ሲሆን አስረጂ 47 በገጽ/118/ ደግሞ ‹‹ከተዘረዘሩት ቃላት ዉስጥ የተጸዉዖ ስም፣የወል ስሞችና ግሶች ተቀላቅለዉ ቀርበዋል፡፡እየለያችሁ በደብተራችሁ ዘርዝሩ፡፡››በማለት ሲቀርብ አስረጂ 48 በገጽ/127/ ላይ ‹‹ቀጥሎ የተዘረዘሩትን የወል ስሞች፣የተጸዎዖ ስሞችና ግሶች በተገቢ ቦታቸዉ በማስገባት ዓረፍተ ነገሩን አሟሉ፡፡››በማለት ቀርቧል፡፡*

ከላይ የቀረቡትን አስረጂዎች ስንመለከት ይዘቱ በምዕራፍ አንድና በምዕራፍ ስድስት ሶስት ጊዜ ተከታትሎ ቀርቧል፡፡ተከታታይነት በአንድ የክፍል ደረጃ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በዛዉ ክፍል በተለያዩ ምዕራፎች ተደጋግመዉ መቅረብን የሚመለከት መሆኑን Tayler(1949) እንደሚገልጹ በክለሳ ድርሳን ክፍል ለመጥቀስ ተሞክሯል፡፡ከዚህ አንጻር ስንመለከተዉ ይዘቱ የመታወስ ዕድሉ ከፍተኛ በመሆኑ መልካም የሚባል አደረጃጀት ነዉ፡፡ሌላዉ ተከታትለዉ በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ከቀረቡ የሰዋስዉ ይዘቶች መካከል በቃላትና ሐረጋት ዓረፍተነገር መመስረት ለማስተማር የቀረበዉ ይዘት ስድስት ጊዜ እየተከታተለ ቀርቧል፡፡ምን እንደሚመስል አስረጂ በማቅረብ ለማየት እንሞክር፡-

*አስረጂ 49 በምዕራፍ ሁለት ‹‹የሚከተሉት ቃላት በምንባቡ ዉስጥ ያላቸዉን ፍቺ ስጡና ዓረፍተ ነገር በመመስረት አሳዩ፡፡››/ገጽ፣37/ የቀረበ ሲሆን አስረጂ 50 በምዕራፍ ስድስት ደግሞ ‹‹በተሰመረባቸዉ ቃላትና ሐረጋት የዓረፍተ ነገሩን ሀሳብ የማይለዉጥ ሌላ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡››/ገጽ፣108/ ላይ ቀርቧል፡፡በዚሁ ምዕራፍ ገጽ/124/ ደግሞ ‹‹ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላትና ሐረጋት በተጓደሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ በማስገባት አሟሉ፡፡››በማለት ተከታትሎ የቀረበ ሲሆን አስረጂ 51 በምዕራፍ ሰባት ‹‹ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት ተመሳሳይ ፍቻቸዉን ከሰጣችሁ በኋላ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡››/ገጽ፣150/ በማለት ቀርቧል፡፡አስረጂ 52*

በምዕራፍ ስምንት ደግሞ ‹‹የተሰመረባቸዉን ቃላት በመጠቀም ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ፡፡››/ገጽ፣159/ ሲል *ቀርቧል፡፡አስረጂ 53 በምዕራፍ ዘጠኝ ደግሞ ‹‹የሚከተሉትን ግሶች በመጠቀም ዓረፍተ ነገር መስርቱና ግሳዊ ሀረጉን በእዝባር (/) አሳዩ፡፡››/ገጽ፣201/ በማለት እየተከታተለ ቀርቧል፡፡*

ከላይ ከቀረበዉ አስረጂ መረዳት እንደሚቻለዉ ይዘቱ በአምስት የተለያዩ ምዕራፎች እየተከታተለ ቀርቧል፡፡ይኸዉም ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ቅርጾችን በተገቢዉ ሁኔታ ከክፍል ዉጪ ለተግባቦት እንዲያዉሉት የሚያስችል በመሆኑ የተሻለ አደረጃጀት ነዉ ማለት ይቻላል፡፡በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አራት ጊዜ በመከታተል የቀረበዉ የሰዋስዉ ይዘት የቃላትና ሀረጋት አዉዳዊ ፍቺ ሲሆን በመቶኛ ያለዉ ድርሻ 7% መሆኑን በሰነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡የዚህን ይዘት አደረጃጀት ምን እንደሚመስል ቀጥሎ እንመልከት፡-

*አስረጂ 54 በምዕራፍ አራት ‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ለተሰመረባቸዉ ቃላትና ሐረጋት ዐዉዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡››/ገጽ፣64/ በማለት የቀረበ ሲሆን አስረጂ 55 በገጽ /*78/ *ደግሞ ‹‹የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሰረት ያላቸዉን ዐዉዳዊ ፍቺ በጹሁፍ ግለጹ፡፡››በማለት ቀርቧል፡፡አስረጂ 56 በምዕራፍ ስድስት ደግሞ ‹‹የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ዐዉዳዊ ፍቺ በጹሁፍ ግለጹ፡፡››/ገጽ፣115/ በማለት የተደራጀ ሲሆን አስረጂ 57 በምዕራፍ ዘጠኝ ገጽ/199/ ‹‹ለሚከተሉት ቃላት ዐዉዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡››በማለት እየተከታተለ ቀርቧል፡፡*

*ከላይ የቀረቡትን መልመጃዎች ስንመለከት ሰዋስዋዊ ይዘቱ በሶስት ምዕራፎች አራት ጊዜ እየተከታተለ ቀርቧል፡፡ይኸዉም ተማሪዎች* መልመጃዉን ሳይሰላቹ በመስራት ይዘቱን እንዳይረሱት ያደርጋል፡፡

በመቀጠልም ሶስት ሶስት ጊዜ ተከታትለዉ የቀረቡት ይዘቶች ስነ ምዕላድን ለማስተማር ከተካተቱት ይዘቶች መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮች፣ኢ-ሳቢ ግሶች፣ሳቢ ግሶች፣ስም እንደባለቤትና ግሳዊ ሀረግን መለየት የተሰኙት ይዘቶች ሲሆኑ ስነ-አገባብን ለማስተማር ከቀረቡት ይዘቶች መካከል አዎንታዊና አሉታዊ ሀተታ ዐረፍተ ነገሮችን መመስረትና መለየት የተባሉት ይዘቶች ናቸዉ፡እነዚህ ይዘቶች እያንዳንዳቸዉ በመቶኛ ያላቸዉ ድርሻ 5% ነዉ፡፡ከተጠቀሱት ይዘቶች መካከል መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮችን መለየት የተሰኘዉን ይዘት ለአብነት እንመልከት፡-

*አስረጂ 58 ይህ ይዘት በምዕራፍ ሁለት ‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮችን ለይታችሁ ጻፉ፡፡››/ገጽ፣26/ በማለት የቀረበ ሲሆን በገጽ /32/ ደግሞ ‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ያሉትን ቁጥሮች በምሳሌዉ መሰረት መጣኝ ወይም ደረጃ አመልካች*

*መሆናቸዉን በመለየት ጻፉ፡፡››በማለት ቀርቧል፡፡/አስረጂ 60/ በዚሁ ምዕራፍ ገጽ/39/ ላይ ‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮችን ለይታችሁ ተናገሩ፡፡››በማለት ተከታትሎ ቀርቧል፡፡/አስረጂ 61/፡፡*

*በመቀጠል ኢ-ሳቢ ግሶችን ለማስተማር የቀረቡ የሰዋስዉ ይዘቶች በመማሪያ መጽሀፉ ዉስጥ እንዴት እንደተደራጁ የሚያሳዩ አስረጂዎችን እንመለከታለን፡-አስረጂ 62 በምዕራፍ ሶስት ገጽ/48/ ‹‹ተኛ የሚለዉን ግስ በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ስሩ፡፡››በማለት የቀረበ ሲሆን በገጽ/54/ ደግሞ ‹‹በቅንፍ ዉስጥ ከቀረቡት ኢ-ሳቢ ግሶች መካከል ተስማሚዉን በመምረጥ ዓረፍተ ነገሩን አሟልታችሁ ጻፉ፡፡››ሲል ቀርቧል፡፡በዚሁ ምዕራፍ በገጽ/160/ ‹‹በሀ ስር የተዘረዘሩትን ጅምር ዓረፍተ ነገሮች ከለ ስር ከተዘረዘሩት ተስማሚ ግሶችን በመምረጥ አሟልታችሁ ጻፉ፡፡›› በማለት ተከታትሎ ቀርቧል፡፡/አስረጂ 64/፡፡*

ሌላዉ ሶስት ጊዜ ተከታትለዉ ከቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል ሳቢ-ግስ መለየት የተባለዉ ይዘት ሲሆን በተተኳሪዉ መጽሐፍ ዉስጥ በምን ዓይነት መልኩ ተከታትሎ እንደመጣ ቀጥሎ የቀረቡትን አስረጂዎች *እንመልከት፡-አስረጂ 65 በምዕራፍ አራት ገጽ /67/‹‹ወሰደ የሚለዉን ግስ በምሳሌዉ መሰረት በተለያየ ቅርጽ አርቡ፡፡››በማለት የቀረበ ሲሆን በገጽ /74/ ደግሞ ‹‹ገዛ የሚለዉን ግስ በተለያየ ቅርጽ እያስተካከላችሁ የተጓደሉትን ዓረፍተ ነገሮች አሟሉ፡፡››ሲል ቀርቧል፡፡/አስረጂ 66/፡፡ በተመሳሳይ ምዕራፍ በገጽ /80/ ደግሞ ‹‹በቅንፍ ዉስጥ ያሉትን ግሶች በተስማሚ ቅርጽ በመቀየር ዓረፍተ ነገሮቹን አስተካክላችሁ ጻፉ፡፡›› በማለት ቀርቧል፡፡/አስረጂ 67/፡፡*

ሁለት ጊዜ ተደጋግሞ የቀረበዉ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘት በአንቀጽ ዉስጥ የተጓደሉ ቃላትን ማሟላት የተሰኘ ከስነ አገባብ ጋር የተገናኘ መልመጃ ሲሆን ከጠቅላላዉ በመቶኛ ያለዉ ድርሻም 3% ነዉ፡፡ በተተኳሪዉ መጽሐፍ ሳይደገም የቀረበዉ የትምህርት ይዘት አንድ ብቻ ሲሆን ይኸዉም ቃላት ከምንባቡ ዉጪ ያላቸዉ ፍቺ የሚያስተምር ነዉ፡፡ከመቶኛ ያለዉ ድርሻም 2% ነዉ፡፡

ከላይ የቀረቡትን አስረጂዎች ስንመለከት በተጠኘዉ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ከቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል አብዛኛዎቹ ይዘቶች እየተከታተሉ የተደራጁ መሆናቸዉን ማስተዋል ይቻላል፡፡ቀጥለን ደግሞ በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሀፍ ለሚያስተምሩ መምህራን የይዘቶቹን ተከታታይነት አስመልክቶ ከቀረበ መጠይቅ የተገኙ ምላሾችን እንመልከት፡-

ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ ቁጥር 5.በመማሪያ መጽሐፉ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች ዉስጥ እየተከታተሉ ቀርበዋል፡፡

መምህር 1‹‹አዎ በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የተካተቱ አብዛኛዎቹ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች እየተከታተሉ የተደራጁ ናቸዉ፡፡››በማለት መልሰዋል፡፡

መምህርት 2‹‹በእርግጥ ብዙዎቹ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች እየተከታተሉ የቀረቡ ቢሆንም ጥቂት ይዘቶች ደግሞ አንድ ጊዜ ብቅ ብለዉ የጠፉም አሉ፡፡››በማለት አስረድተዋል፡፡

መምህርት 3 ደግሞ‹‹ከይዘቶች ተከታታይነት አንጻር ስናየዉ መማሪያ መጽሀፉ በጥሩ ሁኔታ የተደራጀ መሆኑን አስተዉያለሁ፡፡››በማለት ምላሻቸዉን ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ ከሰነድ ፍተሻዉ ከተገኘዉ ዉጤትና ከተማሪዎችና ከመምህራን ከተገኙት ምላሾች በመመርኮዝ በተተኳሪዉ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በተለያየ መጠን በተለያዩ ምዕራፎች እየተደጋገሙ መቅረባቸዉን ማስተዋል ተችሏል፡፡በዚህም በመማሪያ መጽሀፉ ከተካተቱት 14 የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል 13ቱ ማለትም (92.8%)ተደጋግመዉ መቅረባቸዉ መረዳት ተችሏል፡፡ ይኸዉም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ተከታታይነት ባለዉ መልኩ ከማደራጀት አንጻር መማሪያ መጽሀፉ ጠንካራ ጎን የሚስተዋልበት ቢሆንም የተወሰኑ ይዘቶች በአንድ ምዕራፍ ዉስጥ እየተከታተሉ መቅረባቸዉንም ማስተዋል ተችሏል፡፡

#### 4.1.3.1.2 የ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የቀረቡ በርካታ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች ዉስጥ እየተከታተሉ መቅረባቸዉን በሰነድ ፍተሻ መመልከት ተችሏል፡፡ቀጥሎ የቀረበዉም ሰንጠረዥ በተጠኘዉ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች የክትትሎሽን ሁኔታ ይመለከታል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.4 በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች የድግግሞሽ መጠን**

| የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በአብይ ክፍል ደረጃ | የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በንዑሳን ክፍል ደረጃ | የሚገኝበት ገጽ | የድግግሞሽ መጠን | |
|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ስነ ድምጽ | የቃላትን ፍደላት ማጥበቅና ማላላት | 155 | 1 | 2% |
| ስነ ምዕላድ | የተጸዉዖ፣የወል ስሞችና የዋህ ኃላፊ ግስን መለየት | 8፣15፣21 | 3 | 5% |
| | ባለቤት፣ተሳቢንና ማሰሪያ ግስን መለየት | 29፣95፣101፣108፣233 | 5 | 8% |
| | ስማዊ ሐረግና ግሳዊ ሐረግን መለየት | 35፣42 | 2 | 3% |
| | ቃላትን በማቃረን ማዛመድ | 46፣92 | 2 | 3% |
| | ቃላትንና ሐረጋትን በተመሳሳያቸው መተካት | 55፣85፣139፣172 | 4 | 7% |
| | ጥቅል ቃላትንና ሐረጋትን መዘርዘር | 4፣70፣229 | 3 | 5% |
| | ቅጽልንና መስተዓምርን መለየት | 73፣88 | 2 | 3% |
| | መጣኝና ደረጃ አመልካች መስተዓምርን መለየት | 80 | 1 | 2% |
| | ምድብ ተውላጠ ስምን፣ አገናዛቢ ተውላጠ ስምና ዘርፍን መለየት | 118፣126፣135 | 3 | 5% |
| | ተውሳከ ግስንና እምርነት አመልካች ቅጥያዎችን መለየት | 143፣157 | 2 | 3% |
| | ግስን በመደብ፣በጾታና በቁጥር ማርባት | 147 | 1 | 2% |
| | ጠቋሚ መስተዓምርና ወደረኛ መስተፃምርን መለየት | 167፣175፣183 | 3 | 5% |
| | ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ተሳቢን መለየት | 216፣224 | 2 | 3% |
| ስነ አገባብ | ሐተታዊ(አዎንታዊና አሉታዊ)ዓረፍተ ነገሮችን መለየት | 51፣58፣65 | 3 | 5% |
| | ቃላትን በተገቢ ዐውድ በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን ማሟላት | 19 | 1 | 2% |
| | ቃላትን በተገቢ ዐውድ በመጠቀም አንቀጽን ማሟላት | 147 | 1 | 2% |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | አያያዥን በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን ማሟላት | 191፣198 | 2 | 3% |
| | በአንቀጽ ውስጥ አያያዥን መጠቀም | 206 | 1 | 2% |
| ስነ ፍቺ | ለቃላትና ሐረጋት ዐውዳዊ ፍች መስጠት | 12፣26፣78፣99፣106፣114፣124፣188፣202፣212፣220 | 11 | 18% |
| | ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች መስጠት | 32፣40 | 2 | 3% |
| | ቃላት ከምንባብ ውጪ ያላቸውን ፍች ማሳየት | 63 | 1 | 2% |
| | ለቃላትና ሐረጋት ፍች መስጠት | 132፣180 | 2 | 3% |
| | ቃላትና ሐረጋትን ከሁኔታዎች ጋር በማዛማድ ፍች መስጠት | 164 | 1 | 2% |
| | በፍች ልዩ የሆነውን ቃል መለየት | 195 | 1 | 2% |
| | | ድምር | 60 | 100% |

ከላይ በሰንጠረዡ እንደተመለከቱት በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከቀረቡት ሃያ አምስት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል አስራ ስድስት የሚሆኑት ከሁለት እስከ አስራ አንድ ጊዜ ተደጋግመዉ የቀረቡ ሲሆን ምንም ሳይደገሙ አንድ ጊዜ ብቻ የቀረቡ ደግሞ ዘጠኝ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ናቸዉ፡፡በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል በከፍተኛ ደረጃ የድግግሞሽ መጠን የሚታይበት ስነ ፍቺን ለማስተማር የቀረበዉ ለቃላትና ሀረጋት ዐዉዳዊ ፍቺ መስጠት ሲሆን ይዘቱ አስራ አንድ ጊዜ ተደጋግሞ ቀርቧል ፡፡ይኸዉም በመቶኛ ያለዉ ድርሻ ከጠቅላላዉ 18% ያህሉን ይሸፍናል ፡፡ይህ ይዘት በመማሪያ መጽሐፉ ዉስጥ በምን አይነት መልኩ ተደራጅቶ እንደቀረበ የሚከተሉትን አስረጂዎች እንመልከት፡-

*አስረጂ 68 ፡-በምዕራፍ አንድ ገጽ/12/‹‹ለተሰመረባቸዉ ቃላት ዐዉዳዊ ፍቺ በጹሑፍ ግለጹ፡፡››በማለት የቀረበ ሲሆን በምዕራፍ ሁለት ገጽ/26/ ‹‹ለሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገር በመስራት ዐዉዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡››በማለት ቀርቧል፡/አስረጂ 69/፡፡በተጨማሪም በምዕራፍ አራት ገጽ/78/ ‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ለተሰመረባቸዉ ቃላትና ሐረጋት ዐዉዳዊ ፍቺ በጹሑፍ ስጡ፡፡››በማለት ተደራጅቷል፡/አስረጂ 70/፡፡በምዕራፍ አምስት ገጽ/99/ ደግሞ ‹‹በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገር በመስራት ዐዉዳዊ ፍቻቸዉን አሳዩ፡፡››በማለት ቀርቧል፡/አስረጂ 71/፡፡በዚሁ ምዕራፍ ገጽ/106/ ‹‹ለሚከተሉት ቃላት ዐዉዳዊ ፍቻቸዉን በጹሑፍ ስጡ፡፡››በማለት* ተከታትሎ

*ቀርቧል።/አስረጂ 72/።በምዕራፍ ስድስት ገጽ/114/ ላይ ‹‹ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሰረት ዐዉዳዊ ፍቻቸዉን ጻፉ።››ሲል የቀረበ ሲሆን በገጽ/124/ ደግሞ ‹‹ለሚከተሉት ቃላት ጓደኞቹ በሚለዉ ምንባብ ዉስጥ ያላቸዉን ዐዉዳዊ ፍቺ ከጻፋችሁ በኃላ በምንባቡ ካላቸዉ ፍቺ ዉጪ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸዉ።››በማለት ቀርቧል።/አስረጂ 73/።በምዕራፍ ዘጠኝ ገጽ/188/ላይ ‹‹ከምንባቡ ዉስጥ ዘጠኝ ቁልፍ ቃላትንና ሐረጋትን ለይታችሁ በማዉጣት ዐዉዳዊ ፍቻቸዉን ግለጹ።››ሲል የቀረበ ሲሆን በገጽ/202/ ደግሞ ‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ለተሰመረባቸዉ ቃላትና ሐረጋት ዐዉዳዊ ፍቺ ስጡ።››በማለት ቀርቧል።/አስረጂ 74/።በምዕራፍ አስር ገጽ/212/ ‹‹ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሰረት ዐዉዳዊ ፍቻቸዉን በጽሑፍ ግለጹ።››ሲል የቀረበ ሲሆን በገጽ /220/ ደግሞ‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ለተሰመረባቸዉ ሐረጋት ተመሳሳያቸዉን ጻፉ።››በማለት እየተከታተለ ቀርቧል።/አስረጂ 75/።*

በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ በተደጋጋሚ እየተከታተለ የቀረበዉ ይዘት ለቃላትና ሐረጋት ዐዉዳዊ ፍቺ መስጠት የሚለዉ ይዘት መሆኑን ከላይ ለመግለጽ ተሞክሯል። ተማሪዎች የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶችን በቀላሉ ለመረዳት የሚያስቸግራቸዉ በመሆኑ በመማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ በተለያዩ ምዕራፎች እየተደጋገሙ መቅረብ እንዳለባቸዉ LarsenFreeman(1991) አበክረዉ እንደሚገልጹ በክለሳ ድርሳናት ክፍል ተጠቅሷል።በመሆኑም በአስረጂነት የቀረበዉ ይዘት ከሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት መርህ አንጻር ጠንካራ ጎን ይስተዋልበታል።

በሁለተኛ ደረጃ ተደጋግሞ የቀረበዉ ደግሞ ከስነ ምዕላድ ጋር በተገናኘ የተካተተዉ ባለቤት፣ተሳቢና ማሰሪያ ግስን መለየት ነዉ።ይዘቱ በተለያዩ ገጾችና ምዕራፎች ለአምስት ጊዜ ተደጋግሞ የቀረበ ሲሆን ከጠቅላላዉ በመቶኛ ያለዉ ድርሻም 8% ነዉ።የዚህን ይዘት አደረጃጀት ምን እንደሚመስል ቀጥሎ ከቀረቡት አስረጂዎች እንመልከት፡-

*አስረጂ 76፡-በምዕራፍ ሁለት ገጽ /29/ ‹‹ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ባለቤትና ማሰሪያ ግስን ለይታችሁ ጻፉ።››ሲል የቀረበ ሲሆን በምዕራፍ አምስት ገጽ/95/ ‹‹ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ሰዋስዋዊ ባለቤት የሆኑትን ስሞች ከስራቸዉ በማስመር ለዩ።››በማለት መቅረቡ ይስተዋላል።/አስረጂ 76/።በተጨማሪም በዚሁ ምዕራፍ ገጽ/101/ ‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ባለቤት፣ተሳቢና ግስ የሆኑትን ቃላት ለይታችሁ ጻፉ።››ሲል የቀረበ ሲሆን በገጽ/108/ ‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ባለቤት ፣ተሳቢ ያላቸዉዓረፍተ ነገሮች መስርቱ።››በማለት ቀርቧል።/አስረጂ 77/።*

*በምዕራፍ አስር ገጽ /233/ ‹‹በሚከተሉት ቃላት ባለቤት፣ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ተሳቢ ያሏቸዉ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡››በማለት እየተከታተለ ተደራጅቷል፡፡/አስረጂ 78/፡፡*

ይህ ይዘት በመማሪያ መጽሐፉ ዉስጥ አምስት ጊዜ እየተደጋገመ መቅረቡን ከቀረቡት አስረጂዎች መረዳት ይቻላል፡፡ነገር ግን አደረጃጀቱን ስንመለከት በምዕራፍ አምስት ሶስት ጊዜ ተከታትሎ ቀርቧል፡፡በምዕራፍ ሁለትና አስር ደግሞ አንድ አንድ ጊዜ ቀርቧል፡፡በእርግጥ ይዘቱ እየተከታተለ መቅረቡ መልካም ቢሆንም በአንድ ምዕራፍ ዉስጥ ሶስት ጊዜ ከመቅረብ ይልቅ በሌሎች ምዕራፎች ዉስጥ እየተካተተ ቢቀርብ የተሻለ ይሆን ነበር፡፡በሶስተኛ ደረጃ በመደጋገም የቀረበዉ ቃላትንና ሀረጋትን በተመሳሳያቸዉ መተካት የሚለዉ ይዘት ሲሆን ለአራት ጊዜ ተደጋግሞ ቀርቧል ፡፡ይኸዉም ከጠቅላላዉ በመቶኛ ያለዉ ድርሻም 7% ነዉ፡፡ቀጥለን የዚህን ይዘት አደረጃጀት ለማየት እንሞክራለን፡-

*አስረጂ 79፡-በምዕራፍ ሶስት ‹‹ለተሰመረባቸዉ ቃላትና ሐረጋት በፍቺ የሚመሳሰሏቸዉን ቃላት ከግጥሙ ዉስጥ በመፈለግ ተክታችሁ ጻፉ፡፡››በማለት ገጽ/55/ ላይ የቀረበ ሲሆን በምዕራፍ አራት ገጽ/85/ ደግሞ ‹‹የሚከተሉትን ጥቅል መግለጫዎች በሰንጠረዡ ዉስጥ ያሉትን ፊደላት በተለያየ አቅጣጫ በማንበብ ተመሳሳይ ፍቺ ከሚሰጡ ቃላት ጋር አዛምዱ፡፡››በማለት ቀርቧል፡፡/አስረጂ 80/፡፡በምዕራፍ ሰባት ገጽ/139/ ደግሞ ‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች የተሰመረባቸዉን ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሰረት በተመሳሳይ ቃላትና ሐረጋት ተክታችሁ ጻፉ፡፡››ሲል ተደራጂቷል፡፡/አስረጂ 81/፡፡በምዕራፍ ስምንት ገጽ/172/ ‹‹ከሚከተሉት ቃላት ተገቢ የሆኑትን እየመረጣችሁ በዓረፍተ ነገር ዉስጥ በተሰመረባቸዉ ቃላትና ሐረጋት ተኩ፡፡››በማለት እየተከታተለ ቀርቧል፡፡/አስረጂ 82/፡፡*

ከቀረቡት መልመጃዎች መረዳት እንደሚቻለዉ ይዘቱ በተለያዩ አራት ምዕራፎች ለአራት ጊዜ እየተከታተለ ቀርቧል፡፡ይኸዉም ለማስተማር የተፈለገዉን ይዘት ተማሪዎች በተለያዩ ምዕራፎች ዉስጥ የሚያገኙት በመሆኑ እንዳይረሱት ያግዛል፡፡በተጨማሪም ሳይሰላቹ የቀረበዉን መልመጃ በትኩረት እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡ስለዚህ ይዘቱ ከአደረጃጀት አንጻር ጠንካራ ጎን ይታይበታል፡፡

በመቀጠል ሶስት ሶስት ጊዜ ተደጋግመዉ የቀረቡት ስነ-ምዕላድና ስነ-አገባብን ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎች ሲሆኑ እነሱም የተጸዉዖ፣የወል ስሞችንና የዋህ ኃላፊ ግስን መለየት ፤ጥቅል ቃላትንና ሀረጋትን መዘርዘር ፤ምድብ ተዉላጠ ስም፣አገናዛቢ ተዉላጠ ስምንና ዘርፍን መለየት ፤ጠቋሚ መስተአምርንና ወደረኛ መስተጻምርን መለየትና ሐተታ(አዎንታዊና አሉታዊ) ዓረፍተ ነገሮችን መለየት ሲሆኑ እያንዳንዳቸዉ በመቶኛ ያላቸዉ ድርሻም 5% ነዉ፡፡እነዚህ ሰዋስዋዊ ይዘቶች እንዴት እንደተደራጁ የሚከተሉትን አስረጂዎች እንመልከት፡-

*በምዕራፍ አንድ ገጽ/8/ ‹‹የሚከተሉትን ስሞች የወል ወይም የተጸዉኦ በማለት በሁለት ምድብ ለይታችሁ በደብተራችሁ ጻፉ፡፡››በማለት የቀረበ ሲሆን በገጽ/15/ ደግሞ እንዲህ ሲል ቀርቧል፡፡ ‹‹በሚከተሉት የዋህ ኃላፊ ግሶች ዓረፍተ ነገር ሰርታችሁ አሳዩ፡፡››/አስረጂ 84/፡፡በዚህ ምዕራፍ በገጽ /21/ ላይ ‹‹የሚከተሉትን ቃላት የወል ወይም የተጸዉኦ በማለት ለይታችሁ ጻፉ፡፡››ሲል ተደራጂቷል፡፡/አስረጂ 85/፡፡*

ከላይ የቀረቡትን አስረጂዎች ስንመለከት የተጸዉኦ፣የወል ስሞችና የዋህ ኃላፊ ግስን መለየት የተሰኘዉ ይዘት በምዕራፍ አንድ ስር ሶስት ጊዜ እየተደጋገመ ቀርቧል፡፡ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ምድብ ተዉላጠ ስምን፣አገናዛቢ ተወላጠ ስምንና ዘርፍን መለየት የተባለዉ ይዘት እንዲሁ በምዕራፍ ስድስት ብቻ እየተደጋገመ ቀርቧል፡፡ይህንን ከሚከተሉት አስረጂዎች እንመልከት፡-

*አስረጂ 86፡-በምዕራፍ ስድስት ገጽ/118/ ‹‹ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ባለንብረትነትን የሚያመለክቱ አገናዛቢተዉላጠ ስሞችን (ዘርፎችን) አስምሩባቸዉ፡፡››ሲል የቀረበ ሲሆን በገጽ/126/ በሚከተለዉ መልኩ ቀርቧል፡፡ ‹‹ተስማሚ ተዉላጠ ስምን በክፍት ቦታዉ በማስገባት ዓረፍተ ነገሩን አሟሉ፡፡››/አስረጂ 87/፡፡በገጽ/135/ ደግሞ‹‹የሚከተሉትን ተዉላጠ ስሞች በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ስሩ፡፡››በማለት ቀርቧል፡፡/አስረጂ 88/፡፡*

ሌላዉ ስነ አገባብን ለማስተማር ከቀረቡት ሰዋስዋዊ ይዘቶች መካከል ሐተታዊ (አዎንታዊና አሉታዊ) ዓረፍተ ነገሮችን መለየት በምዕራፍ ሶስት ሶስት ጊዜ እየተከታተለ ቀርቧል፡፡ይህንን አደረጃጀት ቀጥሎ ከቀረቡት አስረጂዎች *እንመልከት፡-አስረጂ 89 በገጽ /51/ ‹‹የሚከተሉትን ሐተታዊ ዓረፍተ ነገሮች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መሆናቸዉን በምክንያት ግለጹ፡፡››በማለት የቀረበ ሲሆን በገጽ /58/ ደግሞ‹‹የሚከተሉትን ሐተታዊ ዓረፍተ ነገሮች አሉታዊ ወይም አዎንታዊ በማለት በምክንያት ግለጹ፡፡››ሲል ቀርቧል፡፡በዚሁ ምዕራፍ ገጽ /65/‹‹የሚከተሉትን አዎንታዊ ዓረፍተ ነገሮች ወደ አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች በመለወጥ ጻፉ››በማለት እየተከታተለ ተደራጂቷል፡፡/አስረጂ 90/፡፡*

እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸዉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ተከታታይነታቸዉን ጠብቀዉ የተደራጁ ሲሆን በአንድ ምዕራፍ ዉስጥ ብቻ እየተከታተሉ መቅረባቸዉን ማስተዋል ተችሏል፡፡ተከታታይነትን አስመልክተዉ LarsenFreeman(1991)ተከታታይነት ሲባል ሰዋስዋዊ ይዘቶች እየተከታተሉ መምጣት ብቻ ሳይሆን እነዚህ ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎችና አዉዶች ዉስጥ መገኘት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

*ሁለት ሁለት ጊዜ ተደጋግመዉ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ስምንት ሲሆኑ እነሱም ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግን መለየት ፣ቃላትን በማቃረን ማዛመድ ፣ቅጽልንና መስተዓምርን*

መለየት፤ተዉሳክ ግስንና እምርነት አመልካች ቅጥያዎችን መለየት ፤ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ተሳቢን መለየት፤አያያዦችን በመጠቀም ዐረፍተ ነገሮችን ማሟላት ፤ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች መስጠትና ለቃላትና ሀረጋት ፍች መስጠት ናቸዉ፡፡እያንዳንዳቸዉ በመቶኛ ያላቸዉ ድርሻ 3% ነዉ፡፡ከተዘረዘሩት ይዘቶች መካከል የተወሰኑትን ለአብነት በመዉሰድ ተከታታይነታቸዉ ምን እንደሚመስል እንመልከት፡-

*አስረጂ 91፡-በምዕራፍ ሁለት ገጽ/35/‹‹የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግን ለይታችሁ ጻፉ፡፡››በማለት የቀረበ ሲሆን በገጽ /42/ ደግሞ‹‹የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ ለይታችሁ ጻፉ፡፡››በማለት ቀርቧል፡፡/አስረጂ 92/፡፡*

*ቅጽልንና መስተዓምርን መለየት በሚመለከት የቀረቡ ይዘቶች ደግሞ እንዴት እንደተደራጁ ቀጥለን እንመልከት አስረጂ 92 ምዕራፍ አራት ‹‹በሚቀጥለዉ ባሉ ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ቅጽል የሆኑትን ቃላት ከስር አስምሩባቸዉ፡፡››/ገጽ፣73/ በዚሁ ምዕራፍ ዉስጥ ‹‹የሚከተሉትን ቃላት ቅጽል ወይም መስተዓምር በማለት በሰንጠረዥ ዉስጥ ለይታችሁ አመልክቱ››/ገጽ፣88/ ይገኛሉ፡፡/አስረጂ 93/፡፡ተዉሳክ ግስንና እምርነት አመልካች ቅጥያዎችን መለየት የተባለዉ ይዘት ደግሞ ምዕራፍ ሰባት /ገጽ፣143/‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ተዉሳክ ግስ የሆኑትን ቃላትና ሐረጋት ለይታችሁ ጻፉ፡፡በማለት ሲቀርብ /ገጽ፣157/ ደግሞ‹‹የሚከተሉትን ተዉሳክ ግሶች በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ስሩ››በማለት ቀርቧል፡፡/አስረጂ 94/፡፡*

እነዚህ ለአብነት የቀረቡት ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ዉስጥ ሁለት ጊዜ በመከታተል የቀረቡ ናቸዉ፡፡ሳይከታተሉ አንድ ጊዜ ብቻ ከቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ዉስጥ ስነ-ድምጽን ለማስተማር ከተካተቱት መካከል የቃላትን ፊደላት ማጥበቅና ማላላት ሲሆን ከስነ-ምዕላድ ጋር በተገናኘ መጣኝና ደረጃ አመልካች መስተዓምርን መለየት ይገኙበታል፡፡ከስነ-አገባብ ጋር በተገናኘ ቃላትን በተቢዉ ዐዉድ በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን ማሟላት፣ቃላትን በተገቢዉ ዐዉድ በመጠቀም አንቀጽን ማሟላት፣ በአንቀጽ ዉስጥ አያያዦችን መጠቀም የሚሉት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ሲሆኑ ከስነ-ፍቺ ጋር በተያያዘ ደግሞ ቃላት ከምንባብ ዉጪ ያላቸዉን ፍቺ ማሳየት፣ቃላትንና ሀረጋትን ከሁኔታዎች ጋር በማዛመድ ፍቺ መስጠትና በፍቺ ልዩ የሆነዉን ቃል መለየት ናቸዉ፡፡እያንዳንዳቸዉ በመቶኛ ያላቸዉ ድርሻም 2% ያህሉን ይሸፍናሉ፡፡ቀጥለን ደግሞ ይህን አደረጃጀት አስመልክቶ ለመምህራን ከቀረበዉ መጠይቅ የተገኙ ምላሾች እንደሚከተለዉ ቀርበዋል፡፡ ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ ቁጥር 5. በመማሪያ መጽሐፉ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች እየተከታተሉ ቀርበዋል፡፡

መምህር 1‹‹በዚህ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ካስተዋልኩት ጠንካራ ጎኖች መካከል ብዙዎቹ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች ዉስጥ እየተከታተሉ መቅረባቸዉን ነዉ፡፡ይህ ደግሞ ተማሪዎች ይዘቱን በቀላሉ እንዲያስታዉሱት ይረዳል፡፡››በማለት አስረድተዋል፡፡

መምህር 2 ደግሞ‹‹በእርግጥ አብዛኛዎቹ ይዘቶች እየተከታተሉ ቀርበዋል፡፡ነገር ግን አንዳንድ ይዘቶችን ስንመለከት ከመከታተል ይልቅ መደጋገም ይታይባቸዋል፡፡››ሲሉ ምላሻቸዉን ሰጥተዋል፡፡

መምህርት 3 በበኩላቸዉ‹‹እኔ በዚህ መጽሀፍ ሳስተምር ከአስተዋልኩት ጥሩ ጎኑ ይዘቶቹ በተለያዩ ምዕራፎች እየተከታተሉ መምጣታቸዉ ነዉ፡፡››በማለት ምላሻቸዉን ሰጥተዋል፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለዉ ሶስቱም መምህራን ተቀራራቢነት ያላቸዉ ምላሾችን በመስጠት በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች እየተከታተሉ በቅረባቸዉን አስረድተዋል፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ በ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከቀረቡት 25 የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል 16ቱ ማለትም( 64%) ያህሉ ተከታትለዉ መቅረባቸዉን መምህራን ከተገኙ ምላሾችና በሰነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ነገር ግን እነዚህ ተከታትለዉ ከቀረቡ አብዛኞቹ ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች ዉስጥ ተከታትለዉ የቀረቡ ሲሆን የተወሰኑት ይዘቶች ደግሞ በአንድ ምዕራፍ ዉስጥ ተጠቅልለዉ መቅረባቸዉን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ተከታታይነት በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ተደጋግመዉ መቅረብን የሚመለከት ቢሆንም እንኳ እነዚህ ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎችና አዉዶች ዉስጥ ሳይቆራረጡ መደራጀት እንዳለባቸዉ Tayler (1949) እና Taba(1962) ይገልጻሉ፡፡በመሆኑም ተተኳሪዉ መማሪያ መጽሀፍ ከሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት መርህ አንጻር ሲታይ ጠንካራ ጎኑ እንደሚያመዝን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

በአጠቃላይ ጥናቱ ከሚመልሳቸዉ ጥያቄዎች መካከል አንዱ በ5ኛና 6ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከአደረጃጀት አንጻር የይዘቶች ተከታታይነት ምን ይመስላል? የሚል ነዉ፡፡ይህንን ጥያቄ በመመርኮዝ በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በሰንጠረዥ 13 እና15 ለማሳየት እንደተሞከረዉ አብዛኛዎቹ ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች ተከታትለዉ መቅረባቸዉን መመልከት ተችሏል፡፡ይኸዉም ተማሪዎች ይዘቱን የበለጠ እንዲረዱትና በቀላሉ እንዳይረሱት የሚያግዝ

በመሆኑ ከጠንካራ ጎን የሚጠቀስ ቢሆንም በተለይ በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከተካተቱ ይዘቶች የተወሰኑት ግን ተከታትለዉ መቅረብ አይታይባቸዉም፡፡ተከታትለዉ የቀረቡት ይዘቶችም ቢሆን በአንድ ምዕራፍ ዉስጥ ብቻ ተገድበዉ የቀረቡ መሆናቸዉን መረዳት ተችሏል፡፡

4.1.3.1.3 በ5ኛ እና በ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት መካከል ያለዉ የሰዋስዉ ትምህርት የይዘቶች ተከታታይነት

በሰንጠረዥ 4.3 እና 4.4 እንደተገለጸዉ በ5ኛ ክፍል 14 በ6ኛ ክፍል 25 የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች የቀረቡ ሲሆን ከእነዚህ ይዘቶች ዉስጥ 11 በ5ኛ ክፍል የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ዉሰጥ ተደጋግመዉ ቀርበዋል፡፡በሁለቱ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ ተከታታይነት አግኝተዉ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በሚከተለዉ ሰንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.5 በ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍት መካከል ተከታታይነት አግኝተዉ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች**

| | በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | ገጽ | በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | ገጽ |
|---|---|---|---|---|
| ስነ ምዕላድ | የተፃውዖ የወል ስሞችንና ግስን መለየት | 7፣13፣ 19፣111 118፣127 | የተፃዉዖ የወል ስሞችንና የዋህ ኃላፊ ግስን መለየት | 8፣15፣21 |
| | መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮች | 26፣32፣39 | መጣኝና ደረጃ አመልካች መስተኣምርን መለየት | 80 |
| | ግሳዊ ሀረግን መለየት | 188፣195፣201 | ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግን መለየት | 35፣42 |
| | ቅጽልን መለየት | 87፣95፣103፣163፣ 171፣179 | ቅጽልንና መስተኣምርን መለየት | 73፣88 |
| ስነ አገባብ | በቃላትና በሀረጋት ዓረፍተ ነገር መመስረት | 37፣108፣124፣150 159፣215 | ቃላትን በተገቢ አውድ በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን ማሟላት | 19 |
| | በአንቀጽ ውሰጥ የተጓደሉ ቃላትን ማሟላት | 142፣177 | ቃላትን በተገቢው አውድ በመጠቀም አንቀጽን ማሟላት | 147 |
| | አዎንታዊና አሉታዊ ሀተታ ዓረፍተ ነገሮችን | 210፣218፣225 | ሀተታ(አዎንታዊና አሉታዊ) ዓረፍተ ነገሮችን መለየት | 51፣58፣65 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | መለየትና መመስረት | | | |
| ስነ ፍቺ | የቃላትና ሀረጋት ተመሳሳይ ፍቺ የቃላትና ሀረጋት ተቃራኒ ፍቺ | 4፣24፣31፣51፣58፣72፣ 93፣100፣134፣168፣184፣193 11፣17፣44፣84፣199 | ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት | 32፣40 |
| | የቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ | 64፣78፣115፣199 | ለቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ መስጠት | 12፣26፣78፣ 99፣106፣144፣ 124፣188፣202፣ 212፣220 |
| | ቃላት ከምንባቡ ውጭ ያላቸው ፍቺ | 206 | ቃላት ከምንባብ ውጭ ያላቸውን ፍቺ ማሳየት | 63 |

ከቀረበዉ ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለዉ በ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ በተለያዩ ምዕራፎች ዉስጥ ተደጋግመዉ ከቀረቡት 14 የሰዋስዉ ትምህርት ትምህርት ይዘቶች 11 ይዘቶች ማለትም 78.5% በ6ኛ ክፍል ከቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ጋር ተከታታይነት አግኝተዉ ቀርበዋል፡፡በተጠኝዎቹ መማሪያ መጻህፍት ዉስጥ ተከታትለዉ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶችን በተመለከተ 6ኛ ክፍል ለሚያስተምሩ መምህራን ከቀረበ መጠይቅ የተገኙ ምላሾች በሚከተለዉ መልኩ ቀርበዋል፡፡

ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ ቁጥር 6 በመማሪያ መጽሐፉ ዉስጥ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች አሁን ካሉበት የክፍል ደረጃ በፊት የተዋወቋቸዉ ነበሩ፡፡

መምህር 1‹‹አዎ፡፡ብዙ እንግዳ ይዘቶችን በዚህ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ አላስተዋልኩም፡፡››ሲሉ መልሳቸዉን ሰጥተዋል፡፡

መምህር 2‹‹አብዛኛዎቹ ይዘቶች ባለፉት የክፍል ደረጃዎች እየተማሯቸዉ የመጡ በመሆናቸዉ በቀላሉ እንዲረዱት ያግዛል፡፡››በማለት አስረድተዋል፡፡

መምህረት 3 ደግሞ‹‹ጥቂት እንግዳ የሆኑ ይዘቶችን በዚህ መጽሀፍ ዉስጥ ባስተዉልም በርካታ ይዘቶች ግን እንግዳ አይደሉም፡፡››በማለት መልሳቸዉን ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ መምህራኑ የሰጡትን ምላሾች ስንመለከትና ተተኳሪዎቹን መማሪያ መጻህፍት በመፈተሽ ከተገኙ ዉጤቶች መረዳት እንደሚቻለዉ በ6ኛ ክፍል የቀረቡ አብዛኛዎቹ የሰዋስዉ

ትምህርት ይዘቶች በ5ኛ ክፍል *መማሪያ መጽሀፍ* ዉስጥ *ተማሪዎች* የተዋወቋቸዉ ናቸዉ፡፡ስለዚህ *ሁለቱ መማሪያ መጻህፍት* ተከታታይነት አላቸዉ ማለት ይቻላል፡፡

### 4.1.3.2 ተለጣጣቂነት

ተለጣጣቂነት በአንድ የክፍል ደረጃ ወይም በተከታታይ የክፍል ደረጃዎች የሚቀርብ የትምህርት ይዘት *መጀመሪያ* ከቀረበዉ የትምህርት ይዘት ተነስቶ ነገር ግን ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ መምጣትን የሚመለከት እንደሆነ በክለሳ ድርሳን ክፍል ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ በዚህም መሰረት በዚህ ጥናት ታላሚዎቹን መጻሕፍት *መጀመሪያ* ለየብቻ ነጣጥለን ካየን በኃላ መልሰን በሁለቱ መጻሕፍት መካከል ያለዉን የተለጣጣቂነት ሁኔታ በአንድ ላይ በማምጣት ለማየት እንሞክራለን፡-

#### 4.1.3.2.1 የ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ *መማሪያ* መጽሐፍ

በሰንጠረዥ 3 እንደተመለከተዉ በአምስተኛ ክፍል *መማሪያ* መጽሐፍ ዉስጥ ከቀረቡት 14 የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ዉስጥ 13 ( 92.8%)ያህሉ በተለያዩ ምዕራፎችና ገጾች ዉስጥ ተደጋግመዉ የቀረቡ ናቸዉ፡፡ ከእነዚህ አብዛኛዎቹ ስፋትና ጥልቀታቸዉን እየጨመሩ የተደራጁ ሲሆኑ የተወሰኑት ግን የተለጣጣቂነት ችግር እንዳለባቸዉ ተስተዉሏል፡፡ስፋትና ጥልቀታቸዉን እየጨመሩ ተደጋግመዉ ከቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች የተወሰኑትን ለአብነት እንመልከት:: በተተኳሪዉ መጽሀፍ መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮች የሚል የሰዋስዉ ትምህርት ይዘት በገጽ 26፣33 እና 40 የቀረቡትን አስረጂዎች እንመልከት፡-

*አስረጂ 93‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮችን ለይታችሁ ጻፉ፡፡››*

*ምሳሌ፡-አልማዝ ከአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች አንደኛ ወጣች፡፡*

*አምስተኛ = ደረጃ አመልካች ቁጥር*

*አንደኛ = ደረጃ አመልካች ቁጥር /ገጽ፣26/*

*አስረጂ 94‹‹ቀጥሎ ከቀረበዉ አንቀጽ መጣኝና ደረጃ አመልካች የሆኑት ቀጥሮች ለይታችሁአዉጡ››*

*ቅዳሜ የሳምንቱ ስድስተኛ ቀን ነዉ፡፡አስቴርና ባለቤቷ የዕረፍት ጊዜያቸዉ ስለሆነ*

*ወደ ገበያ ሄዱ፡፡አትክልት ተራ በመሄድ ስድስት ኪሎ ሽንኩርት ፣ሶስት ኪሎ ቲማቲምና*

*አንድ ኪሎ ቃሪያ ገዙ፡፡ከዚያም በገበያ አዳራሹሰባተኛ ፎቅ ላይ ከሚገኘዉ የልብስ ሱቅ*

*አስረጂ 95‹‹ከሚከተለዉ ጽሑፍ መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮችን ለይታችሁጻፉ፡፡››*

*ትምህርት ቤታችን ለሦስተኛ ጊዜ በተካሄደዉ ክልላዊ የትምህርት ቤቶች ስፖርታዊ ዉድድር ላይ ተካፋይ ነበር፡፡በዉድድሩ ላይም በመረብ ኳስ 19፣በእግር ኳስ 38 እና በአትሌቲክስ 18 ተወዳዳሪዎች ይዞ ቀርቧል፡፡አሰልጣኙንና ሌሎች ረዳት ባለሙያዎችን ጨምሮ የስፖርት ልዑካን ቡድኑ 82 አባላት ነበሩት ፡፡በዉድድሩ መጨረሻም በዉድድሩ ከቀረቡት 30 ትምህርት ቤቶች መካከል ቡድናችን በመረብ ኳስ ሦስተኛ፣ በእግር ኳስ 12ኛ፣ በአትሌቲክስ ደግሞ አምስተኛ ደረጃ ሊይዝ ችሏል፡፡በፀባይ ደግሞ አንደኛበመዉጣቱ የዋንጫ ተሸላሚ ሆኗል፡፡/ገጽ፣40*

*ለልጆቻቸዉ ልዩ ልዩ ልብሶች ገዙ፡፡ /ገጽ፣33/*

ከላይ የቀረቡት አስረጂዎች ስንመለከት በገጽ 26 ላይ ከቀረቡት ዘጠኝ ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ መጣኝና ደረጃ አመልካች የሆኑ ቁጥሮችን ለይተዉ እንዲጽፉ የሚያዝ መልመጃ ቀርቧል ፡፡በገጽ 33 አጠር ካለ አንቀጽ ዉስጥ መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮችን በመለየት እንዲያመለክቱ ያዛል ፡፡በገጽ 40 ደግሞ ሰፋ ካለ አንቀጽ ዉስጥ መጣኝና ደረጃ አመልካች የሆኑ ቁጥሮችን በመለየት በሰንጠረዥ ዉስጥ እንዲያሰፍሩ የሚያዝ መልመጃ ቀርቧል ፡፡ቀጥለን ደግሞ ቅጽልን ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎችን እንመልከት፡-‹‹ከቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ቅጽሎችን እየለያችሁ ጻፉ፡፡

*አስረጂ 97 ሀ. በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀመጥን ፡፡*

*ለ.ሱዳናዊ አርሶ አደር ተዋወቅሁ፡፡ /ገጽ፣87/*

*‹‹ቅጽሎችን ወደ ብዙ ቁጥርና አነስታይ ጾታ ቀይሩ፡፡››*

*ሀ.ረጅም --------- --------*

*ለ.ቀጭን --------- -------- /ገጽ፣95/*

*አስረጂ 98‹‹ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት ቅጽል የሆኑትን መርጣችሁ ዐረፍተ ነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ፡፡››*

*ሀ. እኔ -------ገመድ ገዛሁ።*

*ለ.------ተማሪ ሁልጊዜ ያጠናል። /ገጽ፣103/*

*አስረጂ 99‹‹ቅጽሎችን ፣መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮችን ተጠቅማችሁ 6 ዓረፍተ ነገሮች ጻፉ።›› /ገጽ፣172/*

ከላይ የቀረቡት መልመጃዎች እንደሚያስረዱት ገጽ 87 ከተሰጡ ዓረፍተ ነገሮች ቅጽልን እንዲለዩ የሚያዝ መልመጃ ቀርቧል። በገጽ 95 ደግሞ ቅጽሎችን በማቅረብ ተማሪዎች ወደ ብዙ ቁጥርና አንስታይ ጾታ እንዲቀይሩ ምሳሌዎችን በማቅረብ ያዛል።በገጽ 103 ላይ ስንመለከት ደግሞ ቅጽሎችን በመጠቀም የተጓደሉ ዓረፍተ ነገሮችን እንዲያሟሉ የሚያዝ መልመጃ ቀርቧል።ይህንኑ ይዘት በተመለከተ በተተኳሪዉ መጽሀፍ ገጽ 172 ተማሪዎች ቅጽሎችን በመጠቀም ስድስት ዓረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ የሚያዝ መልመጃ ቀርቧል ።በመሆኑም ይዘቱ ስፋቱን እየጨመረ መሄዱን ያሳያል።ሌላዉ ስፋትና ጥልቀታቸዉን እየጨመሩ ከቀረቡት ሰዋስዋዊ ይዘቶች መካከል ቀጥሎ የቀረቡትን መልመጃዎች እንመልከት፡-

*አስረጂ 100‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ያሉትን ባለቤቶች በምሳሌዉ መሰረት ለዩ።››*

*ምሳሌ፡-ሀቢባ ጠረጴዛ ጠገነች።*

*ባለቤት-------ሀቢባ*

*ሀ.ሀና ቀሚስ ለበሰች።*

*ለ.ዉሻዉ አጥንት በላ። /ገጽ፣138/*

*አስረጂ 101‹‹ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ያሉትን ባለቤቶች ለዩ።ከዚያም ባለቤቶቹ የተጸዉዖ ወይም የወል ስሞች መሆናቸዉን ለይታችሁ በደብተራችሁ ጻፉ።››*

*ሀ.ዓሣ በባህር ዉስጥ ይኖራል።*

*ለ.አባቴና እናቴ የመንግስት ሠራተኞች ናቸዉ። /ገጽ፣144/*

*አስረጂ 102‹‹አምስት የወልና አምስት የተጸዉዖ ስሞች እንደባለቤት በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ስሩ።›› /ገጽ፣153/*

ባለቤትን መለየት በተመለከተ በታላሚዉ መጽሐፍ ገጽ 138 ስድስት ዓረፍተ ነገሮችን በማስቀመጥ ከዓረፍተ ነገሮቹ ዉስጥ ባለቤት የሆኑ ስሞችን ተማሪዎች እየለዩ እንዲያስቀምጡ መልመጃ ቀርቦላቸዋል:: በገጽ 144 ደግሞ ከዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ባለቤት ስሞችን በመለየት ባለቤቶቹ የተጸዉዖ ወይም የወል ስሞች መሆናቸዉን እንዲያመለክቱ የሚያደርግ መልመጃ ተቀምጧል ።በገጽ 153 ላይ ስንመለከት ደግሞ ተማሪዎች አምስት የወልና አምስት የተጸዉዖ

ስሞች እንደባለቤት በመጠቀም ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ የሚያዝ መልመጃ ይታያል ። ከቀረበዉ መልመጃ መረዳት የሚቻለዉ ይዘቱ እየተከታተለ ሲቀርብ እራሱን እየደገመ ሳይሆን ስፋትና ጥልቀቱን እየጨመረ መሆኑን ነዉ።ከዚህ በተጨማሪ ተለጣጣቂነታቸዉን ጠብቀዉ ከቀረቡት ይዘቶች መካከል ግሳዊ ሐረግን መለየት የተሰኘዉ ይዘት ይጠቀሳል።አደረጃጀቱ ምን እንደሚመስል ቀጥለዉ ከቀረቡት መልመጃዎች እንመልከት፡-

*አስረጂ103 ‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ የሚገኙትን ግሳዊ ሐረጎች ለይታችሁ በደብተራችሁ ጻፉ።››*

*ሀ. ማስተዋል የቤት ስራዋን ሰራች።*

*ለ. እድሪስ የጓሮ አትክልት ተከለ፡ / ገጽ፣189/*

*አስረጂ104‹‹የሚከተሉትን ግሶች በመጠቀም ዓረፍተ ነገር መስርቱና ግሳዊ ሐረጉን በእዝባር ( / ) አሳዩ። /ገጽ፣201/*

ግሳዊ ሐረግ መለየትን ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎችን ስንመለከት በተተኳሪዉ መጽሀፍ ገጽ 189 ምሳሌ በማሳየት ከተሰጡ ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ግሳዊ ሀረግን እንዲለዩ ያዛል ።በገጽ 201 ላይ ግን ግሳዊ ሐረግን መለየት ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች የቀረቡላቸዉን ግሶች በመጠቀም ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ እና ግሳዊ ሐረጉን ለይተዉ እንዲያመለክቱ የሚያዝ መልመጃ ቀርቧል ።ከመልመጃዎቹ መረዳት የምንችለዉ ይዘቱ እየሰፋ መሄዱን ነዉ።

በተተኳሪዉ መጽሐፍ ዉስጥ ጥልቀታቸዉ እየጨመረ ከተደራጁት ይዘቶች መካከል ስነ አገባብን ለማስተማር የቀረቡትን መልመጃዎች ስንመለከት ደግሞ፡-

*አስረጂ105‹‹የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መሆናቸዉን በመለየት በደብተራችሁ ጻፉ።››*

*ምሳሌ ፡-ሴትየዋ ክፉ ሰዉ አይወዱም።(አሉታዊ ዓረፍተ ነገር )*

*ሀ.መስተዋት መኪና አልገዛችም።*

*ለ.ነኢማ ዳቦ ቤት አላት፡ /ገጽ፣210/*

*አስረጂ106‹‹የሚከተሉትን አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች ወደ አዎንታ ለዉጡ።››*

*ሀ. አርሶ አዳሪዉ በዚህ ዓመት ብዙ አላመረተም።*

*ለ. መምህሯ ዛሬ አልመጡም፡ /ገጽ፣218/*

*አስረጂ107‹‹አምስት አምስት አዎንታዊና አሉታዊ ሐተታ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ።›› /ገጽ፣225/*

ስነ አገባብን ለማስተማር ከቀረቡት ሰዋስዋዊ መልመጃዎች መካከል ገጽ 210 በርካታ ሐተታዊ ዓረፍተ ነገሮችን በማቅረብና ምሳሌ በማሳየት የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች አሉታዊ ወይም አዎንታዊ መሆናቸዉን ብቻ እንዲለዩ ያዛል፡፡ገጽ 218 ላይ ስንመለከት ደግሞ አሉታዊ ሐተታ ዓረፍተ ነገሮችን ወደ አዎንታዊ ሐተታ ዓረፍተ ነገሮች፣ አዎንታዊ ሐተታ ዓረፍተ ነገሮችን ወደ አሉታዊ ሐተታ ዓረፍተ ነገሮች በመለወጥ እንዲያሳዩ የቀረቡ መልመጃዎች ይስተዋላሉ ፡፡በገጽ 225 ይህንኑ ይዘት አስመልክቶ ተማሪዎች አምስት አምስት አዎንታዊና አሉታዊ ሐተታ ዓረፍተ ነገሮችን መስርተዉ እንዲያሳዩ የሚያዙ መልመጃዎች ቀርበዋል፡ከዚህ መረዳት የምንችለዉ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶቹ ስፋትና ጥልቀታቸዉን እየጨመሩ የሚሄዱ መሆናቸዉን ነዉ፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ስፋትና ጥልቀታቸዉን ጠብቀዉ የተደራጁ ናቸዉ፡፡የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ ተለጣጥቀዉ መደራጀት እንዳለባቸዉ በክለሳ ድርሳን ክፍል ለመጥቀስ እንደተሞከረዉ Nunan(1988) የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ተለጣጣቂነት ባለዉ መልኩ እርስ በርስ ተሳስረዉ መደራጀት እንዳለባቸዉ ይገልጻሉ፡፡ከዚህ አንጻር መማሪያ መጽሐፉ ጠንካራ ጎን የሚስተዋልበት ቢሆንም ስፋትና ጥልቀታቸዉ እየጨመረ የማይሄዱ ይዘቶችም እንዳሉ ተስተዉሏል፡፡ ለአብነት የተወሰኑትን እንመልከት ፡-

*አስረጂ108‹‹ሄደ የሚለዉን ግስ በመጠቀም በምሳሌዉ መሰረት ዓረፍተ ነገር ሥሩ፡፡››*

*ምሳሌ፡- ሄደ*

*እኔ ሄድኩ፡፡*

*እኛ ሄድን፡፡ /ገጽ፣48/*

*አስረጂ109‹‹በቅንፍ ዉስጥ ከቀረቡት ኢ-ሳቢ ግሶች መካከል ተስማሚዉን በመምረጥ ዓረፍተ ነገሩን አሟልታችሁ ጻፉ፡፡››*

*ሀ. እኔ-----------፡፡(መጣ/መጣሁ)*

*ለ .እኛ------------፡፡(ሳቅን/ሳቁ /ገጽ፣54)*

*አስረጂ110‹‹በ ሀ ስር የተዘረዘሩትን ጅምር ዓረፍተ ነገሮች ከ ለ ሥር ከተዘረዘሩት ተስማሚ ግሶች በመምረጥ አሟልታችሁ ጻፉ፡፡›› /ገጽ፣60/*

*በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ገጽ 48 ላይ ኢ-ሳቢ ግስ በሚል የሰዋስዉ ትምህርት ይዘት ስር ተግባር 1 ላይ ሄደ በሚል ግስ ተማሪዎች ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ መልመጃ ቀርቦላቸዋል፡በገጽ 54 ላይ በቅንፍ ዉስጥ የቀረቡ ኢ-ሳቢ ግሶችን በመምረጥ ዓረፍተ ነገሮችን*

*እንዲያሚሉ የሚያዝ መልመጃ ይስተዋላል*:: ይህንኑ ይዘት አስመልክቶ በገጽ 60 ደግሞ በ‹‹ሀ››ስር የተዘረዘሩ ጅምር ዓረፍተ ነገሮችን ከ‹‹ለ››ስር ከተዘረዘሩት ግሶች በመምረጥ እንዲያሟሉ የሚያደርግ መልመጃ ቀርቧል፡፡የዚህን ይዘት አደረጃጀት ስንመለከት ስፋትና ጥልቀቱን የጠበቀ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ኢ-ሳቢ ግሶችን ተጠቅሞ ዓረፍተ ነገር መመስረት የተሰጡ ኢ-ሳቢ ግሶችን ተጠቅሞ ዐረፍተ ነገር ከማሟላት ከበድ የሚል ይዘት በመሆኑ ነዉ፡፡በመሆኑም ይዘቶቹ በሚደራጁበት ጊዜ ከቀላል ወደ ከባድ ወይም ስፋትና ጥልቀታቸዉን እየጨመሩ መንዝ ሲገባቸዉ ከከባድ ወደ ቀላል የተደራጁ ናቸዉ፡፡ስለዚህ ኢ-ሳቢ ግሶችን ተጠቅሞ ዐረፍተ ነገር ማሟላትን በማስቀደም ኢ-ሳቢ ግሶችን ተጠቅሞ ዐረፍተ ነገርን መመስረት መከተል ነበረበት፡፡ከዚህ አንጻር ሲታይ አደረጃጀቱ ተለጣጣቂነትን የጠበቀ አይደለም፡፡

ሌላው ስነ ፍች ለማስተማር ከቀረቡት ይዘቶች መካከል ለቃላትና ለሐረጋት ተመሳሳይ ፍች መስጠትን አስመልክቶ የቀረቡትን መልመጃዎች ስንመለከት ይህ ይዘት በታላሚው መጽሐፍ ውስጥ ለ 12 (አስራ ሁለት) ጊዜ ተደጋግሞ ቀርቧል፡፡ነገር ግን አደረጃጀቱን ስንመለከት በተወሰኑ ገፆች ለምሳሌ ገጽ 4፣31፣58 እና 134 ላይ ቃላትና ሐረጋቱን በማቅረብ ተመሳሳያቸውን እንዲያዛምዱ መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ለአስረጂነት መልመጃዎቹን እንመልከት፡-

*አስረጂ111«በ ሀ ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺ ከለ ረድፍ እየመረጣችሁ በማዛመድ ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡›› /ገጽ፣4/*

*አስረጂ112‹‹በ ሀ ረድፍ ለቀረቡት ቃላትና ሐረግ ተመሳሳይ ፍቻቸዉን በ ለ ረድፍ ካሉት ጋር እያዛመዳችሁ ጻፉ፡፡›› /ገጽ፣31/*

*አስረጂ113‹‹በ ሀ ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸዉን ከ ለ ረድፍ ካሉት በመምረጥ አዛምዱ፡፡›› /ገጽ፣58/*

*አስረጂ114‹‹በ ሀ ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸዉን ከ ለ ረድፍ በመምረጥ አዛምዳችሁ ጻፉ፡፡›› /ገጽ፣134/*

*በገጽ 24፣ 93፣168፣184 እና 193 ላይ ደግሞ ቃላትና ሐረጋቱን በዓረፍተ ነገር ውስጥ በማስመር ተማሪዎች ተመሳሳይ ፍቻቸውን እንዲጽፉ መልመጃዎች ቀርበዉላቸዋል፡፡ቀጥሎ የዚህን ይዘት አደረጃጀት እንመልከት፡-*

*አስረጂ115‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ለተሰመረባቸዉ ቃላትና ሐረጋት ፍቺ ስጡ፡፡› /ገጽ፣24/*

*አስረጂ116‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ የተሰመረባቸዉ ቃላት በምንባቡ መሰረት ያላቸዉን ፍቺ በደብተራችሁ ሠንጠረዥ አዘጋጅታችሁ ጻፉ፡፡›› /ገጽ፣93/*

*አስረጂ117‹‹ቀጥሎ በሳጥን ዉስጥ የቀረቡትን ቃላት ከፍቻቸዉ ጋር እያዛመዳችሁ በደብተራችሁ ጻፉ፡፡›› /ገጽ፣168/*

*አስረጂ118‹‹በምንባቡ ዉስጥ የተሰመረባቸዉን ቃላትና ሐረጋት የምንባቡን ሀሳብ በማይቀይሩ ተመሳሳይ ቃላትና ሐረጋት ተክታችሁ ጻፉ፡፡›› /ገጽ፣184/*

*አስረጂ119‹‹በሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ዉስጥ የተሰመረባቸዉን ቃላትና ሐረጋት የሚተኩ ተመሳሳይ ቃላትና ሐረጋት ከቀረቡት አማራጮች መርጣችሁ ጻፉ፡፡›› /ገጽ፣193/*

የዚህን ሰዋስዋዊ ይዘት አደረጃጀት ስንመለከት ስፋትና ጥልቀቱን እየጨመረ ከመሄድ ይልቅ ተመሳሳይ አደረጃጀቶችን የተከተለ ነው፡፡LarsenFreeman(1991) ተለጣጣቂነት የትምህርት ይዘቶች ተደጋግመዉ መምጣትን የሚመለከት ሳይሆን ተደጋግመዉ የሚመጡት የትምህርት ይዘቶች መጀመሪያ የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች መነሻ አድርገዉ ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ መምጣትን የሚመለከት መሆኑን አበክረዉ ይገልጻሉ፡፡በመሆኑም ከዚህ የአደረጃጀት መርህ አንጻር ሲታይ ከላይ የቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ክፍተት የሚታይባቸዉ ናቸዉ፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የቃላትና ሐረጋት ተቃራኒ ፍችን ለማስተማር የቀረቡት ይዘቶች በ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ 5 (አምስት) ጊዜ ተደጋግመው ቀርበዋል፡፡ነገር ግን ሁሉም መልመጃዎች ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ማለትም ተቃራኒያቸዉን በማዛመድ መልመጃዎችን እንዲሰሩ ተደርጎ የቀረቡ ናቸዉ፡፡እነዚህ ይዘቶች በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ እንዴት እንደተደራጁ የሚከተሉትን አስረጂዎች እንመልከት፡-

*አስረጂ120‹‹በምንባቡ ዉስጥ ለተሰመረባቸዉ ቃላትና ሐረጋት ተቃራኒያቸዉን አዛምዱ፡፡›› /ገጽ፣11/*

*አስረጂ121‹‹በ ሀ ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላት በ ለ ረድፍ ከቀረቡት ተቃራኒያቸዉን በመምረጥ አዛምዳችሁ ጻፉ፡፡›› /ገጽ፣17/*

*አስረጂ122‹‹በ ሀ ረደፍ ለተዘረዘሩት ቃላትና ሐረጋት ተቃራኒ ፍቻቸዉን ከ ለ ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ፡፡›› /ገጽ፣44/*

*አስረጂ123‹‹በ ሀ ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላት በምንባቡ መሠረት ተቃራኒያቸዉን ከ ለ ረድፍ በመምረጥ አዛምዳችሁ ጻፉ፡፡›› /ገጽ፣84/*

*አስረጂ124‹‹በ ሀ ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸዉን ከ ለ ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ፡፡›› /ገጽ፣199/*

ከላይ በአስረጂነት የቀረቡት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች ተከታትለዉ የተደራጁ ቢሆንም ከተለጣጣቂነት አንጻር ስንመለከታቸዉ ግን ፍጹም ተመሳሳይ በሆነ መልኩ የተደራጁ በመሆናቸዉ ይህን የአደረጃጀት መርህ የተከተሉ አይደሉም፡፡

በመቀጠል በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሀፉ ዉስጥ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች የተለጣጣቂነታቸዉ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ለመምህራን ከቀረበዉ መጠይቅ የተገኙ ምላሾች እንመልከት፡-

ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ ቁጥር 7 በመማሪያ መጽሐፉ ተከታትለዉ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀታቸዉን እየጨመሩ ነዉ፡፡

*መምህር 1‹‹በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የተካተቱ ብዙዎቹ ይዘቶች ክብደታቸዉን እየጨመሩ የተደራጁ መሆናቸዉን ተመልክቻለሁ፡፡››በማለት ምላሻቸዉን ሰጥተዋል፡፡*

*መምህርት 2 ደግሞ‹‹በዚህ መጽሀፍ ዉስጥ ከቀረቡት ይዘቶች አብዛኛዎቹ እየሰፉ የሄዱ ቢሆንም የተወሰኑት ደግሞ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ መደራጀታቸዉን አስተዉያለሁ፡፡››ብለዋል፡፡*

*መምህርት 3 በበኩላቸዉ‹‹በመማሪያ መጽሀፉ ዉስጥ ከቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶቹ አብዛኛዎቹ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ መደራጀታቸዉን ማየት ችያለሁ፡፡ነገር ግን ጥቂት ይዘቶች እየሰፉ የሄዱ መሆናቸዉንም ተመልክቻለሁ፡፡››በማለት ምላሻቸዉን ሰጥተዋል፡፡*

*ከመምህራኑ ከተገኙ ምላሾች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አብዛኛዎቹ ይዘቶች እየሰፉ የሄዱ ሲሆን የተወሰኑ ይዘቶች ደግሞ ጥልቀታቸዉን ሳይጨምሩ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ እየተከታተሉ መቅረባቸዉን ማስተዋል ተችሏል፡፡*

ጠቅለል ባለ መልኩ ስንመለከተዉ በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከአደረጃጀት አንጻር የይዘቶች ተለጣጣቂነት ምን እንደሚመስል በጥናቱ ለቀረበዉ ጥያቄ በሰነድ ፍተሻ፣ ከተማሪዎችና መምህራን ከተገኘዉ ምላሽ ማረጋገጥ እንደተቻለዉ በተተኳሪዉ መጽሐፍ ዉስጥ ከተካተቱት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መካከል አብዛኛዎቹ ይዘቶች ስፋትና ጥልቀታቸዉን እየጨመሩ የተደራጁ ቢሆንም ጥቂት ይዘቶች ደግሞ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ በተለያዩ ምዕራፎች ተደራጅተዉ መቅረባቸዉን ማስተዋል ተችሏል፡፡እንደ LarsenFreeman (1991) ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች እርስ በራሳቸዉ

ተደጋግፈዉ በመሄድ የተማሪዉን የተግባቦት ደረጃ ለማሳደግ በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ስፋትና ጥልቀት እያገኙ መሄድ እንዳለባቸዉ ያስረዳሉ፡፡በመሆኑም ተተኳሪዉ መማሪያ መጽሀፍ ከተለጣጣቂነት አንጻር በአብዛኛዉ ጠንካራ ጎኑ እንደሚያመዝን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

4.1.3.2.2 የ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

በ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከተካተቱት 25 የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል 16ቱ (64%) የሚሆኑት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በተለያየ መጠን ተደጋግመዉ ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ተደጋግመዉ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ምን ያህል ተለጣጥቀዉ እንደቀረቡ ምሳሌዎችን በማቅረብ ለማየት እንሞክራለን፡፡ በተተኳሪዉ መጽሐፍ ዉስጥ ተለጣጣቂነታቸዉን ጠብቀዉ ከቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል ለቃላትና ሀረጋት ዐዉዳዊ ፍቺ መስጠት አንዱ ሲሆን ይህ ይዘት በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ በ7 ምዕራፎች ማለትም በምዕራፍ 1፣2፣4፣5፣6፣9፣እና 10 ዉስጥ በቁጥር 11 ጊዜ በፐርሰንት ደግሞ 18% ያህል ተደጋግሞ ቀርቧል፡፡የይዘቱን ተለጣጣቂነት በተመለከተ የሚከተሉትን አስረጂዎች እንመልከት፡-

*አስረጂ125‹‹ለተሠመረባቸዉ ቃላት ዐዉዳዊ ፍቺ በጹሁፍ ግለጹ፡፡››*

*ሀ.የሃይማኖት አባቶች በዓዉደ ዓመት ዕለት ካባ ይደርባሉ፡፡*

*ለ .አዛዉንቶች በጥምቀት ዕለት በርኖስ ደርበዉ ለብሰዋል፡፡ /ገጽ፣12/*

*አስረጂ126‹‹ለሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገር በመስራት ዐዉዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡››*

*ሀ .ሥራ*

*ለ .ዝና /ገጽ፣26/*

*አስረጂ127‹‹ለሚከተሉት ቃላት ዐዉዳዊ ፍቻቸዉን በጹሑፍ ስጡ፡፡››*

*ሀ.ቃሬዛ (አንቀጽ3)*

*ለ መጤ (አንቀጽ4) /ገጽ፣106*

*አስረጂ 128‹‹ከምንባቡ ዉስጥ ዘጠኝ ቁልፍ ቃላትንና ሐረጋትን ለይታችሁ በማዉጣት ዐዉዳዊ ፍቻቸዉን ግለጹ፡፡›› /ገጽ፣188/*

*አስረጂ 129‹‹በሚከተሉት ቃላት የተለያየ ፍቺ ያላቸዉ ሁለት ሁለት ዓረፍተ ነገሮች መሥርቱ፡፡››*

*ሀ ጠላ*

*ለ መረቀ /ገጽ፣203/*

*አስረጂ130‹‹በሚከተሉት ቃላት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የተለያየ ፍቺ ያላቸዉ ዓረፍተ ነገሮችን መሥርቱ፡፡*

*ሀ ሰም*

*ለ መደብ /ገጽ፣221/*

የይዘቱን አደረጃጀት ስንመለክት በገጽ 12 ላይ ተማሪዎች በዓረፍተ ነገር ዉስጥ ለተሰመረባቸዉ ቃላት ዐዉዳዊ ፍቺ እንዲጽፉ መልመጃ ቀርቧል ፡፡በገጽ 26 ሰባት ቃላትን በማቅረብ በእነዚህ ቃላት ዓረፍተ ነገር በመመስረት ዐዉዳዊ ፍቻቸዉን እንዲሰጡ የሚያዝ መልመጃ ለተማሪዎች ቀርቦላቸዋል፡፡ በገጽ 106 ደግሞ በአንቀጽ ዉስጥ ለተሰመረባቸዉ ቃላት ዐዉዳዊ ፍቻቸዉን እንዲጽፉ የሚያዝ መልመጃ ቀርቧል፡፡ በገጽ 188 ተማሪዎች ከቀረበላቸዉ ምንባብ ዉስጥ ዘጠኝ ቁልፍ ቃላትንና ሀረጋትን በራሳቸዉ ለይተዉ በማዉጣት ዐዉዳዊ ፍቺዉን እንዲጽፉ ታዘዋል፡፡ በገጽ 203 ዘጠኝ ቃላትን በማቅረብ በእያንዳንዱ ቃል የተለያየ ፍቺ ያላቸዉ ሁለት ሁለት ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ የሚል መልመጃ ይስተዋላል፡፡ በገጽ 221 ደግሞ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የተለያየ ፍቺ ያላቸዉ ዓረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ የሚያዝ መልመጃ ቀርቧል፡፡ የእነዚህን ይዘት አደረጃጀት ስንመለከት ከቀላል ወደ ከባድ የሚጓዝ በመሆኑ ጥልቀቱ እየጨመረ ሄዷል ማለት ይቻላል፡፡

ሌላዉ ስነ-ምዕላድን በሚመለከት ከቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል ባለቤት ተሳቢንና ማሰሪያ ግስን መለየት የሚለዉ ይዘት በመማሪያ መጽሐፉ ዉስጥ አምስት ጊዜ የቀረበ ሲሆን ተለጣጣቂነቱ ምን እንደሚመስል በምሳሌ አስደግፈን ለማየት እንሞክራለን ፡-

*አስረጂ 131‹‹ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ባለቤትና ማሰሪያ ግስን ለይታችሁ ጻፉ፡፡››*

*1. ዓለሙ ተኛ፡፡*

*2. ዘይነባ ተነሳች፡፡ /ገጽ፣29/*

*አስረጂ 132‹‹ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ሰዋስዋዊ ባለቤት የሆኑትን ስሞች ከስራቸዉ በማስመር ለዩ፡፡››*

*ሀ ትግስት ፈጣን ልጅ ናት፡፡*

*ለ ልጆቹ ኳስ ተጫወቱ፡፡ /ገጽ፣95/*

*አስረጂ 133‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች የተሰመረባቸዉን ቃላት ሰዋስዋዊ ተግባር ጻፉ፡፡››*

*ሀ ሥርጉት የገዛችዉ ቤት በጣም ያምራል፡፡*

*ለ ሶፊያ ባለፈዉ ወር ሶፋ አሰራች ፡፡ /ገጽ፣101/*

*አስረጂ 134‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ባለቤት ፣ተሳቢና ግሥ የሆኑትን ቃላት ለይታችሁ ጻፉ፡፡››*

*ሀ ዝናሽ ለባለቤቷ ያነበበችዉን መጽሀፍ መለሰች፡፡*

*ለ ተማሪዎች ጥያቄዉን መለሱ፡፡ /ገጽ፣108/*

*አስረጂ 135‹‹በሚከተሉት ቃላት ባለቤት ፣ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ተሳቢ ያሏቸዉ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡››*

*ሀ ነገረቻት*

*ለ ሸለሙት /ገጽ፣233/*

በታላሚዉ መጽሐፍ ገጽ 29 የተወሰኑ ኣረፍተ ነገሮችን በማቅረብ ባለቤትና ማሰሪያ ግሱን ለይታችሁ ጻፉ፡፡ የሚል መልመጃ ቀርቧል ፡፡በገጽ 95 ከዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ሰዋስዋዊ ባለቤት የሆኑትን ስሞች ከስራቸዉ በማስመር እንዲያመለክቱ ለተማሪዎች መልመጃ ቀርቦላቸዋል ፡፡በገጽ 101 ላይ በዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ለተሰመረባቸዉ ቃላት ሰዋስዋዊ ተግባራቸዉን እንዲጽፉ የሚያዝ መልመጃ ይስተዋላል፡፡በገጽ 108 ስንመለከት ደግሞ ስድስት ቃላትን በማቅረብ ተማሪዎች እነዚህን ቃላት በመጠቀም ባለቤትና ተሳቢ ያላቸዉ ዓረፍተ ነገሮችን መስርተዉ እንዲያሳዩ የሚገልጽ መልመጃ ቀርቧል ፡፡በገጽ 233 የተሰጡ ቃላትን በመጠቀም ባለቤት፣ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢ ያላቸዉ ዓረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ የሚያዝ መልመጃ ይስተዋላል ፡፡ከላይ የቀረቡትን ይዘቶች አደረጃጀት ስንመለከት ቀለል ከሚሉ መልመጃዎች በመነሳት ወደ ከበድ የሚሉ መልመጃዎች የተጓዙ መሆናቸዉን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

በተተኳሪዉ መጽሐፍ ዉስጥ እኩል ሶስት ሶስት ጊዜ ተደጋግመዉ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶችን ስንመለከት ደግሞ ምድብ ተዉላጠ ስምን ፣አገናዛቢ ተዉላጠ ስምንና ዘርፍን መለየትና ስነአገባብን ለማስተማር ከቀረቡት ይዘቶች መካከል ሐታታዊ(አዎንታዊና አሉታዊ) ዓረፍተ ነገሮችን መለየት የሚሉት ይዘቶች ይጠቀሳሉ ፡፡በመቀጠል እነዚህ ይዘቶች ምን ያህል ተለጣጥቀዉ እንደቀረቡ ለማየት እንሞክራለን፦

*አስረጂ 136‹‹በምሳሌዉ መሰረት በቅንፍ ዉስጥ ያሉትን ተዉላጠ ስሞች በመምረጥ ዓረፍተ ነገሩን አሟሉ፡፡*

*ምሳሌ፡------ንቁ ተማሪ ናት፡፡*

*እሷ ንቁ ተማሪ ናት፡፡*

*ሀ---ወደ ትምህርት ቤት ሄድን፡፡(እነሱ፣እኛ)*

*ለ---ገንዘብ እንዳስቀምጥለት ሰጠኝ፡፡(እኔ፣እሱ) /ገጽ፣118)*

*አስረጂ 137‹‹ተስማሚ ተዉላጠ ስምን በክፍት ቦታዉ በማስገባት ዓረፍተ ነገሩን አሟሉ፡፡››*

*ሀ---አኩሪ ተግባር የፈጸሙ ናቸዉ፡፡*

*ለ---የሀገር ፍቅር ስሜት ሊያድርብን ይገባል፡ /ገጽ፣126/*

*አስረጂ 138‹‹የሚከተሉትን ተዉላጠ ስሞች በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ስሩ፡፡*

እኛ እሱ አንተ እኔ አንቺ እናንተ እሷ /ገጽ፣135/

ከላይ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች እንዴት እንደተደራጁ ስንመለከት በገጽ 118 በቅንፍ ዉስጥ የቀረቡ ተዉላጠ ስሞችን በመጠቀም ያልተሟሉ ዓረፍተ ነገሮችን እንዲያሟሉ የቀረበ መልመጃ ይስተዋላል፡፡ በገጽ 126 ተማሪዉ ተስማሚ ተዉላጠ ስምን በራሳቸዉ በመፈለግ በክፍት ቦታዉ በማስገባት ዓረፍተ ነገሮቹን እንዲያሟሉ የሚያዝ መልመጃ ቀርቧል፡፡ በገጽ 135 ደግሞ ሰባት ተዉላጠ ስሞችን በማቅረብ በእነዚህ ተዉላጠ ስሞች ዓረፍተ ነገሮችን መስርተዉ እንዲያሳዩ ለተማሪዎች መልመጃ ቀርቦላቸዋል፡፡የእነዚህ ይዘቶች አደረጃጀት ቀለል ካለዉ የሰዋስዉ ትምህርት በመነሳት ከበድ ወደሚለዉ ይዘት የሚጓዝ መሆኑን ከላይ የቀረቡት አስረጂዎች ይገልጻሉ፡፡በመሆኑም ተማሪዎች የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታቸዉን የሚያሳድግ አደረጃጀት በመሆኑ ተመረጭ ነዉ ማለት ይቻላል፡፡በመቀጠል ደግሞ በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የዐረፍተ ነገር አመሰራረትን በተመለከተ የተደራጁ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶችን እንዴት ተለጣጥቀዉ እንደቀረቡ አስረጂ ይዘቶችን በመጥቀስ ለማየት እንሞክራለን፡-

*አስረጂ 139‹‹የሚከተሉትን ሐተታዊ ዐረፍተ ነገሮች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መሆናቸዉን በምክንያት ግለጹ፡፡››*

*ሀ የሙሽራዋ እናት ቆንጆ ልጅ ወልደዋል፡፡*

*ለ የሙሽራዋ ጫማ ጥልፍልፍ ነዉ፡፡ /ገጽ፣51/*

*አስረጂ 140‹‹የሚከተሉትን አዎንታዊ ዓረፍተ ነገሮች ወደ አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች ለዉጣችሁ ጻፉ፡፡››*

*ሀ መልዕክትን በቃል ማስተላለፍ ይቻላል፡፡*

*ለ የሰዉ ልጆች ማንነት በግጥም ይገለጻል፡፡ /ገጽ፣58/*

*አስረጂ 141‹‹ስለፈለጋችሁት ጉዳይ ሦስት አዎንታዊና ሦስት አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮችን በደብተራችሁ ጻፉ፡፡›› /ገጽ፣66/*

ከአስረጂ መልመጃዎች መመልከት እንደሚቻለዉ ገጽ 51 ሐተታዊ ዓረፍተ ነገሮች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መሆናቸዉን እንዲለዩ የሚል መልመጃ ቀርቧል፡፡ገጽ 58 የተወሰኑ አዎንታዊ ዓረፍተ ነገሮችን በማቅረብ ወደ አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች ለዉጠዉ እንዲያሳዩ የሚያዝ መልመጃ ተሰጥቷል ፡፡በገጽ 66 ላይ ደግሞ ሶስት አዎንታዊና ሶስት አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ የሚል መልመጃ ቀርቧል፡፡ የእነዚህን ይዘቶች አደረጃጀት ስንፈትሽ በተለያዩ ምዕራፎች ራሳቸዉን እየደገሙ የቀረቡ ሳይሆን ጥልቀታቸዉን እየጨመሩ የተደራጁ መሆናቸዉን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ ከቀረቡት መልመጃዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከተካተቱት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ዉስጥ የተወሰኑት ከቀላል ወደ ከባድ የተደራጁ ናቸዉ ፡፡እነዚህ ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ እየተደጋገሙ ከመቅረባቸዉም በላይ ስፋታቸዉ እየጨመሩ በመሆናቸዉ የተማሪዉን በቋንቋ የመገልገል ችሎታን ያዳብራሉ፡፡በመማር ማስተማሩ ሂደት አሰልቺ አይሆኑም፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ ተተኳሪዉ መጽሐፍ ጠንካራ ጎን የሚስተዋልበት ሲሆን የተለጣጣቂነት ችግር የሚስተዋልባቸዉን የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በተተኳሪዉ መጽሐፍ ዉስጥ ተስተዉለዋል፡፡ለአብነት ቀጥሎ የቀረቡትን እንመልከት፡-

በታላሚዉ መጽሐፍ ስነ-ምዕላድን ለማስተማር ከቀረቡት ይዘቶች «ቃላትን በተመሳሳያቸዉ መተካት»የተሰኘው ይዘት አንዱ ሲሆን እንዴት ባለ መልኩ እንደተደራጀ ቀጥለን እንመለከታለን፡-

*አስረጂ 142‹‹ለተሰመረባቸዉ ቃላትና ሐረጋት በፍቺ የሚመሳሰሏቸዉን ቃላት ከግጥሙ ዉስጥ በመፈለግ ተክታችሁ ጻፉ፡፡››*

*ሀ ሥራዉ እንደሬት መሮታል፡፡ (ከስንኝ 2-4)*

*ለ ማረሻዉ ጠንካራ በመሆኑ አይሰበርም፡፡ (ከስንኝ 5-7) /ገጽ፣55/*

*አስረጂ 143‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች የተሰመረባቸዉን ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሰረት በተመሳሳይ ቃላትና ሐረጋት ተክታችሁ ጻፉ፡፡››*

*ሀ የኤች አይ ቪ ኤድስ በሽተኞች ቀጥር በየዓመቱ እየጨመረ ነዉ፡፡*

*ለ ኢትዮጵያ ኤች አይ ቪ /ኤድስ በፍጥነት ከሚዛመትባቸዉ ሀገራት አንዷናት፡፡ /ገጽ፣139/*

*አስረጂ 144‹‹ከሚከተሉት ቃላት ተገቢ የሆኑትን እየመረጣችሁ በዓረፍተ ነገር ዉስጥ በተሰመረባቸዉ ቃላትና ሐረጋት ተኩ፡፡››*

*ሀ በለቅሶዉ ዕለት ዘመዶቹ ከአንጀታቸዉ ሲያለቅሱ ዋሉ፡፡*

*ለ የዕድር አባላት አንድ ቀን ሙሉ ተቀምጠዉ ይዉላሉ፡፡/ገጽ፣172/*

ገጽ 55 በዓረፍተ ነገር ውስጥ በቀረቡ ቃላትና ሐረጋት ላይ በማስመር በፍቺ የሚመሳሰሉትን ቃላት ከግጥም ውስጥ በመፈለግ ተክተው እንዲጽፉ የሚያዝ መልመጃ ነዉ፡፡ገጽ 139 ደግሞ ከዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ የተሰመረባቸውን ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሰረት በተመሳሳይ ቃላትና ሐረጋት ተክተዉ እንዲጽፉ በሚል ትዕዛዝ ስድስት ዓረፍተ ነገሮችን ቀርበዋል፡፡ገጽ 172 ለተሰመረባቸዉ ቃላት ተገቢ የሆኑ ቃላትን እየመረጡ እንዲተኩ የሚል መልመጃ ቀርቧል:: የሶስቱንም ይዘቶች አደረጃጀት ስንመለከት ተመሳሳይ እንጅ እየሰፉ መሄድ አይታይባቸዉም፡፡ሌላዉ የተለጣጣቂነት ችግር ከሚስተዋልባቸዉ ይዘቶች መካከል የሚከተለዉን ይዘት እንመልከት፡-

*አስረጂ 145‹‹በምንባቡ መሰረት የቢጋር ሰንጠረዡን በተገቢዉ ቃላት አሟልታችሁ ጻፉ፡፡›› /ገጽ፣4/*

*አስረጂ 146‹‹መሀረቤን ያያችሁ የሚለዉን ጫወታ የድርጊት ቅደም ተከተል በቢጋር ሠንጠረዥ ዉስጥ ግለጹ፡፡›› /ገጽ፣70/*

*አስረጂ147‹‹የሚከተለዉን የቢጋር ሠንጠረዥ በተገቢዉ ቃላት አሟሉ፡፡››/ገጽ፣229/*

ከአስረጂዎቹ መረዳት እንደሚቻለዉ በመማሪያ መጽሐፉ ገጽ 4 የቢጋር ሰንጠረዥ በማቅረብ ጥቅል ቃላትንና ሀረጋትን እንዲዘረዝሩ የቀረበ መልመጃ ይስተዋላል ፡፡በገጽ 70 እንዲሁ የጫወታ ዓይነቶችን የሚገልጹ ቃላትና ሐረጋትን በቢጋር ሠንጠረዥ ውስጥ እንዲጽፉ የሚያዝ መልመጃ ለተማሪዎች ቀርቦላቸዋል፡፡በገጽ 229 ደግሞ ‹‹የህመም ዓይነቶች »የሚል ጥቅል ሐረጋትን በማቅረብ በቢጋር ሠንጠረዥ ውስጥ ተገቢዉን ቃላትና ሐረጋት ዘርዝሩ፡፡ የሚል መልመጃ ቀርቧል፡፡እነዚህ ጥቅል ቃላትንና ሐረጋትን ለመዘርዘር የቀረቡ ሶስት መልመጃዎች በተለያዩ ምዕራፎችና ገፆች ላይ ይቅረቡ እንጂ ፍጹም ተመሳሳይ በሆነ መልኩ የተደራጁ ናቸው፡፡ይዘቶቹንም ስንመለከት ስፋታቸዉንና ጥልቀታቸዉን እየጨመሩ መሄድ አይስተዋልባቸዉም፡፡ ጠቋሚ መስተኣምርንና ወደረኛ መስተጻምርን መለየትን አስመልክተዉ የተደራጁ ይዘቶችን ስትፈትሽ ደግሞ የሚከተለዉን ይመስላሉ፡-

*አስረጂ 148‹‹የሚከተሉትን ጠቋሚ መስተኣምሮች በመጠቀም በምሳሌዉ መሰረት ዓረፍተ ነገር ስሩ፡፡››*

*ያ እነዚያ ይቺ ይህ እነዚህ ያቺ*

*ምሳሌ ያቺ ልጅ ጎበዝ ተማሪ ናት፡፡‹‹ያቺ ››የሚለዉ ጠቋሚ መስተዓምር ነዉ፡፡ /ገጽ፣167/*

*አስረጂ 149‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ያሉትን ጠቋሚ መስተዓምሮች ለዩ፡፡››*

*ሀ ያ መጽሐፍ በጣም ትልቅ ነዉ፡፡*

*ለ እነዚያ ልጆች ተማሪዎቼ ናቸዉ፡፡/ገጽ፣175/*

*አስረጂ 150‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ያሉትን ጠቋሚ መስተዓምሮች ለይታችሁ ጻፉ፡፡››*

*ሀ ያቺ ጎበዝ ተማሪ አንደኛ ወጣች፡፡*

*ለ ይህ ሰዉ ጤነኛ አይመስለኝም፡፡ /ገጽ፣183/*

በተተኳሪዉ መጽሐፍ ዉስጥ ጠቋሚ መስተኣምርንና ወደረኛ መስተጻምርን መለየትን በተመለከተ በምዕራፍ ስምንት ሶስት ጊዜ በገጽ /167፣175፣183/ ተደጋግሞ ቀርቧል ፡፡ይዘቱ ምን ያህል ተለጣጣቂነቱን ጠብቆ እንደተደራጀ ስንመለከት በገጽ 167 ጠቋሚ መስተኣምሮችን በመጠቀም ዓረፍተ ነገር መስርተዉ እንዲያሳዩ ይጠበቃል፡፡ በገጽ /175/ ደግሞ ከቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ጠቋሚ መስተኣምሮች በመለየት እንዲጽፉ ሰባት ዓረፍተ ነገሮች ቀርበዋል፡፡ በገጽ /183 / ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ከቀረቡ ስድስት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ተማሪዎች ጠቋሚ መስተኣምሮችን ለይተዉ እንዲጽፉ የሚያዝ መልመጃ ይስተዋላል፡፡የዚህን ይዘት አደረጃጀት ስንፈትሽ በአንድ ምዕራፍ ዉስጥ ማለትም በምዕራፍ ስምንት ብቻ ተጠቅልሎ መቅረቡ የአደረጃጀቱ ደካማ ጎን ሲሆን ከሌሎች ይዘቶች ጋር ቦታ በማቀያየር በተለያዩ ምዕራፎች ተራርቆ እንዲቀርብ ቢደረግ፡፡ሌላዉ ይዘቱ ከቀላል ወደ ከባድ እያደገና ስፋትና ጥልቀቱን እየጨመረ መደራጀት ሲገባዉ ከከባድ ወደ ቀላል የተደራጀ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ጠቋሚ መስተኣምሮችን ተጠቅሞ ዓረፍተ ነገር መመስረት በዓረፍተ ነገር ዉስጥ የቀረቡትን መስተኣምሮች ከመለየት ከበድ የሚል ነዉ፡፡በመሆኑም ከዐረፍተ ነገር ዉስጥ የቀረቡትን መስተኣምሮች መለየት ቀደም ብሎ ቀርቦ መስተኣምሮችን ተጠቅሞ ዐረፍተ ነገር መመስረት ተከትሎት መደራጀት ነበረበት፡፡ከዚህ በመቀጠል ደግሞ በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች የተለጣጣቂነት ሁኔታ በተመለከተ ለመምህራን ከቀረበዉ መጠይቅ የተገኙ ምላሾች በሚከተለዉ መልኩ ቀርበዋል፡፡

ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ ቁጥር 7 በመማሪያ መጽሐፉ ተደጋግመዉ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀታቸዉን እየጨመሩ ነዉ፡፡

መምህር 1‹‹ብዙ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች የተደራጁት ከቀላል ወደ ከባድ ቢሆንም የተወሰኑት ደግሞ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ መደራጀታቸዉን በማስተምርበት ወቅት መመልከት ችያለሁ፡፡››በማለት መልሳቸዉን ሰጥተዋል፡፡

መምህር 2 ደግሞ‹‹አዎ፡፡አብዛኛዎቹ ይዘቶች ስፋትና ጥልቀታቸዉን እየጨመሩ የተደራጁ መሆናቸዉን ተመልክቻለሁ፡፡››በማለት መልሰዋል፡፡

መምህርት 3 በበኩላቸዉ‹‹ስፋትና ጥልቀታቸዉን ሳይጨምሩ የተደራጁ በርካታ ይዘቶች በመማሪያ መጽሀፉ እንዳሉ ማየት ችያለሁ፡፡ስለዚህ ሁሉም የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ተለጣጣቂነታቸዉን ጠብቀዉ ተደራጅተዋል ማለት አይቻልም፡፡››ሲሉ አስተያየታቸዉን ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ከይዘቶች ተለጣጣቂነት አንጻር በተደረገዉ ግምገማ የተወሰኑ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከቀላል ወደ ከባድ ፣ ከግልጽነት ወደ ዉስብስብነት እያደጉና ስፋትና ጥልቀታቸዉን እየጨመሩ መሄዳቸዉን መረዳት ተችሏል፡፡ ነገር ግን የተወሰኑ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ደግሞ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ እንደተደራጁ ፣ከከባድ ተነስተዉ ወደ ቀላል የሚሄዱ መሆናቸዉንና የተወሰኑት ደግሞ በአንድ ዉስን ምዕራፍ ዉስጥ ተጠቅልለዉ መቅረባቸዉን በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ነገር ግን ተለጣጣቂነት በየክፍል ደረጃዎች በሚዘጋጁ መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የሚቀርቡ ይዘቶች ቀጣይነት ያላቸዉና ስፋትና ጥልቀት እንዲኖራቸዉ በሚያስችል መልኩ ማደራጀት እንደሆነ ቀደም ሲል ምሁራን በክለሳ ድርሳን ክፍል ገልጸዋል፡፡ከዚህ መነሻ ሀሳብ ተተኳሪዉን መጽሐፍ ስንፈትሽ ዉስን ክፍተቶች የሚታይበት ቢሆንም ጠንካራ ጎኑ የሚያመዝን መሆኑን በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

4.1.3.2.3.በ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት መካከል ያለዉ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ተለጣጣቂነት

በሠንጠረዥ 5 ከቀረበው መረዳት እንደሚቻለው በ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት በተከታታይነት የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከስነምዕላድ አራት፣ከስነ አገባብ ሶስት፣ከስነ ፍቺ ደግሞ አራት በአጠቃላይ አስራ አንድ ናቸው፡፡እነዚህ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀታቸውን እየጨመሩ መደራጀት ሲገባቸው አብዛኛዎቹ ለውጥ ሳይኖራቸው ቀርበዋል፡፡ጥቂት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ደግሞ ስፋትና ጥልቀታቸውን

በመጨመር የተደራጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ስፋትና ጥልቀታቸውን እየጨመሩ ከተደራጁ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ውስጥ የተወሰኑትን በአስረጂነት እንመልከት፡-

*አስረጂ 151‹‹ለሚከተሉት ቃላት ዐዉዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡››*

*ሀ መቋጫ (አንቀጽ 1)*

*ለ ማጉያ (አንቀጽ 1) (አምስተኛ ገጽ ፣199)*

*አስረጂ 152‹‹ከምንባቡ ዉስጥ ዘጠኝ ቁልፍ ቃላትንና ሐረጋትን ለይታችሁ በማዉጣት ዐዉዳዊ ፍቻቸዉን ግለጹ፡፡›› (ስድስተኛ ገጽ፣188)*

ከላይ በሁለቱ የክፍል ደረጃዎች የቀረቡትን የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ብንመለከት በ5ኛ ክፍል ገጽ 199 የተወሰኑ ቃላትን በማቅረብና የቃሉን መገኛ አንቀጽ በመጠቆም ተማሪዎች «የምሳሌያዊ ንግግሮች ፋይዳ» ከሚለዉ ምንባብ ዉስጥ የቀረቡላቸውን ቃላት በመፈለግ አውዳዊ ፍቺያቸውን እንዲሰጡ የሚል መልመጃ ቀርቧል፡፡ይህንኑ ይዘት አስመልክቶ በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ደግሞ ‹‹ስርዓተ ጾታና ትምህርት ››ከሚለዉ ምንባብ ዘጠኝ ቁልፍ ቃላትን ሐረጋትን በራሳቸዉ ፈልገዉ በማዉጣት ዐዉዳዊ ፍቻቸዉን እንዲገልጹ ያዛል፡፡

የዚህን ይዘት አደረጃጀት ስንመለከት ስፋትና ጥልቀቱን እየጨመረ ቀርቧል ፡፡ምክንያቱም በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ለተሰጡት ቃላት በምንባቡ መሰረት ዐውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ የታዘዙ ሲሆን በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ግን ተማሪዎች ራሳቸዉ ቁልፍ ቃላትን ከምንባቡ በመፈለግ ዐዉዳዊ ፍቻቸዉን እንዲያቀርቡ በማድረግ ይዘቱን ከበድ እያደረጉ ለመጓዝ ተሞክሯል ፡፡በመሆኑም ይዘቱ ተለጣጣቂነቱን ጠብቋል ማለት ይቻላል፡፡ሌላዉ ቃላት ከምንባቡ ዉጪ ያላቸዉን ፍቺ ለማስተማር የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶችን በ5ኛና በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ስንፈትሽ ፡-

*አስረጂ 153‹‹ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት በምንባቡ ካላቸዉ ፍቺ የተለየ ፍቺ የያዘዉን አማራጭ ለይታችሁ በደብተራችሁ ጻፉ፡፡››*

*ለምሳሌ 1 ሲያሰኘዉ ሀ. ሲሻዉ ለ.ሲያስፈልገዉ ሐ.ሲያምረዉ (አምስተኛ ፣ገጽ 206)*

*አስረጂ 154‹‹የሚከተሉት ቃላት ከምንባቡ ዉጪ ያላቸዉን ፍቺ የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገሮችን ሥሩና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡›› (ስድስተኛ ፣ገጽ 63)*

ከላይ ከቀረበዉ አስረጅ መረዳት እንደሚቻለዉ በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ተማሪዎች ቃሉ ከምንባቡ ዉጪ ያለዉን ፍቺ ከቀረቡላቸዉ ሶስት ሶስት አማራጮች መካከል

በመምረጥ እንዲመልሱ ተደርጓል። በ6ኛ ክፍል *መማሪያ መጽሐፍ* ዉስጥ ደግሞ ለቀረቡት *ቃላት* ከምንባቡ ዉጪ *ያላቸዉን* ፍቺ *ተማሪዎች* ዓረፍተ *ነገር* በመመስረት እንዲያሳዩ *መልመጃ* ቀርቦላቸዋል።በመሆኑም ከ5ኛ ክፍል *መማሪያ መጽሐፍ* ከቀረበዉ ይዘት ይልቅ በ6ኛ ክፍል *መማሪያ መጽሐፍ* ዉስጥ የቀረበዉ ይዘት ስፋትና ጥልቀቱን ጨምሮ የቀረበ በመሆኑ ተለጣጣቂነቱን ጠብቋል *ማለት* ይቻላል።

በመቀጠል ደግሞ በሁለቱ ተተኳሪ መጻሕፍት ዉስጥ ተለጣጣቂነታቸዉን ሳይጠብቁ የተደራጁ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በርካታ ሲሆኑ የተወሰኑ ይዘቶችን በአስረጂነት በማቅረብ ለመመልከት እንሞክራለን:: ‹‹በ*ቃላትና ሀረጋት* ዓረፍተ *ነገር መመስረት*›› የተሰኘዉ ይዘት በ5ኛና 6ኛ ክፍል *መማሪያ መጽሐፍ* ዉስጥ እንዴት እንደተደራጀ ከሚከተሉት *መልመጃዎች* እንመልከት፡-

*አስረጂ 155‹‹የሚከተሉትን ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ ዉስጥ ባላቸዉ ፍቺ ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ ፍቻቸዉን የሚያሣዩ ዓረፍተ ነገሮችን በደብተራችሁ ጻፉ።››*
*(አምስተኛ፣ገጽ 215)*

*አስረጂ 156‹‹የሚከተሉትን ቃላት በትክክለኛ ቦታቸዉ በመጻፍ ዓረፍተ ነገሮችን አሟሉ።››*
*(ስድስተኛ ፣ገጽ 19)*

ከላይ የቀረበዉን አደረጃጀት ስንመለከት ተለጣጣቂነቱን የጠበቀ አይደለም። ምክንያቱም በ5ኛ ክፍል ላይ *ተማሪዎች* በተሰጣቸዉ *ቃላትና ሀረጋት* ምንባቡን *መሰረት* በማድረግ ፍቻቸዉን የሚያሳዩ ዓረፍተ *ነገሮችን* ሰርተዉ እንዲያሳዩ *ታዘዋል*። በ6ኛ ክፍል ደግሞ የተሰጣቸዉን *ቃላት* በቀረቡላቸዉ ዓረፍተ *ነገሮች* ዉስጥ እንዲያሟሉ የሚል ነዉ:: በመሆኑም ዓረፍተ *ነገር* *መመስረት* ከዓረፍተ *ማሟላት* ከበድ የሚል በመሆኑ በ5ኛ ክፍል *መማሪያ መጽሐፍ* ዉስጥ የቀረበዉ ይዘት በ6ኛ ክፍል *መማሪያ መጽሐፍ* ዉስጥ ከቀረበዉ ይዘት ይልቅ ጥልቀት *ያለዉ* ነዉ።ስለዚህ ይዘቱ ተለጣጣቂነቱን ጠብቆ ተደራጅቷል *ማለት* አይቻልም።በተጨማሪ *መጣኝና* ደረጃ አመልካች ቁጥሮችን ለማስተማር የቀረቡ ይዘቶች እንዴት እንደተደራጁ እንመልከት፡-

*አስረጂ 157‹‹ከሚከተለዉ ጹሁፍ መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮችን በምሳሌዉ መሰረት ለይታችሁ ጻፉ።›› (አምስተኛ፣ገጽ 39)*

*አስረጂ 158‹‹በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ መስተኣምር የሆኑትን ቃላት ከስራቸዉ አስምሩ ፣መጣኝና ደረጃ አመልካች መሆናቸዉንም ግለጹ።››*
*ሀ ዘገየ አንድ ጥቁር ኮት ገዛ።*

*ለ እኔ ለቤተሰቦቼ ሶስተኛ ልጅ ነኝ። (ስድስተኛ፣ገጽ 80)*

ከላይ በአስረጅነት በ5ኛና 6ኛ ክፍል የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ስንመለከት ከበድ ያለዉ የ5ኛ ክፍል የሰዋስዉ ትምህርት ይዘት ነዉ ።ምክንያቱም በ5ኛ ክፍል የቀረበዉ መልመጃ ከተሰጠዉ አንቀጽ ዉስጥ ተማሪዎች መጣኝና ደረጃ አመልካች የሆኑ ቁጥሮችን ለይተዉ እንዲያወጡ የሚያዝ ነዉ።በ6ኛ ክፍል የቀረበዉ ደግሞ ከነጠላ ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮች ለይተዉ ማዉጣት ነዉ።በሁለቱ መጻሕፍት ላይ ተደጋግሞ የቀረበዉ ይዘት ተያያዥነት ያለዉ ቢሆንም ስፋትና ጥልቀት የሚታይበት ግን በ5ኛ ክፍል መጽሐፍ ዉስጥ የቀረበዉ ይዘት ነዉ።ምክንያቱም በአንድ ዓረፍተ ነገር ዉስጥ የቀረበዉን መጣኝ ወይም ደረጃ አመልካች ቁጥር ከመለየት ይልቅ በአንቀጽ ዉስጥ ያሉትን መለየት ክብደት አለዉና።በተመሳሳይ መልኩ የቃላትና ሀረጋት ተመሳሳይ ፍቺ በተመለከተ በ5ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ገጽ /51/እና /52/ ከምንባቡ ዉስጥ ለቀረቡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲጽፉና በእነዚህ ቃላት ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ የሚያዙ መልመጃዎች ቀርበዋል።በ6ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሀፍ ገጽ /32/እና /40/ ደግሞ በ‹‹ሀ›› ረድፍ ቃላቱን በማቅረብ ከ‹‹ለ››ረድፍ ተመሳሳዩን እንዲያዛምዱ ታዘዋል። የዚህን ይዘት አደረጃጀት ስንመለከት የ5ኛ ክፍሉ ከ6ኛ ክፍሉ ስፋትና ጥልቀት ያለዉ ነዉ።

ከዚህ በተጨማሪም በ5ኛና 6ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ ተመሳሳይ አደረጃጀቶችን የተከተሉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች መኖራቸዉን በሰነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል።ቀጥለን እነዚህ ይዘቶች እንዴት እንደተደራጁ በአስረጂነት የቀረቡ መልመጃዎችን እንመለከታለን።ከእነዚህ ይዘቶች መካከል ስማዊ ሐረግና ግሳዊ ሐረግን መለየትን ለማስተማር የቀረበዉ ይዘት አንዱ ሲሆን አደረጃጀቱ ምን እንደሚመስል ለማየት እንሞክራለን፡-

*አስረጂ 159‹‹ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ዉሰጥ ያሉትን ባለቤቶችና ግሳዊ ሀረጎች እዝባር (/) በማድረግ ለዩ።›› *

*ሀ ማስተዋል የቤት ስራዋን ሰራች።*

*ለ እድሪስ የጓሮ አትክልት ተከለ። (አምስተኛ ፣ገጽ 188)*

*አስረጂ 160‹‹የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግን ለይታችሁ ጻፉ።››*

*ሀ መሰረት አኩሪ ድል አስመዘገበች።*

*ለ ኃይሌ የመርቅ ሜዳልያ ተሸለመ። (ስድስተኛ፣ገጽ 35)*

ከቀረቡት አስረጅዎች መረዳት እንደሚቻለዉ በ5ኛ ክፍል ገጽ/188/ ላይ ተማሪዎች ከተሰጣቸዉ ዐረፍተ ነገሮች ዉስጥ ባለቤቱንና ግሳዊ ሐረጎችን እንዲለዩ የሚያዝ መልመጃ ቀርቧል።በ6ኛ

ክፍል ገጽ/135/ ተማሪዎች ከቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ዉስጥ ስማዊ ሀረጉንና ግሳዊ ሀረጉን ለይተዉ እንዲጽፉ የሚል መልመጃ ቀርቧል። በእነዚህ ሁለት መጻሕፍት ዉስጥ የቀረቡት ይዘቶች ከአደረጃጀት አንጻር ፍጹም ተመሳሳይ ናቸዉ።ስነ አገባብን ለማስተማር ከቀረቡት ይዘቶች መካከል በአንቀጽ ዉስጥ የተጓደሉት ቃላትን ማሟላትና የዐረፍተ ነገር አመሰራረት ይዘቶች ከተለጣጣቂነት አንጻር እንዴት እንደቀረቡ ቀጥሎ የቀረቡትን አስረጅዎች እንመልከት፡-

አስረጂ 161‹‹ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላትና ሀረጋት በክፍት ቦታዎቹ በማስገባት አንቀጹን አሟልታችሁ ጻፉ።›› (አምስተኛ ፣ገጽ 142)

አስረጂ 162‹‹ከሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ተገቢ የሆኑትን መርጣችሁ ጹሁፉን አሟልታችሁ ጻፉ።›› (ስድስተኛ ፣ገጽ 147)

አስረጂ 163‹‹የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መሆናቸዉን በመለየት በደብተራችሁ ጻፉ።››

ሀ መስተዋት መኪና አልገዛችም።

ለ ነኢማ ዳቦ ቤት አላት። (አምስተኛ ፣ገጽ 210)

አስረጂ 164‹‹የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች አሉታዊ ወይም አዎንታዊ በማለት በምክንያት ለዩ።››

ሀ. መልዕክትን በቃል ማስተላለፍ ይቻላል።

ለ. የሰዉ ልጆች ማንነት በግጥም ይገለጻል። (ስድስተኛ ፣ገጽ 58)

አስረጂ 165‹‹የሚከተሉትን አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች ወደ አዎንታዊ ለዉጡ።››

ሀ. አርሶ አዳሪዉ በዚህ ዓመት ብዙ አላመረተም።

ለ. መምህሯ ዛሬ አልመጡም። (አምስተኛ ፣ገጽ 218)

አስረጂ 166‹‹የሚከተሉትን አዎንታዊ ዓረፍተ ነገሮች ወደ አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች በመለወጥ ጻፉ።››

ሀ. አልማዝ ቤቷን አጸዳች።

ለ. ሀያት የሬድዮ ትረካ ትወዳለች። (ስድስተኛ ፣ገጽ 65)

አስረጂ 167‹‹አምስት አምስት አዎንታዊና አሉታዊ ሀተታ ዓረፍተ ነገሮች መስርቱ ።›

(አምስተኛ ፣ገጽ 225)

አስረጂ 168‹‹ስለፈለጋችሁት ጉዳይ ሶስት አዎንታዊና ሶስት አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮችን በደብተራችሁ ጻፉ ።›› (ስድስተኛ ፣ገጽ 66)

እነዚህ ከላይ የቀረቡት ይዘቶች ለአብነት የቀረቡ ሲሆኑ በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ ከተካተቱት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል አብዛኛዎቹ ይዘቶች ምንም ልዩነት ሳይኖራቸዉ የተደራጁ መሆናቸዉን በተደረገዉ ግምገማ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡የተወሰኑ ይዘቶች ደግሞ በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ጥልቀት ያላቸዉ ሆነዉ የቀረቡ ሲሆን በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ግን ቀለል ብለዉ መቅረባቸዉን ማስተዋል ተችሏል፡፡ተለጣጣቂነት በተከታታይ የክፍል ደረጃዎች የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀታቸዉን እየጨመሩ መሄድ እንዳለባቸዉ የሚገልጽ ጽንሰ ሀሳብ እንደመሆኑ መጠን ተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ከይዘቶች ተለጣጣቂነት አንጻር ችግሮች ይስተዋሉባቸዋል፡፡

በመቀጠል ደግሞ ተጨማሪ መረጃዎችን ሊያስገኙ ይችላሉ በሚል እሳቤ በታላሚዎቹ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ለሚያስተምሩ መምህራን ሁለት ሁለት ተጨማሪ ክፍት ጥያቄዎች በማቅረብ የግላቸዉን አስተያየት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡በዚህም መሰረት በቅድሚያ ለ5ኛ ክፍል መምህራን በማቅረብ እነዚህን መጠይቆች የ6ኛ ክፍል መምህራንም ምላሽ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ቀጥሎ የቀረቡ መጠይቆችና የተገኙ ምላሾችን እንመልከት፡-

ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ ቁጥር 8.በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ዙሪያ ምን ምን ደካማና ጠንካራ ጎኖች ተመለከታችሁ?

መምህር 1‹‹እኔ እንዳስተዋልኩት በርካታ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች እንግዳ በመሆናቸዉ ለማስተማር ከበድ የሚል ነበር፡፡በእርግጥም ይዘቶቹ በተለያዩ ምዕራፎች እየተደጋገሙ መቅረባቸዉ እንደጠንካራ ጎን አይቸዋለሁ፡፡በተጨማሪም ምሳሌዎችን በማሳየት መልመጃዎችን ማቅረቡ ከመማሪያ መጽሀፉ ጠንካራ ጎን የሚጠቀስ ነዉ፡፡››በማለት ገልጸዋል፡፡

መምህርት 2 ደግሞ‹‹አብዛኛዎቹ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች የታላሚዉን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ቅርጽ የሚተነትኑ እንጂ ተማሪዎችን ለተግባቦት የሚጋብዙ ባለመሆናቸዉ እንደደካማ ጎን አይቸዋለሁ፡፡ነገር ግን ሁሉንም የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ያካተተ በመሆኑ ጠንካራ ጎንም ይስተዋልበታል፡፡››በማለት ገልጸዋል፡፡

መምህርት 3 የመጽሀፉን ደካማ ጎን ሲገልጹ‹‹በርካታ የሰዋስዉ ትምህርት መልመጃዎች ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ቀርበዋል፡፡ይህ ደግሞ ተማሪዎች እንዲሰላቹ የሚያደርግ በመሆኑ በተቻለ መጠን የተለያዩ አቀራረቦችን ቢከተሉ ጥሩ ነዉ፡፡ይዘቶቹ በተለያዩ ምዕራፎች

እየተደጋገሙ መቅረባቸዉ ተማሪዎች ይዘቱን በቀላሉ እንዳይረሱት የሚያደርግ መሆኑ ደግሞ ከጠንካራ ጎን የሚጠቀስ ነዉ፡፡››በማለት አስረድተዋል፡፡

በመቀጠል ደግሞ ይህንኑ መጠይቅ 6ኛ ክፍል ለሚያስተምሩ መምህራን በማቅረብ የተሰጡ ምላሾችን እንመልከት፡-

መምህር 1‹‹እኔ በማስረተምርበት ወቅት እንደተመለከትኩት መማሪያ መጽሀፉ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ስልት አልተከተለም፡፡ይህ አቀራረብ ተማሪዎችን ሊያግዙ የሚችሉ ገለጻዎችን የሚይዝ በመሆኑ መካተት ነበረበት፡፡ነገር ግን ብዙዎቹ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በ5ኛ ክፍል የተማሯቸዉ መሆናቸዉ ከአቀራረቡ ጠንካራ ጎን ይጠቀሳል፡፡››በማለት የአቀራረቡን ደካማና ጠንካራ ጎኖች ገልጸዋል፡፡

መምህር 2 ደግሞ‹‹መማሪያ መጽሀፉ ቅርብ ጊዜ ስራ ላይ የዋለ እንደመሆኑ መጠን ከቀድሞዎቹ የ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ጋር ሲተያይ የተሻለ የሰዋስዉ ትምህርት አቀራረብ ይታይበታል፡፡ሆኖም ግን ሁሉንም የሰዋስዉ ትምህርት አቀራረቦችን አላካተተም፡፡ከይዘቱ ተለጣጣቂነትም አንጻር በ5ኛ ክፍል የተማሩትን በዚሁ ክፍል ፍጹም ተመሳሳይ በሆነ መልኩ መድገሙ እንደ ክፍተት ይጠቀሳል፡፡››በማለት አስተያየታቸዉን ሰጥተዋል፡፡

መምህርት 3 ደግሞ አስተያየታቸዉን እንዲህ ሲሉ አቅርበዋል‹‹ተተኳሪዉ መጽሀፍ ሁሉንም የአቀራረብ ስልቶች ያልተከተለ መሆኑና በተለይም ደግሞ ተማሪዎች ቋንቋዉ ከመጠቀም ይልቅ ለሰዋስዋዊ ቅርጾች ትኩረት እንዲሰጡ የሚጋብዝ በመሆኑ ሊሻሻል ይገባል፡፡በተለይ ደግሞ ከቀድሞዎቹ መጻህፍት ይልቅ በሁሉም ምዕራፎች የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶችን አካትቶ ማቅረቡ ከጠንካራ ጎን ይጠቀሳል፡፡››በማለት አስረድተዋል፡፡

ሌላዉ በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻህፍት ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ዙሪያ መምህራን የግላቸዉን አስተያየት እንዲሰጡ የቀረበዉ መጠይቅና የተሰጡ ምላሾች በሚከተለዉ መልኩ ቀርበዋል፡፡ በቅድሚያ 5ኛ ክፍል ከሚያስተምሩ መምህራን የተገኙ ምላሾችን እንመልከት፡-

ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ ቁጥር 9 በተጠኝዉ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የሚካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በምን መልኩ መቅረብና መደራጀት እንዳለባቸዉ የራስዎን አስተያየት ይስጡ፡፡የሚል ነበር፡፡

የመጀመሪያዉ መምህር‹‹በ5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የሚደራጁ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከቀደመዉ ክፍል የሰዋስዉ ትምህርት ጋር ተከታታይነት ያለዉ መሆን አለበት፡፡በተጨማሪም የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ሲቀርቡ ሁሉንም የአቀራረብ ስልቶች መከተል አለባቸዉ፡፡ነገርግን የ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብን ያላከተተ በመሆኑ ወደ ፊት መጸሀፉ በሚሻሻልበት ወቅት አሻሻዮች ይህንን ከግንዛቤ ማስገባት አለባቸዉ፡፡››በማለት አስረድተዋል፡፡

መምህርት 2 ደግሞ‹‹የቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማ ተግባቦትን መፍጠር ነዉ፡፡ነገር ግን በ5ኛ ክፍል የቀረቡ አብዛኛዎቹ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ዉጤት ተኮር የአቀራረብ ስልት ላይ የሚያተኩሩ ናቸዉ፡፡ስለዚህ የመጽሀፍት አዘጋጆች በተቻለ መጠን ሂደት ተኮርና ዉጤት ተኮር የአቀራረብ ስልቶችን ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡››በማለት ገልጸዋል፡፡

መምህርት 3‹‹ለ5ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚቀርቡ የሰዋስዉ መልመጃዎች ፍጹም ተመሳሳይ በሆነ መልኩ መቅረብ የለባቸዉም፡፡ምክንያቱም ተማሪዎቹ በዕድሜ ያልበሰሉ በመሆናቸዉ ሊሰላቹ ይችላሉ፡፡ስለዚህ የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም መልመጃዎችን ደጋግሞ ማቅረብ ከመጽሀፍት አዘጋጆች የሚጠበቅ ነዉ፡፡››በማለት አስተያየታቸዉን ሰጥተዋል፡፡

በመቀጠል ደግሞ ይህንኑ መጠይቅ 6ኛ ክፍል ለሚያስተምሩ መምህራን በማቅረብ የተገኙ ምላሾችን እንመልከት፡-

መምህር 1‹‹የ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ አዘጋጆች በየጊዜዉ የሚታተሙ አዳዲስ የአማርኛ ማጣቀሻ መጻህፍትን ማንበብ ይጠበቅባቸዋል፡፡በተጨማሪም ይዘቶችን በሚያቀርቡበት ወቅት የተለያዩ መንገዶችን መከተል አለባቸዉ፡፡ተማሪዎቹ እንዳይሰላቹ ማለቴ ነዉ፡፡››በማለት ገልጸዋል፡፡

መምህር 2 ደግሞ‹‹የሰዋስዉ መልመጃዎች ለተማሪዎች በሚቀርቡበት ወቅት ተመሳሳይ የአቀራረብ መንገዶችን መከተል የለባቸዉም፡፡ለምሳሌ የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ሲቀርብ ሁልጊዜ በአዛምድ መልክ ብቻ መቅረብ የለበትም፡፡በመሆኑም የመጻህፍት አዘጋጆችና አሻሻዮች የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ ከግምት ዉስጥ ማስገባት ይጠበቅባቸዋል፡፡››ሲሉ ሀሳባቸዉን አስረድተዋል፡፡

መምህርት 3 በበኩላቸዉ‹‹በመማሪያ መጻህፍት ዉስጥ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ሲቀርቡ ተማሪዎች በቋንቋዉ ከክፍል ዉጪ እንዲገለገሉበት የሚጋብዝ መሆን አለበት ፡፡በተለይ በ6ኛ

ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች እንዴት መቅረብ እንዳለባቸዉ ጠቁመዋል፡፡በተጨማሪም መማሪያ መጻህፍት ሲዘጋጁ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች የአቀራረብና አደረጃጀት መንገዶችን መከተል አለባቸዉ፡፡››በማለት አስተያየታቸዉን ሰጥተዋል፡፡

## 4.2 የጥናቱ ዉጤት ማብራሪያ

በ5ኛና 6ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ ከተገኙት ዉጤቶች መካከል በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ስልትን ያላካተቱ መሆናቸዉን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ይኸዉም Ur (1996) የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ በሚካተቱበት ጊዜ ሁሉንም የማቅረቢያ መንገዶች ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ አካትተዉ ቢቀርቡ የተሻለ ዉጤት ይገኛል፡፡ ከሚለት ጽንሰ ሀሳብ ጋር ይቃረናል፡፡

በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የተካተቱ አብዛኛዎቹ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ዉጤት ተኮር የአቀራረብ መርህ ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ ሂደት ተኮር የአቀራረብ መርህን ተከትለዉ የቀረቡ የሰዋስዉ  ትምህርት ይዘቶች በጣም ጥቂት መሆናቸዉን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ይኸዉም Ur(1988)ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ወጥ ሆነዉ መቅረብ የለባቸዉም፡፡ምክንያቱም የመማር ፍልጎታቸዉንም ሆነ ችሎታቸዉን ከመገደባቸዉም በላይ አሰልቺ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡በማለት ከሚገልጹት ሀሳብ ጋር ይቃረናል፡፡

በተተኳሪዉ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የቀረቡ በርካታ ሰዋስዋዊ መልመጃዎች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአቀራረብ መርህን ተከትለዉ የቀረቡ መሆናቸዉን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ይኸዉም CunningWorth(1995)፣ Harmer(1997) ፣LarsenFreeman(1991) Nunnan(1991) በዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ የታላሚዉን ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለጻ አይቀርብም:: በቅድሚያ ህግጋቱን ሊያሳዩ የሚችሉ ምሳሌዎች ለተማሪዎች ይቀርባሉ ተማሪዉም ምሳሌዉን በማጤን የቋንቋ ህግጋት ምን ሊሆን እንደሚችል ይገምታል፡፡በሚል ካቀረቡት ሀሳብ ጋር ይደጋገፋሉ፡፡

በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የቀረቡ በርካታ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች እየተደጋገሙ መቅባቸዉን በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ይኸዉም Tayler (1949) ፣ Larsen Freeman (1991) ተከታታይነት በአንድ የክፍል ደረጃና በቀጣዮቹ የክፍል

ደረጃዎች ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ሳይቆራረጡ እየተደጋገሙ መምጣትን የሚመለከት ነዉ፡፡በማለት ካቀረቡት ሀሳብ ጋር ይደጋገፋል፡፡

በ5ኛና 6ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ ከቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል ዉስን ይዘቶች ስፋትና ጥልቀታቸዉን እየጨመሩ የተደራጁ ሲሆን አብዛኛዎቹ ይዘቶች ተለጣጣቂነታቸዉን ሳይጠብቁ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ተደራጅተዉ መቅረባቸዉን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ይህም LarsenFreeman (1991)ተለጣጣቂነት በአንድ የክፍል ደረጃ ወይም በተከታታይ የክፍል ደረጃዎች የሚቀርቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መጀመሪያ ከቀረበዉ ይዘት ተነስቶ ነገር ግን ስፋትና ጥልቀት አግኝቶ መምጣትን የሚመለከት ነዉ፡፡ከሚሉት ሀሳብ ጋር ይቃረናል፡፡

ጠቅለል አድርገን ስንመለከተዉ በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከአቀራረብ አንጻር ክፍተቶች የሚስተዋሉባቸዉ ቢሆንም ይዘቶቹ እየተከታተሉ መቅረባቸዉ ደግሞ ከአደረጃጀት አንጻር የመጻህፍቱን ጥንካሬ ያሳያል፡፡ወደሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት: ማጠቃለያ መደምደሚያና የመፍትሄ ሃሳብ

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዓላማ በደቡብ ክልል ስራ ላይ ባሉ የ5ኛና 6ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል መገምገም ነዉ፡፡ በዚህም መሰረት ጥናቱ ምላሽ ሊሰጥባቸዉ ያነሳቸዉ መሰረታዊ ነጥቦች የሚከተሉት ነበሩ፡፡

1.በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከአቀራረባቸዉ አንጻር ለቋንቋዉ ቅርጽ፣ፍቺና አጠቃቀም የሰጡት ትኩረት ምን ይመስላል?

2. በ5ኛና 6ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከአደረጃጀት አንጻር የይዘቶች ተከታታይነት ምን ይመስላል?

3 በታላሚዎቹ መማሪያ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከአደረጃጀት አንጻር የይዘቶቹ ተለጣጣቂነት ምን ገጽታ አለዉ? የሚሉት ናቸዉ፡፡

ለነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ተፈትሸዋል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎችና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተመርጠዋል፡፡ በዚህም ተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከአቀራረብ አንጻር ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር መርህን ያላካተቱ መሆናቸዉን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ዉጤት ተኮር በሆነ ስልት የቀረቡት ይዘቶች ሂደት ተኮር በሆነ ስልት ከቀረቡት ይዘቶች አብላጫዉን እንደሚይዙ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ይኸዉም አብዛኛዎቹ ይዘቶች የቋንቋዉንቅርጽ የሚተነትኑ እንጅ ቅርጽን ከአጠቃቀም ጋር አዋህዶ ከማቅረብ አንጻር ክፍተቶች ይስተዋሉባቸዋል፡፡ ሆኖም ግን በርካታ ሰዋስዋዊ መልመጃዎች በምሳሌዎች እየታገዙ መቅረባቸዉ ከጠንካራ ጎን የሚጠቀስ ነዉ፡፡ ሌላዉ በ5ኛና 6ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከአደረጃጀት አንጻር የይዘቶቹ ተከታታይነት ምን እንደሚመስል በተደረገዉ ግምገማ በርካታ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች ዉስጥ እየተደጋገሙ መቅረባቸዉን ማስተዋል ተችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አብዛኛዉ በ5ኛ ክፍል የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ እየተከታተሉ መቅረባቸዉን የጥናቱ ዉጤት ያመላክታል፡፡ ይኸዉም ከአደረጃጀቱ ጠንካራ ጎኖች ይጠቀሳል፡፡ ሌላዉ በታላሚዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች የተለጣጣቂነት ሁኔታ ምን እንደሚመስል በተደረገ

ፍተሻ ዉስን ይዘቶች ከግልጽነት ወደ ዉስብስብነት፣ ከቀላል ወደ ከባድ የተደራጁ ሲሆን አብዛኛዎቹ ይዘቶች ግን ስፋትና ጥልቀታቸዉን ሳይጨምሩ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ተደራጅተዉ መቅረባቸዉን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ይህም በመማሪያ መጻሕፍቱ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከአደረጃጀት አንጻር ከታዩ ክፍተቶች መካከል የሚጠቀስ ነዉ፡፡ በአጠቃላይ በመማሪያ መጻሕፍቱ የተካተቱ አብዛኛዎቹ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች የቋንቋዉን ቅርጽ የሚተነትኑ ሲሆኑ ለአጠቃቀም የሰጡት ትኩረት ዝቅተኛ መሆኑን ጥናቱ መልሷል፡፡ ከአደረጃጀት አንጻር ደግሞ በርካታ ይዘቶች እየተደጋገሙ መቅረባቸዉ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ከቀረቡት ይዘቶች መካከል የተወሰኑት ተለጣጣቂነታቸዉን ጠብቀዉ የተደራጁ ሲሆኑ የተወሰኑት ደግሞ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ተደራጅተዉ መቅረባቸዉን በሰነድ ፍተሻ የተገኘዉ ዉጤትና በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻህፍት ለሚያስተምሩ መምህራን ከቀረቡት መጠይቆች የተገኙ ምላሾች አረጋግጠዋል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

በ5ኛና 6ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት በተመለከተ የተሰበሰቡ መረጃዎች ከተተነተኑና ከተብራሩ በኃላ በጥናቱ ዉጤት መሰረት ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል፡፡

የጥናቱ ዉጤት እንደሚያመለክተዉ ከሰዋስዉ ትምህርት አቀራረብ መርህ አንጻር በ5ኛና 6ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ያልተካተተ መሆኑ በአንድ ክፍል ዉስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የተለያዩ እንደመሆናቸዉ መጠን በትምህርት አቀባበላቸዉ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻህፍት ዉስጥ የቀረቡ አብዛኛዎቹ ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ወይም በምሳሌ እየታገዙ የቀረቡ በመሆናቸዉ የተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎት ያዳብራሉ፤ለመማር ያነሳሳሉ፤ኣዕምሮኣቸዉን በጥልቀት እንዲጠቀሙበት ያደርጋሉ፡፡በ5ኛና 6ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የቀረቡ አብዛኛዎቹ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች የቋንቋዉን ቅርጽ የሚተነትኑ እንጅ ቅርጽን ከአጠቃቀም ጋር አዋህዶ ከማቅረብ አንጻር ክፍተት የሚታይባቸዉ በመሆናቸዉ የተማሪዎችን በቋንቋ የመገልገል ችሎታ ይገድባሉ፡፡

በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት የቀረቡ በርካታ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች እየተደጋገሙ የቀረቡ በመሆናቸዉ ይዘቱ የመታወስ እድሉ ከፍተኛ ይሆናል፤ይዘቱን

በተገቢዉ ሁኔታ ለተግባቦት እንዲያዉሉት ይረዳል። ሌላዉ በታላሚዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የተደራጁ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከተለጣጣቂነት አንጻር አብዛኛዎቹ ይዘቶች ስፋትና ጥልቀታቸዉን ሳይጨምሩ የተደራጁ መሆናቸዉ በጥናቱ ተረጋግጧል። ይኸዉም ተማሪዎች የሰፋና የጠለቀ ግንዛቤ እንዳይጨብጡ ያደርጋል፤ኣዕምሮአቸዉን እንዳይጠቀሙበት ያደርጋል፤የቋንቋ አጠቃቀም ዕድገታቸዉን ይገድባል።

## 5.3 የመፍትሄ ሃሳቦች

በዚህ ጥናት ዉስጥ የታዩ ጠንካራ ጎኖች ተጠናክረዉ እንዲቀጥሉና ደካማ ጎኖችም ማሻሻያ ይደረግባቸዉ ዘንድ የሚከተሉት የመፍትሄ ሃሳቦች ተጠቁመዋል።

በ5ኛ ክፍልም ይሁን 6ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ መርህ ያልተካተተ መሆኑን ቀደም ሲል ለመጠቆም ተሞክሯል።በመሆኑም የስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች የሰዋስዉ ትምህርት አቀራረብ መርሆዎችን በመከተል ተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት በሚሻሻሉበት ወቅት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ መርህ ተካትቶ ቢቀርብ፤

በታላሚዎቹ የመማሪያ መጻሕፍት የቀረቡ በርካታ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች የቋንቋዉን ቅርጽ የሚያስተምሩ እንጂ ሰዋስዉ ተግባቦት ላይ እንዲዉል የሚጋብዙ አይደሉም ።ይኸዉም የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችን ከማሳካት አንጻር ችግር የሚስተዋልባቸዉ ናቸዉ።ምክንያቱም ሰዋስዉና ክህል ተነጣጥለዉ የሚታዩ አይደሉምና።በመሆኑም የስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች ተተኳሪዎቹን መጻሕፍት በሚያሻሽሉበት ወቅት ለቅርጽ፣ፍቺና አጠቃቀም ተመጣጣኝ ትኩረት ቢሰጡ፤

በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ሰዋሰዋዊ የትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች እየተደጋገሙ መቅረባቸዉ ከጠንካራ ጎን የሚጠቀስ ቢሆንም የተወሰኑ ይዘቶች በአንድ ምዕራፍ ዉስጥ እየተከታተሉ የቀረቡ መሆናቸዉን ማረጋገጥ ተችሏል። በመሆኑም የመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆችና አሻሻዮች በቀጣይ በሚያዘጋጁት መማሪያ መጽሀፍት ዉስጥ ይህን አደረጃጀት አሻሽለዉ ቢያቀርቡ፤

በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ አብዛኛዎቹ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከተለጣጣቂነት አንጻር ችግሮች ይስተዋሉባቸዋል።ነገር ግን በመማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የሚቀርቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ከክፍል ክፍልና ከምዕራፍ ምዕራፍ ተመሳሳይ በሆነ

መልኩ መቅረባቸዉ ፋይዳ አይኖረዉም፡፡ይልቁንም ስፋትና ጥልቀታቸዉን እየጨመሩ መደራጀታቸዉ ጠቀሜታዉ የጎላ ነዉ፡፡ ስለዚህ የስርዓተ ትምህርት አዘጋጆችና አሻሻዮች ይህን የአደረጃጀት ስልት ታላሚዎቹ የመማሪያ መጻሕፍት በሚሻሻሉበት ወቅት ተግባራዊ ቢያደርጉ፤

በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶችን በሚገባ ፈትሸዉ ለተማሪዎቻቸዉ በተሻለ መልኩ ለማቅረብ ያስችላቸዉ ዘንድ የትምህርት ባለሙያዎች የሰዋስዉ ትምህርት ዓላማና የስነ ትምህርታዊ ሰዋስዉ ንድፈ ሃሳቦችን የሚመለከቱ ተከታታይ ስልጠናዎችን ለመምህራን ቢሰጡ፤

በተጨማሪም የስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች፣ የትምህርት ባለሙያዎችና የቋንቋ መምህራን በየወቅቱ የሚዘጋጁ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶችን የሚያስተምሩ መጻሕፍትን ቢያነቡና በግብዓትነት ቢጠቀሙ፤

## ዋቢ መጻሕፍት


ሐዋዝ ወልደየስ፡፡(2000)፡፡«በአዲስ አበባ ከተማና አማራ ክልል አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አደረጃጀትና አቀራረብ ንጽጽራዊ ጥናት»፡፡ የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

ሰሚራ አሊ፡፡(2010)፡፡«በደቡብ ክልል በ2009 ዓ.ም ሥራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ»፡፡ የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሁፍ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ባየ ይማም ፡፡(2000)፡፡የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አዲስ አበባ፣ እሌኒ ማ.ኃ.የግ. ማህበር፡፡

ኢያሱ መሰለ፡፡(2003)፡፡‹‹በ 1999 ዓ.ም በተሻሻሉት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት የስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ይዘት አመራረጥ፣አቀራረብና አደረጃጀትግምገማ››፡፡ የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

እምሻው ማሞ፡፡ (2005)፡፡ ‹‹ለ9ኛና ለ10ኛ ክፍል በተዘጋጁ (1968-2004ዓ.ም) የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ››፡፡ የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡(ያልታተመ)፡፡

እስሌማን አባይ፡፡(2003)፡፡ ‹‹በ12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ ከሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው አንፃር››፡፡የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡(2009)፡፡ የምርምር መሠረታዊ መርሆች አተገባበር፡፡(5ኛእትም) አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ጌታሁን አማረ፡፡(1989)፡፡ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ፡፡ አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

Batstone, R. (1994) .Language teaching Grammer. Oxford, Oup.

Brown, D. (1994).Principles of Language learning and Teaching.USA, Prentice Hall.

Brown,D.et.al.(2000). Language and linguistics.Encyclopedia vol.9, oxford, Ltd.

Bygate,M.et.al.(1994).Grammar and Language teacher.Hemel Hempstead prentice Hall.

Chalker,s.(1991).Current English Grammer.London,Macmillon Education Ltd.

Cook,V.(2001).Second Language learning and language teaching. Newyork, oxford university press.

Cunningsworth, A. (1984).Evaluating and selecting FEL. Teaching materials (5th print).Oxford, Heinman.

____ (1995).Choosing your course book.Oxford, Heineman.

Donough, J and show. (1995).Material and method in ELT. ATeachers Guides oxford, Blanck Wall.

Ellis, R. (2000). The place of Grammar instruction in second (Foreign language curriculum, "In Brown, K. (ed.) Language and Linguistics Encyclopida. Vol.9, oxford, p28-54.

Good,Cv. (1973). Dictionary of Education. Newyork, MacGrow Hill.

Grant,N. (1988). Making the most of your Text Book. Longman, Longman Group.

Harmer, J. (1987).Teaching and Learning Grammar. London, Longman.

______(1991).The practices of English Language Teaching.London, Longman.

Hdfield,J.and Hdfield, C. (2008). Introducation to teaching English.Oxford,Oxford Univerity press.

LarsenFreeman,D.(1986).Techniques and principles in Language Teaching.Oxfords, Oup.

_____ (1991).Teaching Grammar.In celce-murcia, M(Ed).Teaching English as a second or foreign Language.Boston, Heinman and Heinman Publishers, p246-295.

Michal, B. (2007). « Pedagogical Grammar» Http// Knolgoole.com /K/7/8/2010.

Nunan, D. (1988). Syllabus Design.Oxford, Oup.

______ (1991). Language Teaching Methodology Atext book For Teachers. oxford, international book distribution Ltd.

Richard J,C.(2001).Curriculum Development in Language Teaching.Cambridge Universty Press.

Stern, H. (1992).Issues and options in Language Teaching.Oxf0rd,Oxford University Press.

Taba, H. (1962).Curriculum Development Theory and practice.Newyork, Harcourt Brace Jovanovich.

Tayler, W. (1949).Basic principles of curriculum and Instruction.Chicago, The University of Chicago Press.

Ur, P. (1988).Grammar practices activities.Cambridge, Cup.

________ (1996).Acourse in Language Teaching.Cambridge, Cup.

Woods, E. (1995).Introducing Grammar.London,Lond Press.

## አባሪ 1. ለመምህራን የቀረቡ ቃለ መጠይቆች

ጅማ ዩኒቨርስቲ

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

በመምህራን የሚመለሱ የቃል መጠይቆች

ዉድ መምህራን ፡-

የዚህ መጠይቅ ዓላማ በደቡብ ክልል ስራ ላይ ባሉ የ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል ለመገምገም የሚያስችል መረጃ ማሰባሰብ፣ችግሩን በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ ማቅረብና የጥናቱን ዉጤት መነሻ በማድረግ የመጻሕፍት አዘጋጆች በተተኳሪዎቹ አማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ዉስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን አስመልክቶ በታዩ ጠንካራ ጎኖች እንዲቀጥሉ ደካማ ጎኖቻቸዉን ደግሞ በማረም የተሻለ የሰዋስዉ ይዘቶችን ለማዘጋጀት የሚያስችል ሃሳብ መጠቆም ነዉ፡፡ስለዚህ መጠይቁን በጥንቃቄ በመመለስ ቀና ትብብራችሁን እንድታደርጉ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡ዉድ ባልደረቦቼ ዉድ የሆነዉን ጊዜያችሁን መስዋት በማድረግ ለምታደርጉልኝ ቀና ትብብር ምስጋናዬ ከልብ ነዉ፡፡

የመምህራን አጠቃላይ መረጃ

መምህር 1

1.የሚያስተምርበት ትምህርት ቤት ፡-ዮክጭጪ 1ኛና 2ኛ ሳይክል

2.ጾታ፡-ወ

3.የትምህርት ደረጃ፡-ዲግሪ

4.የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት፡-አማርኛ

5.የአገልግሎት ዘመን ፡-10 ዓመት

6.የሚያስተምርበት የክፍል ደረጃ፡-5ኛና 6ኛ

ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ቀን፡-12/8/2013

መምህርት 2.

1.የሚያስተምርበት ትምህርት ቤት፡-ጫሻ1ኛና 2ኛ ሳይክል

2.ጾታ፡-ሴ

3. የትምህርት ደረጃ፡-ዲግሪ

4.የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት፡-አማርኛ

5.የአገልግሎት ዘመን ፡-8 ዓመት

6.የሚያስተምርበት የክፍል ደረጃ፡-5ኛ

ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ቀን:-13/8/2013

መምህር 3.

1.የሚያስተምርበት ትምህርት ቤት ፡-ጫሻ1ኛና 2ኛ ሳይክል

2.ጾታ፡-ወ

3.የትምህርት ደረጃ ፡-ዲግሪ

4.የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት፡-አማርኛ

5.የአገልግሎት ዘመን ፡-8 ዓመት

6.የሚያስተምርበት የክፍል ደረጃ ፡-6ኛ

ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ቀን፡-13/8/2013

መምህርት 4

1.የሚያስተምርበት ትምህርት ቤት፡-ጌጫ 1ኛና 2ኛ ሳይክል

2.ጾታ ፡-ሴ

3.የትምህርት ደረጃ ፡-ዲግሪ

4.የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት፡-አማርኛ

5.የአገልግሎት ዘመን፡- 14 ዓመት

6.የሚያስተምርበት የክፍል ደረጃ ፡- 5ኛና 6ኛ

ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ቀን፡-14/8/2013

የቀረቡ መጠይቆች

1. በአማርኛ በመማሪያ መጽሀፍ ከተካተቱት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ዉስጥ ቋንቋዉን ሰዋስዋዊ ስርዓት የሚያሳዉቁ ገለጻዎችን በመስጠት በዛዉ መነሻነት ተማሪዎች መልመጃዎችን እንዲሰሩ የሚያደርጉ አቀራረቦች አሉ፡፡
2. በመማሪያ መጽሀፉ ዉስጥ ከቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ዉስጥ ምሳሌዎችን በማቅረብ በዛዉ መነሻነት ተማሪዎች መልመጃዎችን እንዲሰሩና የቋንቋዉን ስርዓት ወደ መለማመድ እንዲሸጋገሩ የሚያደርጉ አቀራረቦች አሉ፡፡
3. በመማሪያ መጽሀፉ ዉስጥ ከቀረቡት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ዉስጥ የቋንቋዉን ሰዋስዋዊ ስርዓት ብቻ የሚያሳዉቁ አቀራረቦች ይገኛሉ፡፡
4. በመማሪያ መጽሀፉ ዉስጥ ከተካተቱት የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል ተማሪዎች በቋንቋዉ እንዲገለገሉ ወይም የሀሳብ ልዉዉጥ እንዲያደርጉ የሚያስችሉ አቀራረቦች አሉ፡፡
5. በመማሪያ መጽሀፉ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች እየተከታተሉ ቀርበዋል፡፡
6. በመማሪያ መጽሀፉ ዉስጥ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች አሁን ካሉበት የክፍል ደረጃ በፊት የተዋወቋቸዉ ነበሩ፡፡
7. በመማሪያ መጽሀፉ ዉስጥ ተከታትለዉ የቀረቡ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀታቸዉን እየጨመሩ ነዉ፡፡
8. በ5ኛ ወይም 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ዙሪያ ያስተዋሉት ደካማና ጠንካራ ጎኖችን ቢዘረዝሩ
9. በ5ኛ ወይም 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የሚካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች በምን መልኩ መቅረብና መደራጀት እንዳለባቸዉ የራስዎን አስተያየት ይስጡ